# ክርስቶስ በገዛ ቃሉ የተገለጠ ነው

አንገታችንን ዝቅ እናድርግ።

የታላቁ መንጋ፡ እረኛ የሆንክ፡ ጌታ ኢየሱስ ሆይ፡ በልባችን ላፈሰስከው ፍቅር፡ ጌታ ሆይ ልንከፍልህ የማንችለው ታላቅ ዕዳ አለብን። ራሳችንን ዝቅ አድርገን በፊትህ ስንቆም እጅግ የማንገባ ሆነን ይሰማናል። ከስህተታችንና ከኃጢአታችን ሁሉ እንድታነጻን እንለምንሃለን። ዛሬ ሰውነታችንን እንድታበረታ እንጸልያለን። እዚህ እንደሚታየው ከተለያዩ ቦታዎች፡ በስልክና በመሐረብ በሚመጡ ጥያቄዎች መሰረት፡ ብዙዎች ታመዋል ተቸግረዋልም።

2 የዚህን ዓለም ታሪክ አሁን እየቋጨን እንዳለን እናምናለን፡ በቅርቡም ጊዜ ወደ ዘላለም ውስጥ ይሸጋገራል፡ ለዚያችም ሰዓት ዝግጁ መሆን እንፈልጋለን። ዛሬ ጧት እዚህ የተሰበሰብነውም፡ ለዚያ ጊዜ ለመዘጋጀት ነው። ዛሬ ጧት በአገሪቱ ዙሪያ፡ ከዳር እስከ ዳር በርካታ በሰልክ-መሰመሮች የሚያዳምጡን እንዳሉ ተነግሮኛል። ድምፃችን በሚሰማበት ቦታ ሁሉ፡ ያች ትንሽ ቡድን የተባረከች ትሁን። በመካከላቸው ያሉትን የታመሙትን ፈውስ፡ ነፍሳቸውንም ከክፉ ነገር ሁሉ እንድታነጻ እጸልያለሁ። እኛም በዚህ ታላቅ ዕድል እንድንባረክ፡ ዛሬ ጧት፡ እዚህ ተብርናክል ውስጥ እርዳን።

3 ዛሬ በተጻፈው ቃልህ እንድትናገረን እንጠይቅሃለን፡ የሚያስፈልገንንም ነገር መንፈስ ይግለጥልን፡ አሁን በአገር አቀፍ ደረጃ እንደ መሰብሰባችን፡ ትንሽ ህዝብ መሆናችን ቢሰማንም፡ ነገር ግን በኢየሱስ ክርስቶስ ስላመንን፡ በዳኑት ሰዎች መካከል ሰፍራ አለን። ጌታ ሆይ፡ ይህ ይሁንልን።

4 አገልግሎቱን ጨርሰን በመላው አገሪቱ ወደሚገኙት የየራሳችን ቤቶች ስንሄድ፡ ልክ እንደ ኤማሁስ መንገደኞች፡ እንዲህ ማለት ይሁንልን፡ “በመንገድ ሲናገረን ልባችን ይቃጠልብን አልነበረምን? ”

5 አሁን፡ አባት ሆይ፡ በመላው አገሪቱ ላሉትና አሁን ለሚከታተሉ ምርጥ ክርስቲያኖች፡ እኔ የ—የምናገረው ማንኛውም ነገር በእርግጥ በቂ እንደማይሆን አውቃለሁ፡ በ—በቂ ሊሆን አይችልም። እኔ የምናገረው ነገር ምንም ጠቀሜታ ሊያመጣ አይችልም፡ ምክንያቱም ሁላችንም በአንድ ምድብ ውስጥ ነንና። እኛ ሟች፡ የሰው ልጆች ነን። ዳሩ ግን ታላቁ መንፈስ ቅዱስ ይናገር፥ ቃሉን አንስቶ ራሱን ይግለጥ። አሁን እርሱን እየጠበቅን ነው፡ በኢየሱስ ስም። አሜን።

መቀመጥ ትችላላችሁ።

6 በመጠኑ... ራሴን እያስገረምኩኝ ነው። ምናልባት እዚያ ቱክሰን ሆና፡ እየሰማች ከሆነ፡ ለባለቤቴ ነግሬያት ነበር፡ ስመለስ ምንም ዓይነት አገልግሎት ይኖረኛል ብዬ አላሰብኩም ነበር፥ ልብስ እንኳ አላመጣሁም። ምራቴን-እንዲህ-አልኳት፡ ኮቴን ተኩሳልኝ ነበር፡ እናም እንዲህ አልኳት፡ “ከቱልፒቱ ጀርባ ነው የምቆመው... ሱሪው ሌላ፡ ኮቱ ሌላ መሆኑን አያዩትም” አልኳት። ወደ ቤት

ስሄድ የለበስኩት ነው። ነገር ግን፡ ሜዳ፡ ሽሚዜንና ሁሉን ነገር አስተካክላ ተኩሳልኛለች፡ ስለዚህ ሁሉም... አትጨነቁ፥ ሁሉም ነገር የተስተካከለ ነው።

7 አሁን፡ እዚህ አንድ የጸሎት ጥያቄ አለን፡ አንድ በጣም የተወደደ ወንድም... ዛሬ ጧት በ—በፕሬስኮት፡ እ—እዚያ አሪዞና፡ ፕሬስኮት ያሉ፡ በስልክ መስመር ላይ የገቡ፡ ይመስለኛል። እንደተረዳሁት፡ የእህት ሜርሲየር አባት የሆኑት ወንድም ኮጊንስ ወደዚህ ስብሰባ በመምጣት ላይ ሳሉ፡ በድንገተኛ የልብ ህመም፡ ወደ ሆስፒታል መወሰድ ነበረባቸው። እንዲሁም፡ ደግሞ፡ ወንድም ጁኒየር ጃክሰንም፡ በሚቀጥለው ራዲዮ፡ ወይም በሚቀጥለው የስልክ መስመር በክላርክስቪል፡ ወይም በኒው አልባኒ እየተከታተለ ይመስለኛል፡ አባቱም በጉበት ካንሰር ምክንያት፡ ከባድ ቀዶ ጥገና አድርገው በሆስፒታል ውስጥ እንዳሉ ሰምቻለሁ። ስለዚህ በእርግጠኝነት እነዚህን በጸሎታችን ልናስባቸው እንፈልጋለን። እዚህም፡ ሌሎች አሉ፡ ነገር ግን ጊዜ መውሰድ አንፈልግም። እግዚአብሔር ስለ እነርሱ ሁሉንም ያውቃል፡ ስለዚህ አሁን ለእነርሱ እንጸልይ።

8 ውድ አምላክ ሆይ፡ ያ የተወደደው፡ ሽማግሌው፡ እጆቹ-የተሸበሸቡት ሰው፡ በአገልግሎቱ መስክ የቆየው አዛውንት፡ ወንድም ኮጊንስ፡ ዛ... ዛሬ ጧት በልብ ህመም እየተሰቃየ፡ በሆነ ቦታ፡ በሆስፒታል ውስጥ ተኝቷል። አምላክ ሆይ፡ ያቺ ምስኪን ያረጀች ልብ በብዙ መከራ ውስጥ አልፋለች። እንድትረዳው፡ እጸልያለሁ፡ አምላክ ሆይ። አድርገው። እሱም... ልክ እንደ ሁላችንም እርሱም ህይወትን ይወዳል፡ መኖርም ይፈልጋል። ጌታ አምላክ ሆይ፡ አድርገው። እንድትፈውሰውና ከዚያ እንድታወጣው፡ በመላው አገሪቱ ሆነን በኢየሱስ ስም እንጸልይለታለን። ይህን እንደምታደርግ እናምናለን፥ በቀጥታ ወደ ስብሰባውም ይመጣል።

9 ለወንድም ጃክሰንም እንጸልያለን፡ እንደ ጁኒየር ያለ ግሩም ልጅ፡ ወደዚህ ዓለም ያመጣው ውድ አባቱ ለሞት ተቃርቦ ተኝቷል። ውድ አምላክ ሆይ፡ እንድትፈውሰው፡ እ—እ—እጸልያለሁ። የማይቻል እንደሚመስል አውቃለሁ። የህክምና ባለሙያዎች፡ ዶክተሮች፡ በ—በእንደዚህ ዓይነት ሁኔታ ምን ማድረግ እንዳለባቸው አያውቁም። ነገር ግን፡ በጉበት ካንሰር ምክንያት፡ በሉዊስቪል ያሉ፡ ታላላቅ ሐኪሞች፡ "በህይወት ለመቆየት ጥቂት ሰዓታት ብቻ ቀርተውታል፡" ባሉት ጊዜ፡ ወንድም ሆልን እናስታውሳለን። ዛሬም በህይወት አለ፡ ይሄ ከሆነ ደግሞ ሃያ-አምስት ዓመታት አልፈዋል፡ ይህ የሆነው በጸጋህ ነው። ስለዚህ ዛሬ ወንድም ጃክሰንን እንድትፈውሰው እጸልያለሁ፡ ጌታ ሆይ፡ ጸጋህና ምህረትህ ከእርሱ ጋር ይሁን።

10 እዚህ በጸሎት ጥያቄ የተቀመጡትን እነዚህን የተከመሩ መሐረቦችና ጨርቆች፥ እንዲሁም ሌሎች ነገሮችን ሁሉ፡ አባት ሆይ አንተ ታውቃቸዋለህ። ለሁሉም ፈውስን እንድትሰጣቸው እጸልያለሁ። በኢየሱስ ክርስቶስ ስም። አሜን።

11 አሁን ስጀምር፡ ዛሬ ጠዋት፡ በመጀመሪያ ደረጃ፡ ባለፈው እሁድ፡ ወደዚህ እመጣለሁ ብዬ አላሰብኩም ነበር። ከዚያም እንደገና፡ ባስታወቅን ጊዜ፡ መጣሁ። ወንድም ኔቪል እንድናገር አደረገኝ! ከዚያም ዛሬም እንደምንገኝ አሳወቅን፡ ዳሩ ግን በመላው ሀገሪቱ ላሉ ሰዎች አልተነገረም ነበር። አሁን ደግሞ ይህ ተሌፎን ሲስተም አለን፡ ይህም እጅግ በጣም፡ በጣም

ጥሩ ነው። ሰዎች እዚያው ቤታቸው ተቀምጠው ወይም… በየሰፍራዎቻቸው፡ በየቤተክርስቲያኖቻቸውና፡ በመሳሰሉት ቦታዎች ተሰብሰበው፡ አገልግሎቱን መሰማት ይችላሉ። ይህንን እጅግ አደንቃለሁ።

12 አሁን እዚህ የተቀመጡትን ሳይ፡ ባለፈው እሁድ በመልእክቱ ላይ ከተናገርኩት ጋር በተያያዘ፡ በዚህ ባለፈው ሳምንት ብዙ ጥያቄዎች መጥተው ነበር። አሁን ርዕሱን ምን እንዳልኩት የረሳሁት ይመስለኛል። ሆኖም እዳዎቻችሁን ስለመክፈል አንዳች ነገር ተናግሬ ነበር። ታውቃላችሁ፡ ምንም ብትናገሩ፡ በብዙዎች ዘንድ በተሳሳተ መንገድ ይረዳል። ይህ የሆነው… በተሳሳተ መንገድ መረዳት ስለፈለጉ አይደለም፡ ነገር ግን ዝም ብላችሁ በተሳሳተ መንገድ ትረዱታላችሁ።

አሁንም አንድ ሰው እንዲህ አለ፡ “መኪና መግዛት እንችላለን? ” ወይም፡ “ምን ላድርግ… ”

አሁን፡ ኢየሱስ የተናገረው፡ ወይም መጽሐፍ ቅዱስ እዚያ ላይ “ለማንም ዕዳ አይኑርባችሁ፡” ያለው፡ ሰለዚያ አይደለም። እነዚያ ልትከፍሏቸው የምትችሏቸው የዘገዩ ዕዳዎች ናቸው። ክፈሏቸው። አይ እንደዛ… ለማንም ዕዳ አይኑርባችሁ ማለት ያ ነው። እንደዛ ማለት አይደለም… ማይ! የቤት ኪራያችንን፡ የስልክ ሂሳባችንንና፡ እኛ… የመሳሰሉትን-መክፈል አለብን። እ—እነዚህ ነገሮች አሉብን፡ እንከፍላቸዋለንም። ነገር ግን፡ መክፈል የምትችሉት፡ የዘገየ ዕዳ ካለባችሁ፡ ክፈሉት። አያችሁ? አሁን፡ እንዲህ ያለ ነገር በእናንተ ላይ ተንጠልጥሎ አትቀጥሉ።

13 ልጅ እያለሁ በአንድ ወቅት፡ ታምሜ የነበረበትን ጊዜ አስታውሳለሁ። ከሆስፒታል ሰወጣ ሁለት ሺህ ዶላር ገደማ ዕዳ ነበረብኝ። እንዲሁም የመድኃኒት ቤቱ ባለቤት የነበሩት፡ ሚስተር ሰዋንጀር፡ የሦስት ወይም አራት መቶ ዶላር፡ የመድኃኒት ዕዳ ነበረብኝ። እርሱ ፈጽሞ አያውቀኝም ነበር። ያም ሰው… ወደ እርሱ ሄድኩ። አላውቀውም ነበር። ያም ሆኖ ግን ዝም ብሎ፡ ይልከው ነበር እንጂ፡ ለመላክ ከልክሎኝ አያውቅም። እኔም፡ “ዕዳ አለብኝ” አልኩት። እናም… ሰዋንጀር፡ ይመስለኛል… በኮርት አቬኑና በስፕሪንግ አካባቢ የነበረው ሚስተር ሜስን ነበረ።

እንዲህም አልኩት፡ “ዕዳ አለብኝ። አ—አሁንም እጅግ ደካማ ነኝ፡ ነገር ግን ሥራ ለመጀመር እየሞከርኩ ነው። አሁን፡ ልከፍልህ ካልቻልኩ… ” ገና አዲስ ክርስቲያን ነበርኩ። “በመጀመሪያ ደረጃ፡ ሚስተር ሜስን፡ ለእግዚአብሔር ካለብኝ ግዴታ አንጻር፡ አሥራት ልሰጠው ይገባኛል። አስቀድሜ፡ ለእርሱ አሥራቴን መሰጠት እፈልጋለሁ፡” አልኩት። በመቀጠልም፡ “ቀጣዩ ግዴታዬ ዕዳዎቼን መክፈል ነው” አልኩት። “አባቴ ታማሚ ነው፡ እርሱም… እሱም… በቤተሰቡ ውሰጥ አሥር ልጆች ነን፡” አልኩት። ነገር ግን እንዲህ አልኩት፡ “እኔ… በየደመወዝ ቀኑ፡ ከዕዳው ላይ ከሃያ-አምስት ሳንቲም በላይ ልከፍልህ ባልችልም፥ ያችን ሃያ-ምስት ሳንቲም እንኳን መክፈል ካልቻልኩ፡ መጥቼ እነግርሃለሁ። ‘በዚህኛው ጊዜ መ—መ—መክፈል አልቻልኩም፡’ ብዬ እነግርሃለሁ።” አሁን፡ በእግዚአብሔር እርዳታ፡ ሁሉንም ከፍዬ ጨረስኩት። አያችሁ? ነገር ግን ለማለት የፈለኩት ይህንን ነው፡ አያችሁ? ዝም ብሎ አንድ ሰው…

14 አህ፡ እዚህ ቤተክርስቲያን ያለ አንድ ክርስቲያን በአንድ ወቅት መኪናውን አሰርቶ መጣ፡ ያም ሰው ወደዚህ መጥቶ… ሰውዬው፡ "እከፍልሃለሁ። ቅዳሜ ደመወዝ ይከፈለኛና፡" ወይም እንደዚህ ያለ ነገር አለው። ነገር ግን በጭራሽ አልከፈለውም። ሳምንታት በሳምንታት ላይ ተቆጠሩ፡ ፈጽሞ አልከፈለውም፡ አንዲትም ቃል አልተናገረም። ሰ—ሰውዬው መጥቶ ጠየቀኝ፡ እርሱም… አያችሁ፡ ይህ በቤተክርስቲያን ላይ ጥላሸት ይቀባል። በክርስቶስ ላይ ጥላሸት ይቀባል።

መክፈል ካልቻላችሁ፡ ሄዳችሁ፡ እንዲህ በሉት፡ "ዕዳ አለብኝ፡ እከፍልሃለሁም። እኔ ክርስቲያን ነኝ፡ ነገር ግን እ—እኔ… አሁን መክፈል አልችልም፡ ሌላ… ይህኛው ዕዳ አለብኝ" በሉት። እናም፡ አስታውሱ፡ የምታደርጉት ነገር፡ በእግዚአብሔር መጽሐፍትም ላይ እንደሚገኝ፡ ታውቃላችሁ። ስለዚህ… እኔ ለራሴም ሆነ ለሁላችንም በአንድነት፡ ዝግጁ እንድንሆን፡ እየሞከርኩ ነው፡ ምክንያቱም ወደ አንድ ነገር እየተቃረብን እንደሆነ፡ አንዳች ነገር ሊፈጸም እጅግ እንደተቃረበ እናውቃለንና። ስለዚህ ዝግጁ መሆን እንፈልጋለን። አሁን የጌታ መምጣት እጅግ በተቃረበበት በዚህ ጊዜ፡ ለዚያች ታላቅ ሰዓት ዝግጁ መሆን እንፈልጋለን።

15 አሁን በጌታ እርዳታ ለዛሬ ጠዋት በመረጥኩት አጭር ርዕስ ላይ ለመናገር፡ እንዘጋጅ። ሰዎች በሰልክ-መስመር ስለተገናኙም፡ በተቻለን መጠን እጅግ በአጭሩ እንናገራለን። በመላው ሀገሪቱ ያላችሁ ሁላችሁም… እዚህ ኢንዲያና ውስጥ እንዳለን ዓይነት፡ ደስ የሚል ጠዋት እንዳላችሁ ተስፋ አደርጋለሁ። ከዝናቡ በኋላ አሁን እጅግ ደስ የሚል፡ ቀዝቃዛና፡ መልካም አየር አለን። እጅግ ደስ ይላል።

16 አሁን ከዕብራውያን መጽሐፍ፡ 1ኛ ምዕራፍና፥ ከዮሐንስ ወንጌል፡ 1ኛ ምዕራፍ ላነብ እፈልጋለሁ። ለርዕስ፡ ዕብራውያን 1፥1-3ና፡ ዮሐንስ 1፥1 እናንብብ። ዛሬ ጠዋት ርዕሴ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ የሚደረግ ጥናት ነው። አሁን ዕብራውያን 1፥1ን እናንብብ።

> ከጥንት **ጀምሮ እግዚአብሔር፡ በብዙ… ዓይነትና በብዙ ጎዳና ለአባቶቻችን በነቢያት ተናግሮ፡**
>
> **ሁሉን ወራሽ** ባደረገው፡ **ደግሞም** ዓለማትን በ**ፈጠረበት፡ በልጁ በዚህ ዘመን መጨረሻ ለእኛ ተናገረን፥**
>
> **እርሱም የክብሩ መንጸባረቅና፡ የባሕርዩ… ምሳሌ ሆኖ፡ ሁሉን በሰልጣኑ ቃል እየደገፈ፡ ኃጢአታችንን በራሱ ካነጻ በኋላ፡ በሰማያት በግርማው ቀኝ ተቀመጠ፥**

እንዴት ያለ ውብ ንባብ ነው! አሁን ዮሐንስ 1፥1።

> **በመጀመሪያ ቃል ነበረ፡ ቃልም በእግዚአብሔር ዘንድ ነበረ፡ ቃልም እግዚአብሔር ነበረ።**

17 አሁን፡ የዛሬው ርዕሴ፥ **ክርስቶስ በገዛ ቃሉ የተገለጠ ነው** የሚል ነው። አሁን፡ በዚህ ላይ ለመናገር ወደ መደምደም የመጣሁበት፡ ምክንያት… የተሰበሰብነው የንናገራቸው ነገሮች ዝም ብለን ያገኘነውን ነገር በዘፈቀደ ለመናገር እንዳልሆነ አውቀን፡ ይልቁንም ህዝቡን ለማጽናት የሚረዳ ነገር

መናገር አለብን፡ ምክንያቱም አደገኛና፡ አስፈሪ በሆኑ ውኃዎች ውስጥ ልናልፍ ነውና። አሁንም ቢሆን በእነርሱ ውስጥ በመጓዝ ላይ ነን። አንዳንድ ጊዜ በእኔ ላይ እንደሚሆነው በእናንተም ላይ እንደዚያው እንደሚሆን አስባለሁ፡ በጣም ብዙ በመሆኑ የተነሳ፡ እጅግ አስፈሪ ነው።

18 ከጥቂት ደቂቃዎች በፊት ክፍል ውስጥ፡ ከአንድ ወጣት አገልጋይና ከሚስቱ ጋር፡ እያወራሁ ነበር። ሁለቱም ልክ እንደተቀረው ዓለም፡ በምድር ላይ እንዳሉት ሌሎች የሰው ልጆች ሁሉ ተረብሸው ነበር። እኔም፡ "እስታውሱ፡ የሰይጣን ጡጫ ከፊታችሁ ይጠብቃችኋል" አልኳቸው። ማንንም ብትሆኑ ለውጥ አያመጣም፡ እግዚአብሔር... እርሱ ለዚያች አንዲት ጡጫ መብት አለው። ያ ጡጫ፡ የቱ ቢሆን ትመርጣላችሁ፥ እውር መሆን፡ ወይስ በአርትራይተስ በሽታ ወንበር ላይ መቀመጥ፡ ወይስ መጨነቅ? እያችሁ? ሊመታችሁ የሚችልበት የሆነ ቦታ አለው። ለዚያ ክፍት ቦታ መብት አለው። አሁን፡ ሁልጊዜ ሽፍናችሁ ልትጠብቁት የሚገባው ቦታ ያ ነው። እየኖርንበት ያለውን ይህንን የጭንቀት ዘመን ስናይ!

19 ባለፈው ሳምንት፡ የተቀረጹት የድምጽ ቴፖች፡ በቂ ቦታ በምናገኝበት ከእነዚህ ቀናት በአንዱ የምንናገርባቸውን ታላላቅ አስፈሪ ነገሮች የሚገልጡላችሁ ይመስለኛል፡ ይኸውም በምድር ላይ ስለሚፈሱት እነዚያ የመጨረሻ መቅሰፍቶች መከፈት፡ ይልቁንም፡ እነዚያ ጽዋዎች፡ የጽዋዎቹ መፍሰስ፡ ስለ ሰባቱ ነጎድጓዶችና፡ በምድር ላይ ስለሚመጡት ስለ እነዚያ አስፈሪ ክስተቶች ይናገራሉ። አሁን ሰው፡ ዛሬ ያሉ ሰዎች፡ እጅግ በተረበሸ ሁኔታ ውስጥ ናቸው፥ መላው ዓለም!

20 የባለፈውን ወር **ሪደርስ ዳይጀስት** መጽሔት ብታነቡ፡ በዚያ ያለውን ርዕስ ታስተውላላችሁ፥ ስለ ታላቁ ወንጌላዊ፡ ቢሊ ግራሃም የሚናገር ነው። እጅግ ስለደከመው አገልግሎቶቹን ማካሄድ አልቻለም፡ ስ—ስለዚህም ለአጠቃላይ የጤና ምርመራ ወደ ሜዮስ ክሊኒክ ሄደ። ምንም ዓይነት የጤና ችግር አልነበረበትም፡ ችግሩ በቂ አካላዊ እንቅስቃሴ አለማድረጉ ብቻ ነበር። ስለዚህ ሩጫ፥ አካላዊ እንቅስቃሴ እንዲጀምር አደረጉት። በየቀኑ አንድ ማይል ይሮጣል።

ከዚያም ጽሑፉ በመቀጠል ሳይንስ ዛሬ ያረጋገጠውን ነገር ይናገራል፡ ይኸውም ወጣት ልጆች፡ እነዚህ ትናንሽ ወንዶችና ሴቶች ልጆች፡ "በሃያ ዓመታቸው መካከለኛ ዕድሜያቸው ላይ ይደርሳሉ" ይላል። በሃያ-አምስት ዓመታቸው፡ ብዙ ጊዜ፡ በብዙ አጋጣሚዎች፡ ሴቶች ልጆች በሃያ-አምስት ዓመታቸው፡ የማረጥ ደረጃ ላይ ይደርሳሉ።

ይህንን ታውቁ እንደሆን አላውቅም፡ ነገር ግን ከጥቂት ምሽቶች በፊት እዚህ አገልግሎት ላይ መንፈስ ቅዱስ እየተናገረ ሳለ፡ እዚህ ታች ተቀምጣ የነበረች አንዲት ትንሽ ልጅ፡ መንፈስ ቅዱስ ሁኔታዋን ሲገልጥ የነበረባት ችግር ይኸው ነበር። ለሁለተኛ ጊዜ ተመለከትኳት፡ ዳግመኛ ተመለከትኳት፡ ከዚያም ችግሩ ምን እንደሆነ አየሁ። እኔም፡ "ይህ ሊሆን አይችልም፥ ያች ልጅ እጅግ ትንሽ ናት" ብዬ አሰብኩ። ነገር ግን የማረጥ ችግር ነበረ፡ በሃያ ዓመቷ አካባቢ፡ ሃያ-ሦስት፡ እንደዚያ አካባቢ ነበረች። እያችሁ?

21 እናቴና እናታችሁ ያንን የዕድሜ ክልል የደረሱት በአርባ-አምስትና በአምሳ ዓመት አካባቢ ነበር። ባለቤቴ ያንን ዕድሜ የደረሰችው በሰላሳ-አምስት

ዓመቷ አካባቢ ነው። አሁን ግን ወደ ሃያ ወርዷል። መላው የሰው ዘር በሰብሷል። ታዲያ፡ አካላዊው ሰውነታችን የተዳቀሉ ምግቦችን በመመገብና፡ በውጥረት፡ በዚህ መልክ እየፈረሰ የሚበሰብስ ከሆነ፡ ያ ደግሞ የአዕምሮን ህዋሳት አያበሰብሰውንም? ስለዚህ ሴቶች ራቁታቸውን፡ መንገድ ላይ እንዴት እንደሚወጡ ማየት እንችላለን። በ—በመንገድ ላይ በሰዓት መቶ ሃያ ማይል እንዴት እንደሚከንፉ፡ እነዚህን ሁሉ ነገሮች ማየት እንችላለን። አጠቃላይ ሀገሪቱ፡ መላው ዓለም፡ ይህች ሀገር ብቻ ሳትሆን፡ ነገር ግን በሁሉም ሰፍራ፡ አዕምሮውን የሳተበት ደረጃ ላይ ደርሷል።

22 ከዚያም የጌታ ፈቃድ ሆኖ፡ እነዚያን ሰባቱን ጽዋዎች ሰንከፍትና፡ እነዚያን አሰፈሪ ነገሮች ሰናሳይ... ከጥቂት ጊዜ በኋላ፡ ሰዎች እጅግ ስለሚያብዱ፡ ተራራ የሚያክሉ ጉንዳኖችን የሚያዩ ይመስላቸዋል። ሴቶችን ያሰቃያል፥ ፀጉራቸውን የሚቆርጡትን ሴቶች ሊያሰቃዩ፡ ረጅም ፀጉር ያላቸው፡ አንበጣዎች በምድር ላይ ይመጣሉ፥ እንደ ሴቶች፡ ወደ ታች የተንዘረፈፈ ፀጉር ያላቸው፥ እንደ አንበሳ ያሉ፡ ረዣዥም ጥርሶች ያላቸው፥ በጅራታቸውም ላይ፡ እንደ ጊንጥ መንደፊያ ያላቸውና፡ የ—የመሳሰሉት፡ በምድር ላይ ያሉትን ሰዎች ሊያሰቃዩ ይመጣሉ። ነገር ግን በዚያን ጊዜ ስለዚህ ጉዳይ ምንም ለማድረግ እጅግ ይረፍዳል። አሁኑኑ ተሰተካከሉ። አያችሁ? ሰቃይ!

23 ባለፈው እሁድ ደግሞ ወደ እነዚያ ዑደቶች ሰንገባ፡ በውጫዊው ዓለም ውሰጥ ሰላሉት አምሰት የሰሜት ሕዋሳት ተመልክተን ነበር። ወደ ሰውነት የሚያሰገቡት መግቢያዎች፡ እነዚያ አምሰቱ የሰሜት ሕዋሳት ናቸው። ወደ ሰውነት ልትገቡ የምትችሉበት አንድ መንገድ ብቻ ነው ያለው፡ እርሱም በእነዚያ አምሰት የሰሜት ሕዋሳት ነው፥ ማየት፡ መቅመስ፡ መዳሰስ፡ ማሽተትና፡ መሰማት። ከ—ከሰውነት ጋር ለመገናኘት ሌላ ምንም መንገድ የለም።

24 በዚያ ሰው ውሰጥ መንፈስ የሚባል ሰው አለ፡ እርሱም አምሰት ሕዋሳት አሉት፥ ማሰብ፡ ሀሳብ... ሀሳብ፡ ፍቅር፡ ህሊናና፡ የመሳሰሉት ናቸው። መልካም።

25 አሁን፡ በሰውነታችሁ ልታሰቡ አትችሉም። የምታሰቡት በአዕምሮአችሁ ነው። እጅግ ብዙ ክርሰቲያኖች፡ የሚያቆሙትም፡ እዚያ ጋ ነው። እነርሱም፡ ልክ በእርሻ ውሰጥ እንዳለው በቆሎና በእርሻ ውሰጥ እንዳለው አረም፡ እውነተኛው አማኝ በተቀባበት በዚያው መንፈስ ቅዱስ ሊቀቡ ይችላሉ።

ዳሩ ግን ከዚያ በታች በውሰጥ በኩል፡ ቀጣዩ ዓለም፡ ሦሰተኛው ዓለም፡ ነፍስ ነው፥ ያም በእግዚአብሔር አሰቀድሞ የተወሰነ ነው። የዘሩ እውነተኛ የሕይወት-ዘር ያለው፡ እዚያ ውሰጥ ነው።

26 እናም፡ አሰታውሱ፡ አንድ የሾህ አረም ወሰጄ ብከፍተው፡ በውሰጡም የ—የሰንዴን ሕይወት ብቀጥልበት፡ እና እዚያ ብቀብረው፡ ከሾሁ አረም ውሰጥ ሰንዴን ያወጣል፡ ውጫዊው ነገር ምንም ቢሆን፡ ሰሜቶቹም ምንም ቢሆኑ ለውጥ አያመጣም።

27 ዛሬ፡ ሰለ መንፈስ ቅዱስ ማረጋገጫና፡ በመሳሰሉት ነገሮች ላይ እጅግ ብዙ መደናገር አለ። ሰይጣን እግዚአብሔር ያለውን ማንኛውንም ዓይነት ሰጦታ ሊያሰመሰል ይችላል፡ ዳሩ ግን ያንን ቃል፡ ቃል በቃል ሊያመጣ አይችልም። በኤደን ገነት የወደቀው እዚያ ላይ ነው፡ ሁልጊዜም የሚወድቀው እዚያ ላይ ነው። እነዚያ፡ **በሐሰት የተቀቡ...** ፡ ወይም፡ **የተቀቡት...** በተሰኘው ቴፕ

ላይ እንደተነገረው፡ በመንፈስ ሊቀቡ፡ በልሳናት ሊናገሩ፡ ሊጨፍሩ፡ ሊጮኹ፡ ወንጌልን ሊሰብኩ ይችላሉ፡ ዳሩ ግን አሁንም ዲያብሎስ ሊሆኑ ይችላሉ።

ዋናው የውስጡ ማንነት ነው! አሁን አስታውሱ፡ ኢየሱስ፡ "አብ የሰጠኝ ሁሉ ወደ እኔ ይመጣል። አባቴ አስቀድሞ ካልሳበው በቀር ማንም ወደ እኔ ሊመጣ አይችልም" ብሏል።

አሁን፡ በትምህርቱ ውስጥ እንዳየነው፡ ይህንን ለማሳየት... በሰጋዊ አነጋገር፡ ሙሉ በሙሉ ወደ ኋላ ስንመለስ፡ በቅድመ-ቅድመ-ቅድመ-አያታችሁ ውስጥ እንደነበራችሁ አይተናል። ከዚያም፡ በሰጋ ማንነታችሁ፡ በተፈጥሮ እንደዚያ ናችሁ። አንዳንዴ በአንድ ቤተሰብ ውስጥ፡ ቀይ-ፀጉር ያለው ልጅ ይወለዳል። ይህ አባትን ያስገርመዋል፡ ምክንያቱም ከእርሱ ቤተሰብም ሆነ፡ ከእናትየው ቤተሰብ፡ ቀይ-ፀጉር ያለው፡ ማንም እንደሌለ ስለሚያውቅ ነው። ነገር ግን ወደ ኋላ ብዙ ትውልዶች ብትመለሱ፡ አንድ ቀይ-ፀጉር የነበረው ሰው እንደነበር ታገኛላችሁ። ያ ዘር ወደ ታች መውረዱን ይቀጥላል፡ እናንተም ከሩቅ ዘመን የመጣ የአንዱን ተፈጥሮ ይዛችሁ ትመጣላችሁ።

ልክ ዕብራውያን 7ኛ ምዕራፍ እንዳለው፡ ማለትም፡ "መልከ ጼዴቅ፡ አብርሃም ነገሥታትን ገድሎ ሲመለስ፡ አሥራትን ለእርሱ ከፈለ። አሥራትን የሚቀበለው፡ ሌዊም ቢሆን፡ አሥራትን ከፈለ፡" ምክንያቱም መልከ ጼዴቅን በመ... ወይም፡ ይልቁንም፡ መልከ ጼዴቅን ባገኘው ጊዜ፡ "በአብርሃም አብራክ" ውስጥ ነበረና።

28 አሁን ይኸው ተመሳሳይ ነገር ነው። እናንተ የእግዚአብሔር ልጅ ከሆናችሁ፡ እንዲሁም እኔ የእግዚአብሔር ልጅ ከሆንኩ፡ ወይም የእግዚአብሔር ሴት ልጅ ከሆናችሁ፡ በመጀመሪያ በእግዚአብሔር ውስጥ ነበርን። ኢየሱስ የቃሉ ሙላት በሆነ ጊዜ፡ በዚያን ጊዜ በዘር መልክ፡ በእርሱ ውስጥ ነበርን። እርሱ በተሰቀለ ጊዜ፡ በእርሱ አካል ውስጥ ሆነን ተሰቅለን ነበር። ከሙታን ሲነሳ፡ ከእርሱ ጋር ተነስተናል። አሁን ደግሞ፡ ያንን ስላስተዋልን፡ "አሁን በክርስቶስ ኢየሱስ፡ በሰማያዊ ስፍራ ከእርሱ ጋር በአንድነት ተቀምጠናል።" አያችሁ? ምክንያቱም እርሱ... እኛ፡ የእግዚአብሔር ወንዶችና ሴቶች ልጆች ከሆንን፡ የእግዚአብሔር ልጆች ከሆንን፡ ያኔ የእግዚአብሔር ባህርያት ነን። ከዚያም እኛ... የዘላለም ሕይወት አለን። ያለው ብቸኛ የዘላለም ሕይወት ደግሞ እግዚአብሔር ነው። ያኔ፡ ከመጀመሪያው በእርሱ ውስጥ ነበርን። ኢየሱስ ያ ቃል ሁሉ በሆነ ጊዜ፡ ያኔ እኛ የእርሱ አካል ነበርን። አሜን! ይኸውና። በዚያ ውስጥ አለ፡ ምንም ዲያብሎስ፡ ምንም ኃይላት፡ ምንም ነገር መቼም ሊያናውጠው አይችልም። የነፍስ ቱምቢ ያ ነው።

29 **እዚህ** ውጪ፡ በዚህ መንፈስ ልትቀቡ፡ ልትመኙ፡ እንዲሁም እነዚህን ሌሎች ነገሮች ሁሉ ልታደርጉ ትችላላችሁ። ነገር ግን ከቃሉ ጋር ወዳለው ወደዚህ ማስሪያ ምሰሶ ሲመጣ ግን፡ ከዚያ ፈጽሞ አትናወጡም። ወደዚያ ቃል፡ በተቻለው መጠን፡ እጅግ ጸንቶና እውነተኛ ሆኖ ይይዛል። ከዚያ ውጪ፡ የምታደርጉት ምንም ቢሆን፡ አሁንም ጠፍታችኋል።

30 ያ የሎዶቅያ ቤተክርስቲያን ዘመን፡ "ዕውር፡ ጐስቋላና፡ ራቁትዋን ሆና፥ ይህንንም እንኳ አታውቅም።" አያችሁ፡ ከውጪ... የተቀባ ነው፥ በእውነተኛው መንፈስ የተቀባ ነው። አያችሁ፡ ያ መንፈስ ቅዱስ በሰው ላይ፡ በመንፈሱ

ላይ ሊወርድ ይችላል። ነፍሱ ግን የእርሱ የሕይወት ዘር ናት፥ ያቺ ዘር ቃሉ ናት። አያችሁ? ታዲያ እንዴት... ምንም ያህል መሰበክ ብትችሉ፡ **ይህንን** ምን ያህል በሚገባ ብታደርጉ፡ ምንም ያህል ብትወዱ ለእኔ ለውጥ አያመጣም፥ ያ ወደ መንፈስ መግቢያ መንገዶች አንዱ ነው። በሰውነታችሁ ልትወዱ አትችሉም፥ የምትወዱት በመንፈሳችሁ ነው። መግቢያዎቹ አንዱ ያ ነው። መውደድ ትችላላችሁ፡ እግዚአብሔርን እንኳን ልትወዱ ትችላላችሁ፡ ዳሩ ግን አሁንም ትክክል ላትሆኑ ትችላላችሁ። አጋንንትን ልታወጡ፡ ልትሰብኩ፡ እንዲሁም እነዚህን ነገሮች ልታደርጉ ትችላላችሁ፡ አሁንም ግን ትክክል ላትሆኑ ትችላላችሁ። ኢየሱስ እንዲህ ብሏል፡ በዚያ ቀን ብዙዎች ይመጣሉ ብሏል። ያ ቃል እልባት ይሰጠዋል!

**በመጀመሪያ ቃል ነበረ፡ ቃልም በእግዚአብሔር ዘንድ ነበረ፡ ቃልም እግዚአብሔር ነበረ።**

**ቃልም ሥጋ ሆነ፡ በእኛም አደረ፡...**

31 አስተውሉ፡ **ክርስቶስ በገዛ ቃሉ ተገልጧል፡** በሚለው፡ በዚህ የመጽሐፍ ቅዱስ ርዕስ ላይ ልናገር ነው። ወደዚህ መደምደሚያ የመጣሁት፡ በክፍሌ ውስጥ ሳለሁ ነው።

አንድ ውድ ሰው፡ ምናልባት ዛሬ ጠዋት እዚህ ተቀምጦ ሊሆን ይችላል... እዚያ በጥናት ክፍሌ ውስጥ የተሰቀለ ሰዕል አለኝ፡ እርሱም በብፁዓን ትምህርት የተሳለ፡ የሆፍማን **የክርስቶስ ራስ** ሰዕል ነው። የጸጉሩ ክፍል ወደሚያስፈልገበት ሰፍራ ሰትደርሱ፡ ያንን ክፍል በሚያልፉበት ጊዜ በብዕሩ ላይ ትንሽ ጠበቅ አድርገው ጽፈውታል። እዚያ፡ እነሆ እርሱ፡ በቃሉ ውስጥ ሆኖ፡ ቀጥታ ወደ ውጪ ይመለከታል፥ ክርስቶስ በብፁዓን ትምህርት ውስጥ። ማንም ትሁን ማን፡ የሰጠኸኝ ሰው፡ ሰለዚህ ነገር አመሰግንሃለሁ።

እንዲሁም ሌላ ሰው ደግሞ ኤልያሰ በእሳት ሰረገላ ወደ ላይ ሲወጣ የሚያሳየውን ያንን ሰዕል፡ አምጥቶ እዚያ በጥናት ክፍሌ ውስጥ አሰቀምጦታል። እነዚህን ነገሮች እናደንቃለን። ብዙ ጊዜ፡ በታላላቅ ሰብሰባዎች ውስጥ፡ ተነሰቼ እነዚህን ነገሮች ለመናገር ዕድል አላገኝም፡ ዳሩ ግን ወንድሜ፡ እህቴ፡ አየዋለሁ። አ—አውቀዋለሁ፡ እግዚአብሔርም ያውቀዋል።

32 አሁን ልናገርበት ያሰብኩት ርዕሰ፥ **ክርስቶስ በገዛ ቃሉ ተገልጧል** በሚለው ላይ ነው። በብፁዓን ትምህርት ውስጥ፡ የክርስቶሰ ምሰል፡ እንዴት፡ በቀጥታ ጎልቶ፡ እንደሚታይ አይቻለሁ። ይህንን ርዕሰ ያሰብኩትም ከዚሁ ተነሰቼ ነው። አሁን፡ ክርሰቶሰና ቃሉ አንድ ናቸው። አያችሁ?

33 እንዲህ ይላሉ፡ "እንዴት ነው መጽሐፍ ቅዱሰ... ? " ሰዎች እንደዚያ ይላሉ። በቅርብ ጊዜ ከአንድ ሰው ጋር በመኪና እየተጓዝኩ ነበር። እርሱም፡ "እሰቲ አሰበው። እኛ እዚህ ምድር ላይ፡ በዚህ ሁኔታ ላይ ሆነን ሳለ፡ እንደዳንን የምናውቀው ወይም መናገር የምንችለው መጽሐፍ ቅዱሰ በሚባል በአንድ የአይሁድ ተረት ብቻ ነው" አለኝ።

34 እኔም፡ "ወዳጄ፡ እንዴት እንዲህ እንደምትል አላውቅም፡ ነገር ግን የአይሁድ ተረት ነው ብዬ አላምንም፡" አልኩት።

እርሱም፡ “መልካም፡ ትጸልያለህ፡ ለማን ነው የምትጸልየው? **ይህን-እና-ያንን** አንዳንድ ነገሮችን ጠየቅሁ፥ ነገር ግን አልገባኝም” አለ።

35 እኔም፡ “የምትጸልየው በተሳሳተ መንገድ ነው። መቼም ቢሆን የእግዚአብሔርን ሀሳብ ለመለወጥ መጸለይ የለብንም፥ የራሳችንን ሀሳብ እንዲለውጥልን ነው መጸለይ ያለብን። የእግዚአብሔር ሀሳብ ምንም መለወጥ አያስፈልገውም። አየህ? አየህ፡ ልክ ነው” አልኩት። እንዲህም አልኩት፡ “ስለጸለይክለት ነገር ሳይሆን... ”

በአንድ ወቅት፡ አንድ ወጣት የካቶሊክ ልጅ አውቅ ነበር፡ የጸሎት መጽሐፍ ይዞ፡ እናቱ በሕይወት እንድትኖር፡ ይጸልይ ነበር። ሆኖም ሞተች፡ እርሱም የጸሎት መጽሐፉን እሳት ውስጥ ወረወረው። ደህና፡ እያችሁ፡ የጸሎት መጽሐፍ አልደገፍም፥ ነገር ግን፡ ያም ሆነ ይህ፡ እያችሁ፡ የተሳሳተ አመለካከት ነው የምትይዙት። እግዚአብሔር ምን ማድረግ እንዳለበት ልትነግሩት እየሞከራችሁ ነው።

ጸሎት እንዲህ ሊሆን ይገባል፡ “ጌታ ሆይ፡ ከቃልህ ጋር እንድገጠም ለውጠኝ።” እንጂ፡ “ለውጥ፡” “የአንተን ሀሳብ ልቀይር። አንተ የእኔን ሀሳብ ቀይረው፡” አይባልም። እያችሁ? “ሀሳቤን ወደ ፈቃድህ ለውጠው። ፈቃድህ ደግሞ እዚህ መጽሐፉ ውስጥ ተጽፏል። እናም፡ ጌታ ሆይ፡ ሀ—ሀሳቤ ልክ እንደ ሀሳብህ እስኪሆንልኝ ድረስ አ—አትተወኝ። ከዚያም ሀሳቤ እንደ ሀሳብህ ሲሆንልኝ፡ ያኔ የጻፍከውን እያንዳንዱን ቃል አምናለሁ። በዚያም ውስጥ፡ ለሚወዱህ ሰዎች ‘ነገር ሁሉ ለበጎ እንዲሆን፡’ እንደምታደርግ ተናግረሃል። ጌታ ሆይ፡ እወድሃለሁ። ሁሉም ነገር ለበጎ እየሆነ ነው።”

36 በዚህ ሳምንት ገጠር ውስጥ፡ ከእጅግ ውድ ጓደኞቼ ጋር ነበርኩ። ትላንትና፡ እየበላን ሳለ፡ በማዕድ ዙሪያ አንዳንዶቹን ጠየቅኋቸው። ሁልጊዜም በአንድ ላይ ተቀምጠን በመጽሐፍ ቅዱስ ላይ አነስተኛ... ልክ እንደ አነስተኛ ጥናት እናደርጋለን። ስለ ፍቅር እያወራን ነበር።

አንድ ሰውም እንዲህ አለኝ፡ “አንተ የክርስቶስ ተቃዋሚ እንደሆንክ አምናለሁ፡” አለ።

37 እኔም፡ “ያ ጌታዬን ደስ የሚያሰኘው ከሆነ፡ መሆን የምፈልገው ያንን ነው። እርሱ እንድሆን የሚፈልገውን ማንኛውንም ነገር መሆን እፈልጋለሁ። እወደዋለሁ። ወደ ገሃነም እንኳን ቢጥለኝ፡ አሁን ባለኝ መንፈስ እስከሄድኩ ድረስ፡ አሁንም እወደዋለሁ” አልኩት። በተለየ ሁኔታ ተመለከተኝ።

በዚያ አራት ወይም አምስት የሚሆኑ፡ ወጣቶችን አየሁ፥ ወጣት ሚስቶች፡ መልካም ሴቶች ነበሩ። እነዚያ ወጣቶች ሚስቶቻቸውን እንዴት እንደሚወዱ አውቅ ነበር፡ ስለዚህም፡ እንዲህ አልኳቸው፡ “ነገሩን የምንፈትሽበት መንገድ ይኸውላችሁ። ሚስት፡ ከማግባታችሁ በፊት... አሁን፡ ወደ ኋላ ተመልሳችሁ፡ እንበልና... በዚህ የትዳር ሕይወት፡ እንዳገባችሁ በህልም እያያችሁ ነበር እንበል፥ በእርግጥ አላገባችሁም፡ ዳሩ ግን እንዳገባችሁ በህልማችሁ እያችሁ። ከእንቅልፋችሁ ነቅታችሁ፡ ከሴት ጓደኛችሁ ጋር ለመወያየት ሄዳችሁ፡ እንዲህ አላችኋት፡ ‘ታውቂያለሽ፡ ሰናገባና፡ ልጆች ስንወልድ በህልሜ አየሁ። በደስታ እየኖርን፡ የ—የጌታን መምጣትና፡ ሁሉንም ነገር ስንጠባበቅ አየሁ።’ ከዚያም ይህቺ ልጅ እንዲህ ብትላችሁ፡ ‘ታውቃለህ፡ ከአንተ ይልቅ ሌላ ሰው እወዳለሁ።

ከሌላው ሰው ጋር ብሆን ይበልጥ ደስተኛ መሆን እችላለሁ።’ ይህ ቢሆን ኖሮ፡ በፍጹም ልባችሁ፡ እንዲህ፡ ‘የእግዚአብሔር በረከት በአንቺ ላይ ይሁን፡ የኔ ውድ። ከዚህኛው ሰው ጋር ሂጂ’ ለማለት እስከምትችሉ ድረስ ልትወዷት ትችላላችሁን? ”

አሁን፡ አሁን እያንዳንዳችሁ ወንዶች ወይም ሴቶች፡ ይህንን መርምሩ። አያችሁ? መልካም፡ ፍቅራችሁ ትክክለኛ ከሆነ፡ ያንን ታደርጋላችሁ፡ ምክንያቱም ደህንነቷ ያሳሰባችኋልና። እንዴ፡ የራሳችሁ ልታደርጓት እንደምትችሉ፡ አብራችኋት ልትኖሩ እንደምትችሉ ታውቃላችሁ፡ እናንተ... ሚስታችሁ ናት፥ ትሆናለችም። ታገባችኋለች፡ ዳሩ ግን ደስተኛ አትሆንም። ይበልጥ ደስተኛ የምትሆነው... እንግዲያውስ፡ የምትወዷት ከሆነ፡ ደስተኛ እንድትሆን ትፈልጋላችሁ።

ስለዚህ፡ የትኛውም ቢሆን የእግዚአብሔር ፈቃድ ይሁን፡ በእርሱ ደስተኛ ብሆንም ባልሆንም፡ የእግዚአብሔር ፈቃድ ይፈጸም። እኔ መኖር የምፈልገው በማደርገው ነገር እርሱን ደስ ለማሰኘት ነው። ስለዚህ ዓላማችሁንና የ— የልብ ሀሳባችሁን በዚህ መርምሩ፥ እግዚአብሔርን እንደምትወዱ ወይም እንደማትወዱ ታውቃላችሁ።

እርሱ፡ “ወደ ውጪ ብጥልህም ታገለግለኛለህን” ቢላችሁስ?

“ያም ሆኖ፡ እወድሃለሁ።”

38 ስለዚህ፡ አብያተ ክርስቲያናት ያንን አይተው በዚያ መንገድ ማመን ቢችሉ ኖሮ፡ አንዱ ኳሱን ይዞ ሲሮጥ ሌላው ነጥቆት ለመውሰድ አይሞክርም ነበር። ይልቁንም ያኛውን ይጠብቀው ይከላከልለት ነበር። አያችሁ? እውነተኛና ትክክለኛ የልብ ሀሳብና፡ ዓላማ ሲኖር፡ አንዱ፡ “ሄይ፡ እኔም **ይህ** አለኝ! እኔ፡ **ይህ** እኔ ነኝ፡ **ይህ**” ለማለት አይሞክርም። አያችሁ፡ እግዚአብሔር ሰውን ሊጠቀምበት አይችልም። እጅግ ብዙ ማስመሰል ይከተለዋል፡ ያም ሰይጣን ነው። ሰዎቹም ይህንን ሊገነዘቡ አይችሉም። ኳሱን ከተሰጠው ሰው ላይ ለመውሰድ ይሞክራሉ። እግዚአብሔር አንድ አገልግሎት ያስነሳና ሰንቱ ከእርሱ በኋላ እንደሚከተል ተመልከቱ። አያችሁ? አያችሁ?

39 አሁን፡ ለእግዚአብሔር ያለው እውነተኛ ፍቅር፡ “ጌታ ሆይ፡ ምንም ዓይነት የሥራ ድርሻ ቢኖረኝ ለውጥ አያመጣም፡ አንዲት ቃል እንኳ ስለ እርሱ መናገር ከቻልኩ፡ እርሱን ለመጠበቅ ከረዳሁ፡ ያንን ላድርግ” የሚል ነው። አያችሁ?

በሚስታችሁም ጉዳይ ላይ የሚሆነው ይኸው ተመሳሳይ ነገር ነው። በእውነት የምትወዷት ከሆነ፡ አያችሁ፡ እ—እርሱ የ—የ**ፊልዮ** ፍቅር አይደለም፥ የ**አጋፓዎ** ፍቅር ነው፡ እውነተኛ ፍቅር። ከሌላ ሰው ጋር፡ በደስታ ልትኖር ትችላለች፥ እናንተ አሁን አላገባችኋትም፡ ስለዚህ፡ የራሳችሁ ማድረግ አትችሉም።

40 በነገራችን ላይ፡ እነዚህን ቴፖች የሚያዳምጡ ሰዎች፡ አንዳንዶቹ፡ እጅግ ብዙዎቹ፡ መልዕክት ሲልኩ፡ “ለምንድነው፡ **በጋብቻና ፍቺ** ትምህርት ላይ፡ **ይህንን** አልክ **ያንን** አልክ፡” ይላሉ። ያንን ብዙ ጊዜ ተናግሬዋለሁ፥ እነዚህ ቴፖች የሚሄዱት... እኔ እየተናገርኩ ያለሁት ለጉባኤዬ ነው፡ ወንድሜ። እግዚአብሔር እንድትጠብቅ ለሰጠህ መንጋ እኔ ተጠያቂ አይደለሁም፥ እኔ ተጠያቂ የምሆነው ለእነዚህ ሰዎች በምመግባቸው የምግብ ዓይነት ላይ ነው።

ይህ ለዚህ ተብርናክል ብቻ የተነገረ ነው። አያችሁ? አሁን፡ ሰዎች ቴፖቹን መስማት ከፈለጉ፡ ያ የራሳቸው ምርጫ ነው። ነገር ግን እኔ እየተናገርኩ ያለሁት እግዚአብሔር ለሰጠኝ ነው። የተሰረዘው የእነርሱ ኃጢአት ነበረ።

አንድ ሰው ጽፎልኝ፡ እንዲህ አለኝ፡ “መልካም፡ እኔ **ይህንን** አድርጌያለሁ ***ያንንም*** አድርጌያለሁ። አንተ ኃጢአታችን... ” እ—እኔ እንደዚያ አላልኩም።

“ይህንን አስተውሉ፡ ይህ የተነገረው እዚሁ ላሉት ሰዎች ብቻ ነው፡ እዚህ ማደሪያው ድንኳን ውስጥ ላሉት ሰዎች፡ ለእኔ መንጋ ብቻ ነው፡” ነበር ያልኩት። አሁን፡ በውጪ ያሉት ሰዎች ምግብንና ነገሮችን ማዳቀል ከፈለጉ፡ እ—እናንተ ከእግዚአብሔር መገለጥን ተቀበሉና እግዚአብሔር እንድታደርጉ የሚነግራችሁን አድርጉ። እኔም ያንኑ ነገር አደርጋለሁ። ነገር ግን እነዚህ መልእክቶች ለዚህች ቤተክርስቲያን የተነገሩ ናቸው።

41 አሁን አስተውሉ፡ ተመልሰን ስንመጣ፡ አጥብቀን የምንይዘው ሌላ አንዳች ነገር ሊኖረን ይገባል። አንዳች ቱምቢ የሆነ ነገር ሊኖር ይገባል፡ በሌላ አባባል፡ መቋጫ መኖር አለበት። እያንዳንዱም ሰው መቋጫው ወይም ፍጹሙ ሊኖረው ይገባል። ከዓመታት በፊት፡ በአንድ ወቅት፡ የመጨረሻው ቃል ስለሆነው፡ ስለ ፍጹሙ ሰብኬ ነበር።

42 ልክ በኳስ ጨዋታ ላይ እንዳለ ዳኛ፡ እርሱ ስትራይክ ነው ካለ፡ ነገሩ በትክክል ያው ነው። በምንም ዓይነት መንገድ ብታዩት፡ ዳኛው ስትራይክ ነው ብሏል። እናንተም እንዲህ ትላላችሁ፡ “እ—እ—እ... ስትራይክ አልነበረም። የሄደው... እኔኮ አይቻለሁ... ” ምንም ቢሆን፡ እርሱ፡ “ስትራይክ” ካለ፡ አበቃ፡ ይህም ነገሩ ምን እንደሆነ እልባት ይሰጠዋል። እርሱ፡ የመጨረሻው ነው።

43 የትራፊክ መብራትም የመጨረሻ ውሳኔ ሰጪ ነው፡ “ሂድ” ካለ፡ ሂድ ነው። እናንተም እንዲህ ትሉ ይሆናል፡ “መልካም፡ እኔ፡ ቸኩያለሁ፡ እኔ... ” አይ፡ አይ። “ሌላው ሰው ሲሄድ አንተ ቆመህ ጠብቅ፡” ይላል። አያችሁ? እሱ የመጨረሻው ነው።

44 አሁን፡ በምታደርጉት ነገር ሁሉ ዋናችሁ ሊኖር ይገባል። ሚስታችሁን ስትመርጡ ዋናችሁ ሊኖራችሁ ይገባ ነበር። ልትመርጧት የሚገባ አንዲት ሴት መኖር ነበረባት።

45 አሁን፡ መኪና ልትገዙ ስትሉ፡ ምን ዓይነት የመጨረሻ ውሳኔ ላይ እንደምትደርሱ፡ የምትወስኑበት ጊዜ ሊኖር ይገባል። ፎርድ፡ ቼቪ፡ ፕሊማውዝ፡ ወይስ የውጭ ሀገር መኪና ይሆናል? ምንም ይሁን ምን፡ የመጨረሻ ውሳኔ ሊኖራችሁ ይገባል።

በክርስቲያናዊ አኗኗርም ነገሩ ልክ እንደዚሁ ነው። የመጨረሻ ውሳኔ ሰጪ ሊኖር ይገባል።

46 አሁን፡ አንድ ሰው ወደ ሌላ ሰው ሄዶ... አንድ ሰው፡ “መልካም፡ መጠመቅ አለብህ” ሲል ቢሰማ፡ ይህ ሰው ደግሞ በጭራሽ... ምናልባት፡ የእርሱ፡ የማታጠምቅ ቤተክርስቲያን ብትሆን፡ ዝም ብለው የሚረጩ ሊሆኑ ይችላሉ። ለምሳሌ ያህል፡ ሜቶዲስቶችን፡ ብንወስድ፡ እንደተረዳሁት ከሆነ፡ ከተጠየቁ ያጠምቃሉ። ወይም ምናልባት የ... ካቶሊኮች፡ የሚረጩት ብቻ ይመስለኛል። ስለዚህ እ—አንድ ሰው “በውሃ ውስጥ ስለመጠመቅ” አንዳች ነገር ቢሰማ፡

መልካም፡ ይህንን አይረዳውም፡ ያደገው በካቶሊክ እምነት ነውና። ስለዚህ ወደ ቄሱ ይሄድና፡ እንድህ ይለዋል፡ “አባባ፡ መጠመቅ ያሊብን በውሃ ውስጥ በመጥለቅ እንደሆነ ተረድቻለሁ። ቤተክርስቲያናችን ስለዚህ ጉዳይ ምን ትላለች” ይለዋል?

47 “እንዴ፡ ቤተክርስቲያኒቱ የ—የምንረጭ መሆናችንን ትናገራለች።” ያቺ ቤተክርስቲያን ለእርሱ የመጨረሻ ውሳኔ ሰጪ ከሆነች፡ ያ እልባት ይሰጠዋል። ሙግቱ ሁሉ አብቅቷል፥ ቤተክርስቲያኒቱ እንዲህ ብላለች፡ ያ ነው በቃ።

48 እንዲህ ቢሆን... የባፕቲስት ወንድም “በውሃ ውስጥ በመጥለቅ” መጠመቅን እንደምናምን ስንናገር ቢሰማስ? እርሱም፡ “ያንን አምናለሁ” ይላል።

“‘በኢየሱስ ክርስቶስ’ ስምም መሆኑን ጭምር።”

አሁን፡ ይ—ይህ የቤተክርስቲያኒቱ አባል ወደ ፓስተሩ ይመለስና፡ “ፓስተር፡ መጠመቅ ያሊብን በውሃ ውስጥ በመጥለቅ እንደሆነ አንድ ሰው ሲነግረኝ ሰማሁ፡ ያማ ልክ ነው፡ ነገር ግን ‘በኢየሱስ ክርስቶስ’ ስም መሆን እንዳለበት ተናገረ” ይለዋል።

49 “መልካም፡” እርሱም፡ “አሁን፡ እስቲ እንመልከት። ታዲያ፡ እዚህ መጽሐፉ የምንጠመቀው ‘በአብ፡ በወልድ፡ በመንፈስ ቅዱስ’ ስም እንደሆነ ይናገራል” ይለዋል። ያቺ ቤተክርስቲያን የመጨረሻ ውሳኔ ሰጪ ከሆነች፡ ያ እልባት ይሰጠዋል። ሌላው ነገር ምንም ቢል ግድ አይሰጠውም፥ የመጨረሻ ውሳኔው ያ ነው።

50 እንግዲህ፡ እያንዳንዱ የሐይማኖት ተቋም ለአማኞቹ የመጨረሻ ውሳኔ ሰጪ ነው።

ነገር ግን፡ ለእኔ፡ እንዲሁም ወደ ክርስቶስ፡ በክርስቶስም እየመራኋቸው ነው ብዬ ተስፋ ለማደርጋቸው ሰዎች፡ መጽሐፍ ቅዱስ የመጨረሻ ውሳኔ ሰጪያችን ነው። ምንም ቢሆን... ምክንያቱም እግዚአብሔር፡ “የሰው ሁሉ ቃል ውሸት፡ የእኔ ግን እውነት ይሁን፡” ብሏልና። እኔም መጽሐፍ ቅዱስ የእግዚአብሔር የመጨረሻ ውሳኔ ሰጪ እንደሆነ አምናለሁ። ሌላ ማንም ምንም ቢል ለውጥ አያመጣም፥ እርሱ የመጨረሻ ውሳኔ ሰጪ ነው።

መጽሐፍ ቅዱስ የመዋቅሮች መጽሐፍ አይደለም። አይ፡ ወዳጄ። የመዋቅሮች መጽሐፍ፡ ወይም የሰነ ምግባር ደንብ አይደለም። መጽሐፍ ቅዱስ የመዋቅሮች መጽሐፍ አይደለም፡ እጅግ ብዙ መዋቅሮችና፡ የመሳሰሉት የሉበትም። በፍጹም፡ ጌታዬ። የሰነ ምግባር መጽሐፍ አይደለም። በፍጹም፡ ጌታዬ። አይደለም። ወይም ደግሞ ሙሉ በሙሉ፡ የታሪክ መጽሐፍም አይደለም። ወይም፡ የሥነ መለኮት መጽሐፍም አይደለም። ምክንያቱም፡ የኢየሱስ ክርስቶስ መገለጥ ነውና።

አሁን ይህንን ማንበብ የምትፈልጉ፡ ወረቀታችሁን ይዛችሁ፡ የምትጽፉ ሰዎች፡ በራእይ 1፥1 እስከ 3 ላይ እንዳለው፡ መጽሐፍ ቅዱስ “የኢየሱስ ክርስቶስ መገለጥ፡” ነው።

51 እስቲ ጊዜ እያለን እናንብበው። የእኔ... እዚህ ለመናገር ያዘጋጀኋቸው ብዙ ማስታወሻዎች የሉኝም። ጌታ ቢዘገይ፡ እንግዲህ፡ ከእነርሱ ውስጥ ለመናገር እንሞክራለን።

> **ቶሎ ይሆን ዘንድ የሚገባው ነገር፡ ለባሪያዎቹ** ያሳይ ዘንድ **እግዚአብሔር** ለእርሱ **የሰጠው በእርሱም የተገለጠው፡ ኢየሱስ ክርስቶስ መገለጥ ይህ ነው፥ ኢየሱስም በመልአኩ ልኮ** ለባሪያው **ለዮሐንስ** አመለከተ፥
>
> **እርሱም ለእግዚአብሔር ቃልና፡ ለኢየሱስ... ክርስቶስ ምስክር፡ ላየውም ሁሉ መሰከረ።**
>
> **ዘመኑ ቀርቦአልና የሚያነበው፡** የ**ትንቢቱን** ቃል **የሚሰሙትና፡ በውስጡ** የ**ተጻፈውን፥ የሚጠብቁት ብፁዓን ናቸው።**

52 ስለዚህ፡ መጽሐፍ ቅዱስ የኢየሱስ ክርስቶስ ሙሉ መገለጥ ነው። የተጻፈውም በነቢያት ነው። ዕብራውያን 1፥1 ላይ፡ በ... "ከጥንት ጀምሮ እግዚአብሔር፡ በብዙ ዓይነት መንገድ ለአባቶቻችን በነቢያት ተናግሮ፡ በዚህ በመጨረሻው ዘመን፡ በልጁ በኢየሱስ ክርስቶስ ተናገረን" ይላል፡ ነቢያት ሁሉ፡ በአንድ ላይ ተደምረው፡ እርሱን ነው። ኢየሱስ ሚልክያስ ነበረ፥ ኢየሱስ ኤርምያስ፡ ኢሳይያስ፡ ኤልያስ ነበረ። እነርሱ የነበሩት ሁሉ፡ በእርሱ ውስጥ ነበረ። እናንተም የሆናችሁት ሁሉ፡ እኔም የሆንኩት ሁሉ፡ በእርሱ ውስጥ ነው፥ የቃሉ ምስክሮች፡ ቃሎች ነን።

ስለዚህ የመዋቅሮች መጽሐፍ፡ የሰነ ምግባር ደንብ፡ እንዲሁም የታሪክ፡ ወይም የሥነ መለኮት መጽሐፍ አይደለም። በፍጹም አይደለም። ነገር ግን የኢየሱስ ክርስቶስ መገለጥ ነው፡ እግዚአብሔር ራሱ፡ ከቃል ወደ ሥጋ የተገለጠበት ነው። ይህ ነው እሱ። መጽሐፍ ቅዱስ ቃሉ ነው፡ እግዚአብሔር ደግሞ ሥጋው ነው፡ እግዚአብሔር በ... ማለቴ፡ እግዚአብሔር ቃሉ ነው፡ ኢየሱስ ደግሞ ሥጋው ነው። እግዚአብሔር (ቃሉ) በሰው ሥጋ፡ እንዴት እንደተገለጠና ለእኛም እንደታየ የሚያሳይ፡ መገለጥ ነው። የእግዚአብሔር ልጅ የሆነውም ለዚህ ነው፥ እርሱ የእግዚአብሔር አካል ነው። ገብቷችኋል? አሁን፡ እሱ ሳይሆን... ሥጋው የእግዚአብሔር አካል በመሆኑ፡ የተነሳ ልጅ ነው።

53 ልጅ፡ ካቶሊኮችና፡ የቀሩት አብያተ ክርስቲያናት ሁሉ እንደሚሉት፥ "ዘላለማዊ ልጅ" ቃሉ ራሱ ምንም ትርጉም አይሰጥም። አያችሁ? ዘላለማዊ ሆኖ ሳለ፡ ልጅ ሊሆን አይችልም፡ ምክንያቱም **ልጅ** ማለት የሆነ "የሚወለድ" ነገር ነውና። ዘላለማዊ የሚለው ቃል፡ እርሱ ዘላለ-... ልጅ ሊሆን ይችላል፡ ዳሩ ግን ዘላለማዊ ልጅ ሊሆን አይችልም። አይ፡ ወዳጄ። ዘላለማዊ ልጅ ሊሆን አይችልም።

54 አሁን፡ እርሱ ግን በእርግጥም፡ ልጅ ነው፡ በኤርምያስ፡ በሙሴ ውስጥ የነበረው ቃል ሁሉ፡ እነዚያ ቃላት ሁሉ፡ እርሱ እንደተናገረው፡ "እነርሱ ስለ እኔ ይናገራሉ" እንዳለው ነው። ያ እውነተኛ መለኮታዊ የቃል መገለጥ ሁሉ በአንድ የሰው አካል ውስጥ ተጠቃሎ ነበር፡ እግዚአብሔርም በዙሪያው ሥጋን አለበሰው። "ልጅ" ተብሎ የተጠራበት ምክንያት ይኸው ነው፡ "አባት" ብሎ የሚጠራበትም፡ ምክንያት ይኸው ነው። እንዴት፡ እግዚአብሔር በአዕምሮአችሁ ውስጥ እንዲያፈሰው ከፈቀዳችሁ፡ ነገሩ እጅግ ቀላል ነው።

አያችሁ? እግዚአብሔር በሥጋ አካል ተገለጠ፡ አስተውሉ፡ ከሥጋ... ወይም ከቃል ወደ ሥጋ ተገለጠ። ዮሐንስ 1፥14 ያ ነው፡ "ቃልም ሥጋ ሆነ፡ በእኛም አደረ።"

55 አሁን ይህንን መጽሐፍ ቅዱስ አስተውሉ። አንዳንዶቹ፡ "ኦህ፡ መልካም፡ እንዲህ አድርጓል፡ እንዲያ አድርጓል" ይላሉ። ዳሩ ግን አንድ ነገር ልንገራችሁ፡ እስቲ ዝም ብለን...

ለአንድ ደቂቃ ያህል፡ ወደ መጽሐፍ ቅዱስ ታሪክ ገብተን፡ ከየት እንደመጣ እንመልከት። የተጻፈው በአርባ የተለያዩ ጸሐፍት ነው። አርባ ሰዎች መጽሐፍ ቅዱስን የጻፉት፡ በአሥራ ስድስት መቶ ዓመታት የጊዜ ልዩነት ውስጥ፡ በተለያዩ ጊዜያት ሆኖ፡ በዓለም ታሪክ ውስጥ የተከሰቱትን እጅግ ጠቃሚ ክስተቶች አስቀድመው ተንብየዋል፡ ይህም፡ ብዙ ጊዜ፡ ክስተቶቹ ከመፈጸማቸው በመቶዎች ከሚቆጠሩ ዓመታት በፊት ነበር። በጠቅላላው በሰልሳ-ስድስቱ መጻሕፍት ውስጥ አንዲትም ስህተት የለበትም። ኦህ፡ ማይ! ከእግዚአብሔር ራሱ በቀር ማንም ደራሲ እንዲህ ትክክለኛ ሊሆን አይችልም። አንዲትም ቃል ከሌላኛው ጋር አትጋጭም።

አስታውሱ፡ መጽሐፍ ቅዱስ የተጻፈው፡ በአሥራ ስድስት መቶ ዓመታት ልዩነት ውስጥ ነው፡ ከሙሴ ጀ—ጀምሮ በደሴቲቱ፡ ወይም በፍጥሞ ደሴት ዮሐንስ እ—እስከሞተበት ጊዜ ድረስ ነው። አሥራ ስድስት መቶ ዓመታት፡ የተጻፈውም በአርባ የተለያዩ ጸሐፍት ነው፥ አንዱ ሌላኛውን እንኳን አያውቅም ነበር፡ እንደ "ቃልም" አድርገው ይዘውት አያውቁም ነበር። ከእነርሱ አንዳንዶቹ "ቃሉን" አይተውት እንኳን አያውቁም። ነገር ግን በጻፉት ጊዜና፡ ነቢያት መሆናቸው በተረጋገጠ ጊዜ፡ ከዚያም፡ ትንቢቶቻቸውን በአንድ ላይ ሲያመጧቸው፡ እያንዳንዳቸው አንዱ ከሌላው ጋር በትክክል ይገጣጠም ነበር።

56 በጴንጤቆስጤ ዕለት፡ ጴጥሮስን ተመልከቱ፡ "ንስሐ ግቡ፡ ኃጢአታችሁም ይሰረይ ዘንድ እያንዳንዳችሁ፡ በኢየሱስ ክርስቶስ ስም ተጠመቁ" ብሎ ሲያውጅ ተመልከቱ።

ጳውሎስ ስለዚህ ጉዳይ ምንም የሰማው ነገር አልነበረም። ብሉይ ኪዳንን ለማጥናት፡ ለሦስት ዓመታት ወደ ዓረብ ሀገር ወረደ፡ "ሳውል፡ ስለ ምን ታሳድደኛለህ? " ብሎ ያነጋገረው፡ ይህ የእሳት ዓምድ ማን እንደሆነ ለማየት ወረደ፡ እንዴት ሊሳሳት ይችላል? ከቤተክርስቲያን ጋር ፈጽሞ አልተማከረም ነበር።

ከአሥራ አራት ዓመታት በኋላ፡ ጴጥሮስን ባገኘው ጊዜ፡ ያንኑ ነገር፡ ቃል በቃል ይሰብኩ ነበር። ያ መጽሐፍ ቅዱሳችን ነው። የሌሎች ሰዎች ቃል ይውደቅ። **ይህን**፡ ማንም ሊጨምርበት አይችልም። በመጽሐፍ ቅዱስ ላይ ከእንግዲህ ምንም አትጨምሩም። አይ፡ ወዳጄ። ይህ ሙሉ መገለጥ ነው። ያ ነው በቃ።

57 ልክ እንደ ሰባቱ ማኅተሞች ነው። "ሰባቱ ማኅተሞች፡" አንድ ሰው ደጋግሞ፡ "አሁን አንተ... ወንድም ብራንሃም፡ እነዚህ ማኅተሞች ሲገለጡ፡ ጌታ ይናገርሃል፡ እንዲሁም ወደ እግዚአብሔር ይበልጥ እንዴት መቅረብ እንዳለብንና፡ እንዴት ማድረግ እንዳለብን ይነግረናል" ይለኝ ነበር።

58 እኔም፡ “እይ፡ ወዳጄ፡ ይህ ሊሆን አይችልም። ምክንያቱም፡ በመጽሐፍ ቅዱስ ላይ ያሉት፡ ሰባቱ ማኅተሞች የተሰወሩትን ሰባት ምስጢራት ይዘው ነው። አስቀድሞ ተጽፎ ነበር፡ ነገር ግን ምን እንደሆነ አላስተዋሉትም ነበር” አልኩት።

በ “ኢየሱስ” ስም እየተጠመቁ፡ በዚያ ላይ እንዴት ሲታገሉ እንደነበር ተመልከቱ፥ አያችሁ፡ ነገሩ ያ አልነበረም። የ “ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ” ስም ነው! እነዚያን ነገሮች ሁሉ፡ እንዴት እንደነበሩ አያችሁ። ምክንያቱም፡ ብዙ ኢየሱስ የሚባሉ አሉ፥ እዚህ ምድር ላይ “ኢየሱስ” የሚባሉ፡ በርካታ አገልጋይ ጓደኞች አሉኝ። ነገሩ እርሱ አይደለም። የኛ “ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ” ነው።

ከእግዚአብሔር በቀር ማንም ደራሲ እንዲህ ትክክለኛ ሊሆን አይችልም። አሁን ይህ መጽሐፍ ቅዱስ እንዴት እንደተጻፈ እስቲ እንመልከት።

59 አሁን፡ ለምሳሌ ያህል፡ ከ... አሁን ሄደን በአርባ የተለያዩ የሕክምና ትምህርት ቤቶች የተጻፉ መቶ አስራ-ስድስት፡ ወይም በአሥራ ስድስት መቶ ዓመታት፡ የጊዜ ልዩነት... ውስጥ የተጻፉና ስለ ሰውነት የሚያጠኑ ሰልሳ ስድስት የሕክምና መጻሕፍትን ብንወስድ ምን የሚሆን ይመስላችኋል? ምን ዓይነት መጣጣም የምናገኝ ይመስላችኋል?

ከሁለት መቶ ዓመታት በፊት፡ ፕሬዝዳንታችን፡ ጆርጅ ዋሽንግተን፡ በሳንባ ምች፡ በታመመ ጊዜ፡ የእግር ጥፍሩን ነቅለው በማውጣት አንድ ፒንት ደም አፍሰሰውታል። ታዲያ ይህንን ብንወስድ ኖሮ...

60 ዛሬ እጅግ ወደምንማረክበት፡ ወደ ሌላ ነገር ትንሽ ጠለቅ ብለን እንሂድ፡ እርሱም ሳይንስ ነው። በአሥራ ስድስት መቶ ዓመታት የጊዜ ልዩነት ውስጥ ያሉ፡ አርባ የተለያዩ ሳይንሶችን ወሰደን፡ ምን ልናገኝ እንደምንችል ብንመለከት ምን የሚሆን ይመስላችኋል? ከሦስት መቶ ዓመታት በፊት፡ አንድ ፈረንሳዊ የሳይንስ ሊቅ፡ ኳስን በማንከባለል፡ በሳይንስ አረጋግጦ፡ ማለት፡ ማንኛውም አካል በሰዓት ከሰላሳ ማይል በላይ የሆነ ከፍተኛ ፍጥነት ካገኘ፡ ከመሬት ተነስቶ ይጠፋል ብሎ ነበር። ሳይንስ መቼስ ወደዚያ ወደ ኋላ ተመልሶ ይጠቅሰዋል ብላችሁ ታስባላችሁ? አሁን እዚህ መንገድ ላይ፡ በጎዳናው፡ በሰዓት መቶ ሃምሳ ማይል ሲያሽከረክሩ፡ ከዚያ ጋር አንዳች የሚጣጣም ነገር አለውን? አያችሁ? ነገር ግን ኳሱ መሬት ላይ በሚንከባለልበት ጊዜ ባለው ግፊት፡ በሰዓት ሰላሳ ማይል ሲጓዝ፡ ማንኛውም ነገር ከምድር ተነስቶ እንደሚሄድና፡ ወደ ጠፈር እንደሚወድቅ፡ በሳይንሳዊ መንገድ፡ አረጋግጦ ነበር። አይ፡ በዚያ ውስጥ ምንም ቀጣይነት የለም።

61 ነገር ግን በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ አንዱ ቃል ሌላውን አይቃረንም። አንድም ነቢይ ሌላውን ነቢይ ተቃርኖ አያውቅም። እያንዳንዳቸው፡ ፍጹም፡ ነበሩ። አንዱ መጥቶ ትንቢት ሲናገር፡ ያ እውነተኛ ነቢይ ተነስቶ ሲገስጸው፡ ያኔ እውነቱ ይገለጥ ነበር። አያችሁ? አያችሁ? ስለዚህ ለእውነተኛ አማኞች፡ መጽሐፍ ቅዱስ ሁሉ የእግዚአብሔር ቃል ነው።

62 አሁን፡ ሐኪሞች በሚስማሙበት ነገር ላይ ምንም ዓይነት ትክክለኛነት ማግኘት አትችሉም። አሁንም ቢሆን ከእነሱ ትክክለኛነትን ማግኘት አትችሉም። አሁን በሳይንስም ውስጥ ትክክለኛነትን ማግኘት አትችሉም።

አሁን፡ ታውቃላችሁ፡ ከጥቂት ጊዜ በፊት፡ እንዲህ ይህ... ይህም፡ “መጽሐፍ ቅዱስ ‘በአራቱ የምድር ማዕዘናት አራት መላእክት ቆመው አየሁ’ ሲል፡ ያ

ሊሆን አይችልም። ምድር ድቡልቡል ናት” ብለው ነግረውን ነበር። ነገር ግን መጽሐፍ ቅዱስ፡ “አራት ማዕዘናት” ነው የሚለው። እንግዲህ፡ አሁን እያችሁ፡ ከሁለት፡ ወይም ከሦስት ሳምንት በፊት፡ የጋዜጣ ጽሁፎች፡ ይህንን ዜና ሲያትሙ፡ ዓለም አራት ማዕዘን መሆኗን ደርሰውበታል። ስንቶቻችሁ ናችሁ ይህንን ያያችሁ? አዎን፡ እርግጥ ነው። እያችሁ? አንድ ሰው የሆነ ነገር እስኪል እየጠበቅሁ፡ ሁሉንም ገልብጬ አስቀምጬዋለሁ።

63 እናም አንድ ቀን፡ መቶ አምሳ ሚሊዮኑን፡ የብርሃን-ዓመታት ርቀትንም እያዩት እንዳልሆነ ይደርሱበታል። እየዞሩ ያሉት በክብ ዙሪያ ነው። ልክ እንደዚያው ነው።

ከእነዚህ ቀናት በአንዱ፡ ወደ ሰማይ ስትሄዱ፡ በራችሁ ወደ ሌላ ሰፍራ እንደማትሄዱ፡ ትደርሱበታላችሁ። አሁንም፡ ያላችሁት ልክ እዚሁ ነው፡ ዳሩ ግን ከዚህኛው ይልቅ ፈጣን በሆነ ሌላ ዳይሜንሽን ውስጥ ነው።

በዚህ ክፍል ውስጥ አሁን እያቋረጡ የሚያልፉ ቀለማት አሉ። እያንዳንዱ ቀለም፡ ሸሚዝ፡ ቀሚስ፡ የለበሳችሁት ማንኛውም ነገር፡ ዘላለማዊ ሆኖ፡ በቅጂ ላይ ሰፍሮ፡ በዓለም ዙሪያ ይሽከረከራል። ዓይኖቻችሁን ባርገበገባችሁ ቁጥር፡ በትክክል ተቀርጾ ይቀመጣል። ተመልከቱ፡ ቴሌቪዥን ይህንን ያረጋግጣል።

64 ስትወለዱ፡ እግዚአብሔር መቅረጫውን ይከፍተዋል። ብዙም... ሪከርድ ማድረግያው ሲከፍተው፡ ታውቃላችሁ፡ ለጥቂት ጊዜ ያን ያህል ድምፅ አያሰማም። ያም ትንሽ ህፃን ነው፡ ለሚያደርገው ነገር ተጠያቂ ወደሚሆንበት ዕድሜ እስኪደርስ ድረስ እንደዚያው ነው፥ ከዚያም ድምፁ ይጀምራል፡ መልስ ሊሰጥባቸው የሚገቡ ነገሮችን መናገርና ማድረግ ይጀምራል። ከዚያም ያ ሕይወት ሲያበቃ፡ ያ የተቀረጸው ክር ወይም ቴፕ ተነስቶ በ—በእግዚአብሔር ታላቅ ላይብሬሪ ውስጥ ይቀመጣል። አሁን፡ በፍርድ ዙፋን ፊት ከዚያ እንዴት ልታመልጡ ትችላላችሁ? ያደረጋችሁት እያንዳንዱ እንቅስቃሴ፡ በአዕምሯችሁ ውስጥ ያለፈው እያንዳንዱ ሀሳብ ሁሉ፡ ከፊታችሁ ዳግመኛ ይከፈታል። ያንን ማየት ትችላላችሁን? አሁን እግዚአብሔር ማየት...

65 ባለፈው ምሽት፡ እዚህ ቆሜ ሳለሁ፡ መድረኩ ላይ፡ አንድ ረጅም፡ መላጣ፡ በእውነትም መልከ-መልካምና፡ ብርቱ የሆነ ሰው ነበረ። እርሱም ወጣ... ጌታ ስለ ቤተሰቡና ምን ማድረግ እንዳለበት ብዙ ነገሮችን ነግሮት ነበር። ወጥቶም ተቀመጠ። ከጥቂት ደቂቃዎች በኋላ፡ ልክ እንደ እርሱ ያለ ሌላ ሰው ከፊቴ መጣ፡ ነገር ግን ራሱን አቀርቅሮ ነበር። መለየት ስላልቻልኩ፡ ውጪ ያለውን ሰውዬ ዳግመኛ ተመለከትኩት፥ እርሱም... እርሱ አልነበረም፡ ምክንያቱም ሌላ ነገር ነበርና። ይህንንም ሰው፡ ላገኘው አልቻልኩም። ዙሪያዬን ተመለከትኩ፡ ከኋላዬ፡ ማንም አልነበረም። እኔም፡ “ሰውዬው እዚያ ከመጋረጃዎቹ ጀርባ ተቀምጧል” አልኩ። እርሱም ወደዚች ቤተክርስቲያን የሚመጣው የእኛ... ወንድም ነበር፡ ያ ረጅም፡ መላጣ፡ መልከ መልካም የሆነው ሰው ልክ እንደዚያ ሆኖ እዚያ ተቀምጦ ነበር። በሆድ ህመም ችግር ምክንያት ሊሞት ደርሶ ስለነበር፡ ራሱን አቀርቅሮ፡ ይጸልይ ነበር።

ጫማ ሊገዛ አስቦ ነበር። ሚስቱ አዲስ ጫማ እንዲገዛ ፈልጋ ነበር። እርሱ ግን፡ “አይ፡ መግዛት አያስፈልገኝም፡ ምክንያቱም እድርጌው ለመኖር አልደርስምና” ነበር ያላት።

እየሞተ ነበር። እዚያም ተቀምጦ ሳለ፡ አያችሁ፡ በዚያኛው ዳይመንሽን ውስጥ፡ ሃሌሉያ፡ እግዚአብሔር ቀጥታ ወደዚያ ተንቀሳቀሰና፡ ልክ በነበረበት ሁኔታ፡ “እነሆ እዚያ ተቀምጧል” አለ። ምን ማለቴ እንደሆነ አያችሁ?

66 አሁን አስተውሉ፡ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ምንም ዓይነት ስህተት የለም። የእግዚአብሔር ቃል የሆነው፡ ኢየሱስ፡ በልብ ውስጥ ያለውን ሀሳብ ያውቃል። ዕብራውያን 4፥12፡ “የእግዚአብሔር ቃል የበረታ፡ የተሳለ ነው” ይላል። “የእግዚአብሔር ቃል የተሳለ ነው፡ ሁለት አፍ-ካለው ሰይፍ ሁሉ ይልቅ ኃይለኛ ነው፡ የአዕምሮን ሀሳብና ዓላማ እንኳን ይመረምራል።” አያችሁ? ወደ አዕምሮ ጠልቆ ይገባል፡ ጎትቶ ያወጣል፡ ይለያል። **መለየት** ማለት ምን ማለት ነው? “ማሳወቅ፡ ገልጦ ማውጣት” ነው። የእግዚአብሔርም ቃል የሚያደርገው ያንን ነው።

ዛሬ፡ “የካቶሊክ ቤተክርስቲያን የእግዚአብሔር ቃል ናት፥ ባፕቲስቶች፡ ሜቶዲስቶች፡ ጴንጤቆስጤዎች፡ ተብርናክል” እንላለን። ያ ስህተት ነው። ቃሉ መገለጥ ነው፥ በእግዚአብሔር ቃል የተገለጠው፡ እግዚአብሔር።

67 አይደለም፡ በሕክምና ባለሙያዎች መካከል፡ በሳይንቲስቶች መካከል፡ በተለያዩት ሰዎች መካከል ምንም ዓይነት ስምምነት ልናገኝ… አናገኝም።

አንስታይን የብርሃንን ህጎችና የ—የመሳሰሉትን ሲያጠና፡ አካላዊውን አተገባበር እንዳወቀ ሁሉ፡ መንፈሳዊውንም አተገባበር፡ አውቆ ቢሆን ኖሮ፡ አንዳች ነገር ሊነግረን በቻለ ነበር። እዚያ ሰማያት ውስጥ ስላለው ታላቅ ማዕከል የተናገረውን መልእክት ስሰማ፡ ይህም፡ “ከዚያ ማዕከል ጋር ከተገናኛችሁ፡ ምድሮችን መፍጠር ትችላላችሁ፡ ማንኛውንም ነገር ማድረግ ትችላላችሁ፡ ኃይሉም ወሰን የሌለው ይሆናል” ብሎ ነበር። አያችሁ? እርሱ ያንን አይቶት ነበር።

68 በአየር ላይ ሲያልፉ የምታዩአቸው እነዚህ ትናንሽ ነገሮች፡ “የሚበሩ ዲስኮች፡” የመሳሰሉት ይሏቸዋል። ሰዎች በጣም… ያ፡ መልካም፡ ያንን ብንተወው ይሻላል። እናንተም “እነዚህ ሁሉ ሰዎች ሲጠፉ ትሰማላችሁን” ትላላችሁ። ከእነርሱ ምንም አትሰሙም፥ እዚያው ቆመው ሳለ፡ በቅጽበት በዚያ አይገኙም።

ንጥቀትም ልክ እንደዚያ ነው የሚሆነው። ከእነርሱ አንዱ ቀጥታ ወደ ታች ይወርዳል፡ ይህም ምድራዊ አካል ሰማያዊውን አካል ይለብሳል። እነርሱም… የሚቀር ቆዳ፡ ፀጉር፡ ወይም አጥንት አይኖርም፥ በቅጽበት ይለወጣል፡ ከጠፈር ቀጥታ ወርዶ ያንን ወደ ቤት ይወስደዋል። ይህ ሁሉ አሁን እየሆነ እንዳለ እናያለን፡ ፔ—ፔንታጎን ስለ እነዚህ ብርሃናት፡ ምስጢራዊ ብርሃናትና፡ በ—በሰማይ ስለሚያዩት ነገር ሁሉ ግራ ተጋብቷል። በዚህ ሳምንት እዚህ ጀፈርሰንቪል ውስጥ በጋዜጣ ላይ አንዱንና፡ ፡ የመሳሰሉትን እንደጻፉ አይታችኋል፡ “ምስጢራዊ ብርሃን” ብለውታል። ስለዚህ፡ ኦህ፡ እነርሱ ምን እንደሆነ አያውቁም። ነገር ግን አዳምጡ፡ ትናንሽ ልጆች፡ ከእነዚህ ቀናት በአንዱ፡ ሊነጥቃችሁ ነው። አያችሁ? አያችሁ? አትጨነቁ።

አስታውሱ፡ ኢየሱስ፡ “በሰዶም ዘመን እንደነበረ” ብሏል።

69 ከሰዶም ጥፋት ጥቂት ቀደም ብሎ ምን ተፈጠረ? እግዚአብሔር ከተወሰኑ መላእክት ጋር ወረደ፡ የምርመራ ፍርድም አደረጉ። እንዲህ አለ፡ “እጅግ

ኃጢአተኛ፡ እጅግ ታላቅ እንደሆነች፡ ጩኸቷን ሰምቻለሁ፡ ስለዚህ ሙሉ በሙሉ እውነት መሆኑንና አለመሆኑን ለማረጋገጥ ወርጃለሁ” አለ። ልክ ነው? ከአብርሃም ጋር የቀረውን ያንን ዋነኛውን አስተውሉ፡ ከኋላው ሆና፡ ሳራ በልቧ ያሰበችውን ሀሳብ መለየት ችሎ ነበር።

አሁን፡ ዘወር ብላችሁ ጥቂት ተመልከቱና አስተውሉ፡ እያችሁ፡ ዛሬም ያንኑ ነገር እያደረገ እንደሆነ ተመልከቱ። የምርመራ ፍርድ ነው።

ለምን፡ ከጥቂት ጊዜ በኋላ፡ ቤተክርስቲያን፡ በዚያ ሰፍራ መቆየት ስትችልና፡ እያንዳንዱም ዘር ወደ ሰፍራው ሲመጣ፡ እነርሱ ይሄዳሉ። ምን እንደተፈጠረባቸው እንኳን እያውቁም። አንዱ በአንድ መንገድ ይሄዳል። እያችሁ? አንዱ ወደ ፓስተሩ ቤት ይሄድ ይሆናል፡ ሌላው ደግሞ **ወደዚህ**፡ ወይም **ወደዚያ** ይሄድ ይሆናል፡ በመጀመሪያ ደረጃ፡ እነርሱ፡ በዚያ አይገኙም። ሄኖክ ምሳሌ ነበረና፡ “እግዚአብሔር ወሰደው፡ አልተገኘምም።” ለመመርመር ወረደ! መጣጣሙን፡ የሄኖክ መነጠቅ፡ እስራኤል በመርከብ ውስጥ የመሻገሯ ምሳሌ እንዴት እንደሆነ...

70 እጅግ ፍጹም ነው፡ የእግዚአብሔር ቃል እጅግ ፍጹም ነው፡ ብሉይና አዲስ ኪዳን እንኳን ሳይቀር፡ ሁለት ግማሽ ክፍሎች አንድ ላይ ሲሆኑ ሙሉ የሆኑ አንድ ናቸው። በትክክል። ብሉይ ኪዳን የእርሱ ግማሽ ነው፡ አዲስ ኪዳንም የእርሱ ግማሽ ነው፥ በአንድ ላይ ስታመጧቸው፡ የኢየሱስ ክርስቶስን ሙሉ መገለጥ ታገኛላችሁ። እዚያ ነቢያት ሲናገሩ ነበር፡ እዚህ ደግሞ ይሄው በበአካል፥ እያችሁ፡ ሁለት ግማሾችና አንድ ሙሉ ናቸው። አሁን ብዙ ጊዜ መውሰድ አንፈልግም...

71 አሁን፡ ብሉይ ኪዳን ያለ አዲስ ኪዳን ሙሉ እንዳልሆነ፡ አስታውሱ። አዲስ ኪዳንም ያለ ብሉይ ኪዳን ሙሉ ሊሆን አይችልም። ሁለት ግማሾች፡ አንድላይ ሲሆኑ አንድ ሙሉ ያልኩበት ምክንያት ይህ ነው። ምክንያቱም፡ ነቢያት እንዲህ ብለዋል፡ “እርሱ እዚህ ይሆናል! እርሱ እዚህ ይሆናል! እርሱ እዚህ ይሆናል፡ **ይህንን** ያደርጉበታል። **ይህንን** ያደርጉበታል!” እነሆ እርሱ፡ “እርሱ እዚህ ነበረ! እርሱ እዚህ ነበረ፡ **ይህንንም** አደረጉበት፡ **ይህንንም** አደረጉበት።” ከጥቂት ምሽቶች በፊት ስለዚህ ጉዳይ ሰብኬ ነበር።

72 አሁን፡ መጽሐፍ ቅዱስን ለማጥናት፡ ጳውሎስ ጢሞቴዎስን፡ “እውነት የሆነውን፡ የእግዚአብሔርን ቃል በትክክል እየከፋፈልህ፡ አጥናው” አለው።

በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ሦስት የግድ ሊባሉ የሚገቡ ነገሮች አሉ። የእግዚአብሔርን ቃል በምንጠቀምበት ጊዜ፡ በፍጹም ልናደርጋቸው የማይገቡ ሦስት ነገሮች አሉ። አሁን በሚቀጥሉት አሥር ደቂቃዎች ስለ እነርሱ እናጥና፥ በፍጹም ልታደርጓቸው የማይገቡ ሦስት ነገሮች። በመላው ሀገሪቱ፡ በየትኛውም ሰፍራ ያላችሁ፡ ሁላችሁም፡ እርሳስ ከሌላችሁ እነዚህን ነገሮች በአዕምሯችሁ ውስጥ ማስቀመጣችሁን እርግጠኞች ሁኑ። እነዚህን ነገሮች በፍጹም ማድረግ የለባችሁም። ምን ማድረግ እንዳለባችሁ ሁልጊዜ እንነግራችኋለን፡ አሁን ግን ምን ማድረግ እንደሌለባችሁ ልነግራችሁ ነው።

73 አሁን፡ ቃሉን **በተሳሳተ መንገድ መተርጎም** የለባችሁም። እናንተም፡ “መልካም፡ ትርጉሙ **ይህ** ይመስለኛል” ትሉ ይሆናል። እርሱ የሚለው ልክ የተጻፈውን ነው። ምንም ተርጓሚ አያስፈልገውም። እንዲሁም ቃሉን

**አለሰፍራው** ማድረግ የለባችሁም። ደግሞ ቃሉን **አለቦታው** ማድረግ የለባችሁም። ከእነዚህ አንዱንም ብናደርግ፡ መላውን መጽሐፍ ቅዱስ ወደ መደናገርና ወደ ምስቅልቅል ውስጥ ይከተዋል።

74 አስተውሉ። ኢየሱስን በተሳሳተ መንገድ ብትተረጉሙት፡ ይኸውም እግዚአብሔር በሰው አምሳል መሆኑን ስታዛቡት፡ እ—እርሱን ከሦስት አማልክት አንዱ ታደርጉታላችሁ። ኢየሱስ ክርስቶስ ቃል መሆኑን በተሳሳተ መንገድ ብትተረጉሙት፡ እርሱን ከሦስት አማልክት አንዱ ታደርጉታላችሁ፡ ወይም በመለኮት ውስጥ ሁለተኛው አካል ታደርጉታላችሁ። ያንንም በማድረግ፡ መላውን መጽሐፍ ቅዱስ ታበላሹታላችሁ። የትም አትደርሱም። ስለዚህ በተሳሳተ መንገድ ሊተረጎም አይገባውም።

75 እንዲሁም አንድን ነገር፡ የራሳችሁን ትርጓሜ ሰጥታችሁት፡ ለሌላ ዘመን ብታውሉት፥ ወይም ለሌላ ዘመን የተነገረ ቢሆን፡ በዚያም የተሳሳተ ትርጓሜ ታደርጋላችሁ።

76 ማንም ሰው በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ኢየሱስ ክርስቶስን በተሳሳተ መንገድ ቢተረጉመው፡ ይኸውም እርሱ ራሱ እግዚአብሔር እንዳልሆነ አድርጎ፡ ሁለተኛ አካል፡ ወይም ከሦስት አማልክት አንዱ ቢያደርገው፡ ይህ በመላው መጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ያለውን እያንዳንዱን ቃል ያቃውሳል። “ከእኔ በቀር ሌሎች አማልክት አይሁኑልህ፡” የሚለውን የመጀመሪያውን ትእዛዝ ይጥሳል። መልካም። መላውን የክርስቲያን ዘር ሦስት የተለያዩ አማልክትን እንደሚያመልኩ የአረማውያን አምላኪዎች ሰብሰብ ያደርገዋል። ምን ዓይነት መጽሐፍ ቅዱስ እንደሚኖራችሁ አያችሁ? ከዚያም አይሁዳውያን ስለ እኛ እንደሚሉት ያደርገናል። እነርሱም፡ “ከእነዚያ አማልክት ውስጥ የእናንተ አምላክ የትኛው ነው” ይላሉ? አያችሁ? ስለዚህ፡ አያችሁ፡ አትችሉ... መጽሐፍ ቅዱስን በተሳሳተ መንገድ መተርጎም የለባችሁም።

ምክንያቱም፡ የአካሉ ክፍል እየተገለጠ ባለበት ዘመን፡ ራሱ ሲገለጥ የመጽሐፍ ቅዱስ ትርጓሜ ራሱ ኢየሱስ ነውና። የእጅ ዘመን ከሆነ፡ እጅ መሆን አለበት፥ የራስ ዘመን ሊሆን አይችልም። የድምፅ ዘመን ከሆነ፡ መልካም፡ እንደዛ ከሆነ፡ የእግር ዘመን ሊሆን አይችልም። አያችሁ? አሁን ደግሞ እኛ በዓይን ዘመን ውስጥ ነን። እንግዲህ ቀጣዩ፡ እርሱ ራሱ፡ መምጣቱ ነው። ማየት፥ ትንቢታዊ!

77 አያችሁ፡ በዘመናት ሁሉ፡ ከመጀመሪያው የቤተክርስቲያን ዘመን፡ ከመሠረቱ ጀምረናል፥ ያም ዘሩ ወደ መሬት በገባ ጊዜ፡ ሙሉው ዘር ማለት ነው። ከዚያም በእግሮቹ በኩል፡ በሉተር በኩል ወጣ፥ ቀጥሎም በዌስሊ በኩል ወደ ላይ ወጣ፥ ከዚያም ወደ ጴንጤቆስጤዎች፡ ወደ ልሳናት፡ ወደ ከንፈሮች ገባ፡ አያችሁ፥ አሁን ደግሞ በዓይኖች ውስጥ ነው፡ ትንቢታዊው፡ የሚልክያስ 4፡ ወዘተ። አሁንም ራሱ መጥቶ ወደዚያ ከመግባት በቀር ሊመጣ የተገባው የቀረ ሌላ ነገር የለም፡ ምክንያቱም ያ የመጨረሻው ነገር ነውና።

ቀጣዩ ብቃት ነው፥ የራሳችንም ብቃት የለንም፥ የእርሱ ነው። የራሳችንም ዕይታ የለንም። ሰው እነዚህን ነገሮች እንዴት አስቀድሞ ሊያይ ይችላል? ሊያደርገው አይችልም። እግዚአብሔር ራሱ ነው። አያችሁ፡ ወደ—ወደ አንድ ስፍራ እየደረሰ ነው። እርሱ አካሉን ከመጀመሪያ እስከ መጨረሻ

ሲያስተዳድረው ቆይቷል፡ ከዚያም የተሟላው የክርስቶስ አካል ከጎኑ በወጣች ሙሽራ መልክ ይገለጣል፡ ይኸውም አዳም በመጀመሪያው እንዳደረገው... ማለቴ፡ የአዳሟ፡ በመጀመሪያው እንደነበረችው ማለት ነው።

78 አዎን፡ "አምላክ፡" ይህ መላውን መጽሐፍ ቅዱስ ግራ በመጋባት ውስጥ ይከተዋል፡ የመጀመሪያውን ትእዛዝ ይጥሳል፡ አምላክንም፡ የሦስት አማልክት አረማዊ አምላክ ያደርገዋል። ይህም የ—የመጽሐፍ ቅዱስን አጠቃላይ ምስል ያበላሸዋል። ስለዚህ መጽሐፍ ቅዱስን በተሳሳተ መንገድ መተርጎም የለባችሁም። አሁን፡ ይህ አንዱ ነገር ብቻ ነው።

79 በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ያለው እያንዳንዱ ቃል፡ ተመሳሳይ አተገባበር ስላለው፡ በተገቢው ስፍራ ላይ ልታስቀምጡት ይገባችኋል። ከተገቢው ስፍራ ውጪ በማድረግም፡ በአንድ ዘመን እግዚአብሔር ልታደርጉት፡ በ—በቀጣዩ ዘመን ደግሞ ታሪክ ልታደርጉት ትችላላችሁ፡ ከተገቢው ስፍራ ውጪ ማድረግ ነውና። ስለዚህ ቃሉን ከተገቢው ስፍራ ውጪ ማድረግ የለባችሁም። እርሱ ሁልጊዜም እግዚአብሔር ነው። ዛሬ የጥንት፡ የታሪክ አምላክ ብቻ ካደረጋችሁትና፡ ዛሬም ያው ካልሆነ፡ ዕብራውያን 13፥8ን ምን ልታደርጉት ነው? አያችሁ፡ "እርሱ ትናንትና፡ ዛሬ፡ እስከ ዘላለምም ያው ነው።"

80 አሁን፡ ስለዚህ ይህ ምን ሊያደርግ እንደሚችልና፡ ምን እንዳደረገም ተመልከቱ። ቃሉን ከተገቢው ስፍራ ውጪ ማድረግ፡ እርሱ የገዛ ቃሉን እንዲክድ ያደርገዋል፡ ያ ደግሞ አስቀድሞ ተደርጓል።

81 መጽሐፍ ቅዱስን ማዛባት፡ አካሉን በተሳሳተ መንገድ መገጣጠም፡ እግር መሆን ያለበትን ራስ ማድረግ፡ ወይም እንደዚያ ያለ ነገር ሊሆን ይችላል። ይህ ልክ እንደ... በሌላ አባባል፡ ኢየሱስ የሙሴን መልእክት እንዲያስተምር ማድረግ ይሆናል። ምናልባት... ወይም ደግሞ ዌስሊ የሉተርን ዘመን እንዲያስተምር ማድረግ ሊሆን ይችላል። ወይም አሁን፡ የእኛን ዘመን፡ ጴንጤቆስጤን፡ የጴንጤቆስጤን መልእክት እንዲያስተምር ማድረግ ሊሆን ይችላል። እንዴት ያለ ምስቅልቅል ውስጥ እንደሚከት አያችሁ? ጴንጤቆስጤ አስቀድሞ እውነተኛ ማንነቱን አሳይቷል። ሉተር አስቀድሞ የራሱን አሳይቷል፡ ወደ የሐይማኖት ተቋምም ገብቷል። እዚያው ላይ ሞተ። ዘመኑ መታ፥ በዚያው አለፈ።

82 አስተውሉ፡ ድርጅት እንደሆነ፡ ወዲያውኑ ሞተ። አሁን፡ ይህ ልክ መሆኑንና አለመሆኑን እስቲ ተመልከቱ። ወደ ኋላ ተመልሳችሁ የታሪክን ገጾች መርምሩ። ድርጅት በሆነ ቁጥር፡ እዚያው ላይ ሞተ፡ ከዚያ ወዲህ ወደ ፊት ፈጽሞ አልቀጠለም። የ—የዚህን ዓለም አምላክ አምላኪ ሆነ፡ ወደ ልዩ ልዩ አካላት፡ ድርጅቶች፡ የሐይማኖት ተቋማትና፡ ቅዝቶች ውስጥ ገባ። የሪኪዎች ስብሰብ ወደዚያ ገብተው የራሳቸውን ተቃውሞ አቀረቡበት፡ ወይም፡ ይልቁንም፡ የራሳቸውን ሀሳብ አስገቡበት። ታዲያ ምን ተፈጠረ? ምስቅልቅሉ ወጣ። ስላምን የሚያመጣላቸው፡ ታላቅ የዓለም መሪ ያገኙ መሰሏቸው፡ ሰይጣንን ራሱን በዙፋን ላይ ወደሚያነግሱበት ወደዚህ ዓለም አምላክ መሪነት ሥር ለመጠቃለል እያመሩ ነው።

83 በቀደም ነግሬአችኋለሁ፡ እንደገና እለዋለሁ፡ ዛሬ ስልጣኔ ራሱ እንኳን ሙሉ በሙሉ የእግዚአብሔር ተቃራኒ ነው። ስልጣኔ ከእግዚአብሔር ተቃራኒ ነው።

ትምህርት ከእርሱ ሚሊዮን ማይሎች የራቀ ነው፥ ሳይንስም ሚሊዮን ማይሎች የራቀ ነው። ሳይንስና ትምህርት በሥነ መለኮት ኮሌጆችና፡ ትምህርት ቤቶች፡ በሳይንስ ክፍሎችና በመሳሰሉት፡ እግዚአብሔርን ሀሰተኛ ለማድረግ እየሞከሩ ነው፡ አያችሁ። መናወጣቸውን አግኝተዋል።

ባለፈው ምሽት ስለታየው ራእይስ ምን ትላላችሁ፡ ያ ሰው ወደ ታች ወዳሉት እነዚያ ሳይንቲስቶች ያንን ነገር እያፈሰሱ ሳለ ሲጮህባቸው የነበረውስ? እነርሱ ግን ዝም ብለው ዘወር ብለው ወደ ላይ አዩ፡ ከዚያም ስራቸውን ቀጠሉ። አንድ ተጨማሪ ጉዞ ይኖራል።

84 አስተውሉ፡ ኦህ፡ እነዚህ ሦስቱ የግድ ሊሆኑ ይገባል። አሁን፡ አትችሉም… ኢየሱስ የኖኅን መልእክት እየሰበከ አልመጣም፡ የሙሴን መልእክት እየሰበከ አልመጣም፡ ወይም ሙሴ እየሰበከ አልመጣም… አያችሁ፡ መጽሐፍ ቅዱስን ከተገቢው ስፍራ ውጪ አታድርጉት፡ በራሱ ጊዜ ውስጥ መሆን አለበት። አሁን፡ ልትተገብሩት አትችሉም…

ያ ታላቅ ሰው፡ ጆን ዌስሊ፡ ሲወጣ፡ ወይም፡ ያ ታላቅ ሰው፡ ሉተር፡ ሉተር ስለ መጽደቅ ያለውን መልእክት ይዞ ሲወጣ፡ አሁን ያ… ሉተር ታላቅ ሰው ነበረ፡ ቤተክርስቲያንን ከጨለማ ጠርቶ አወጣ፡ በእምነት መጽደቅንም መሠረተ፡ ያንንም ሲያደርግ፡ በእርሱ ላይ ድርጅት ገነቡበት እርሱም ሞተ። ሕይወቱ ግን፡ ልክ በስንዴ እገዳ ውስጥ እንዳለው ዓይነት፡ ቀጥታ ወደ ዌስሊ ዘመን፡ ወደ አበቦቹ ተጓዘ። ከዚያ ታላቅ ተሐድሶ ከወጡት ከእነ ዙዊንግሊ፡ ካልቪንና፡ ከተቀሩት ሁሉ ጋር አብረው የሞቱ፡ ሌሎች ቅጠሎች ከሉተር ወጡ።

85 ከዚያም ዌስሊ መጣ፡ ሌላ ዘመን ወደ አበቦች አብቦ ወጣ። ዌስሊ፡ አተርበሪና፡ እነዚያ ሁሉ፡ ጆ—ጆንና ወንድሙ፡ ሁሉም፡ መልእክት የያዙ ታላላቅ የእግዚአብሔር ሰዎች፡ ሀገሪቱን አጥለቀለቋት። ድርጅት አደረጉት፥ እርሱም ሞተ።

ከዚያም አሁን ፍሬውን ልታፈራ እንደሆነች በማስመሰል ወጣች፡ እና፡ ሲታይ ግን፡ ቅርፊቱ፡ ጴንጤቆስጤ ነበረች።

ነገር ግን ከዚህ ሁሉ ጀርባ፡ አንዲት ትንሽ እምቡጥ ወጣች።

አስተውሉ፡ አብዛኛው ጊዜ… የሉተራን ቤተክርስቲያን ድርጅት የሆነችው፡ ሉተር ወደ መስክ ከወጣ፡ ከሦስት ወይም አራት ዓመታት ገደማ በኋላ ይመስለኛል። ዌስሊ ወደ መስክ ከወጣ ከአጭር ጊዜ በኋላ፡ ድርጅት ሆነ።

86 በቱክሰን ውስጥ፡ የዌስሊ ቤተክርስቲያን፡ ወይም የሜቶዲስት ቤተክርስቲያን፡ እንዴት እንደተመሰረተች የሚያሳይ አ—አንድ ዝግጅት ነበረን። ወደዚህ ወደ አሜሪካ በመጡ ጊዜ፡ ከእነርሱ ብዙዎቹ ተመልሰው በ—በመምጣት ከእንግሊዝ ሀገር ያንን ወደዚህ ለማምጣት፡ ደንብና፡ የመሳሰሉትን እንዳቋቋሙ ተናገሩ፡ እንዲሁም ነገሩ ሁሉ እንዴት በድራማ መልክ እንደቀረበ አይተናል። ምን እንደተፈጠረ በዚያን ጊዜ አየሁ። እዚያው ላይ ሞተች።

87 መልካም፡ ከዚያም ጴንጤቆስጤዎች ወጡ፡ እነዚያ ከረጅም ዘመናት በፊት የነበሩት በጩኸት የሚያመልኩት ሰዎች፡ በልሳን የመናገርን ስጦታ አገኙ፡ በልሳን በመናገር ጀመሩ። ከዚያም፡ "የመንፈስ ቅዱስ ማረጋገጫ" ብለው

ሰየሙት። ከዚያም ድርጅት ሆኑ። አንዱ **ይህንን** ላደርግ ነው አለ፡ ሌላው ደግሞ **ያንን፡** ከዚያም ልዩ ልዩ ውዝግቦች ነበሩአቸው። ይህ ምን አደረገ? እያንዳንዳቸው ቅጠሎች ልክ በአገዳው ላይና፡ በአበቦቹ ላይ እንዳደረገው ሁሉ እንዲሁ ተዘረጉ። ዋንነስ፡ ቱነስ፡ ሰሪነስ፡ እንዲሁም ቸርች ኦፍ ጋድ፡ እነዚህ ሁሉ ሌሎቹ ነበሯቸው፥ ዝም ብለው ተዘረጉ፡ ተዘረጉ፡ ተዘረጉ።

አሁን ግን፡ ፍጹም ምሳሌ በሆነው፡ በተፈጥሮ መሰረት፡ በትምህርት ልታሰወጡት አትችሉም።

88 እዚያ ኬንታኪ ውስጥ ያሉ ጓደኞቼ የሆኑ፡ አንድ ቤተሰብ፡ በቀደም አንዲት ት—ትንሽ ህፃን ልጅ ተወለደችላቸው፡ እራት እየሰሩልን ሳለ እናቲቱ ተነስታ ነበር። ለአደን ለወጣን በርካታ ወንዶች እራት በማብሰል ረገድ ሌላኛዋን እህት እየረዳቻት ነበር። ህፃኗም ማልቀስ ጀመረች፡ እኔም እያወራሁ ነበር። እናቲቱ ትንሽ ያፈረች ይመስለኛል፡ ስለዚህ ሮጣ ሄዳ ህፃኗን ያዘቻት፡ ት—ትንሿን ልጅ ማ—ማጥባት ጀመረች። እኔም፡ "ታውቂያለሽ፡ ይህኮ ተፈጥሮ ነው" አልኳት። እያችሁ? አሁን፡ እናንተ...

አንድ ህፃን የሚፈልገውን ነገር ለማግኘት ከማልቀስ የተሻለ ሌላ መንገድ ፈጽሞ አላገኙም። አሁን፡ ምናልባት የ—የሥነ ምግባር መጽሐፍ ሰጥታችሁት፡ እዚህ አስቀምጣችሁት፡ "ልጄ ሆይ፡ ሥነ መለኮትን ላስተምርህ እፈልጋለሁ። አሁን፡ እንደ ሌሎቹ ልጆች እዚህ አካባቢ አትጩህ፥ አንተ የተለየህ ነህ። አሁን፡ መመገብ ስትፈልግ፡ እዚህ ጋ ያለችውን ይህችን ትንሽ ደወል ምታ" ትሉት ይሆናል። ፈጽሞ አይሰራም። አይ፡ በቃ አይሰራም።

89 ስለዚህ፡ ተፈጥሮን ስትመለከቱ፡ አሁን እያንዳንዱ ዘመን የት እንደደረሰ እናያለን፡ በመጨረሻው ዘመን ውስጥ እንዳለን በቀጥታ ያሳያል። ቅርፊቱ ተገፎ ወድቋል። አሁን ደግሞ አሥራ አምስት ዓመታት፡ አሁን ወደ ሃያ የሚጠጉ፡ ዓመታት፡ መልእክቱ ከሀገር ወደ ሀገር ሲዳረስ ቆይቷል፡ ዛሬ ጠዋትም በመላው በዚህ ሀገር በስልክ-መስመር ተገናኝተናል፡ እያችሁ፡ ሆኖም ምንም ድርጅት የለም። ድርጅት ሊሆን አይችልም። እንደዚህ ያለ ነገር መቼም አልነበረም፡ ከዚህም በኋላ አይኖርም። እያችሁ?

ዛሬ በመልእክቱ ላይ ያ—ያለው ችግር፡ ይህ ነው፡ በልባቸው የተቀበሉት ሰዎች እንዲበስሉ፡ በልጁ ህልውና ውስጥ መሆን አለባቸው። እያችሁ? መልእክቱን ልትቀበሉ ትችላላችሁ፡ ከዚያም ልጁ ጥሬነታችሁን ሁሉ በሙቀቱ እንዲያወጣው አድርጉ፡ እያችሁ፡ የበሰሉ ክርስቲያኖች ያደርጋችኋል። ምን ማለቴ እንደሆነ እያችሁ? እግዚአብሔር ቤተክርስቲያኑን ሊወስድ፡ በቅርቡ ይመጣል፡ እኛም እርሱ ሊቀበላቸው የሚገቡ እንደዚያ ያሉ ክርስቲያኖች ሊኖሩን ይገባል። ስ—ስንዴው መብሰል አለበት። መልካም።

90 እነዚህ ሦስቱ የግድ መሆን አለባቸው። በተሳሳተ መንገድ መተርጎም፡ ወይም በተሳሳተ መንገድ መያዝ፡ በተሳሳተ መንገድ መተርጎም፡ ወይም ከ-... ወይም ማዛባት የለባችሁም። ልክ እግዚአብሔር በተናገረበት መንገድ መቀመጥ አለበት።

ለዓለም፡ ይህ የምስጢር መጽሐፍ ነው። ሰዎች ይህ ዝም ብሎ ምስጢራዊ መጽሐፍ እንደሆነ ያምናሉ። በአንድ ወቅት እዚህ ከተማ ውስጥ ካለ፡ በክርስትና ታላቅ ሰፍራ ካለው እጅግ ታዋቂ ሰው ጋር እያወራሁ ነበር፡ እርሱም፡ "አንድ

ምሽት የራእይን መጽሐፍ ለማንበብ ሞክሬ ነበር” አለኝ። እንዲህም አለ፡ “ዮሐንስ እጅግ ብዙ የሚያቃጥል ቃሪያ በልቶ ቅዠት አይቶ መሆን አለበት” አለኝ። አያችሁ፡ የምስጢር መጽሐፍ ነው።

91 ነገር ግን ለእውነተኛው አማኝ፡ እየኖርንበት ባለው ዘመን ውስጥ እየተገለጠ ያለ የእግዚአብሔር መገለጥ ነው። ኢየሱስ፡ “ቃሎቼ መንፈስና ሕይወት ናቸው” ብሏል። እንደገናም፡ “ቃሉ ዘሪው የዘራው ዘር ነው” ብሏል። ይህ እውነት መሆኑን እናውቃለን። እርሱ በቃል መልክ ያለ እግዚአብሔር ነው፡ ሊተረጎም የሚችለውም በእርሱ በራሱ ብቻ ነው።

የሰው አዕምሮ የእግዚአብሔርን ሀሳብ ለመተርጎም አቅም የለውም። እርስ በርሳችን እንኳን የራሳችንን ሀሳብ መተርጎም አቅቶን ሳለ፡ ይህች ት—ትንሽ ወሰን ያላት አዕምሮ ወሰን የሌለውን ታላቁን ሀሳብ እንዴት ልትተረጉም ትችላለች?

92 እንደምታስተውሉት፡ ሊተረጉመው የሚችለው እርሱ ብቻ ነው፡ ሊተረጉምለት ለሚፈቅደው ይተረጉመዋልም። መጽሐፍ ቅዱስ፡ “የጥንት ሟቾች፡ በምድር ላይ ሲራመዱ በብዙ ዓይነትና በብዙ ጎዳና” አላለም። “እግዚአብሔር፡ በብዙ ዓይነትና በብዙ ጎዳና ራሱን ለነቢያቱ ገለጠ” ይላል እንጂ። አያችሁ?

93 እናም፡ “ሊገልጥለት ለሚፈቅደው፡” የሚለውን አስተውሉ። በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ራሱን ከየትኛውም እጅግ ብልጥ ከሆነ የሥነ መለኮት ምሁር፡ መሰወር በሚችልበት መንገድ አዘጋጅቶታል። ኦህ፡ ማይ! እዚያው በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ተቀምጦ፡ ራሱን መሰወር ይችላል፡ እናንተም ቀኑን ሙሉ ብትመለከቱትም በፍጹም አታዩትም፥ ዕድሜ ልካችሁን ብትመለከቱም፡ በፍጹም አታዩትም። እዚያው ተቀምጦ፡ ራሱን ዝም ብሎ መሰወር ይችላል።

94 አሁን፡ እባካችሁ፡ በየትኛውም ሰፍራ ያላችሁ፡ ይህ በልባችሁ ውስጥ ጠልቆ ይግባ። ይህም፡ እግዚአብሔር፡ በቃሉ ውስጥ፡ ራሱን በጣም ሊሰውር ስለሚችል፡ በዓለም ላይ ያለ የትኛውም የሥነ መለኮት ምሁር ወይም ትምህርት ቤት ሊያገኘው አይችልም፡ ነገር ግን እዚያው ተቀምጦ ይገኛል።

እናንተም፡ “ወንድም ብራንሃም፡ ያ ልክ ነውን” ትሉ ይሆናል?

ፈሪሳውያንንና ሰዱቃውያንን ምን ትሏቸዋላችሁ? በየዘመኑ የነበሩትንስ? እርሱ አድርጎታል። እርግጥ ነው። በየዘመናቱ ሁሉ እንዲሁ አድርጓል። አሁን ይህንን መመርመር እንችላለን። የኖኅን ዘመን እስቲ እናስብ፥ እጅግ ብልህ፡ የምሁራን ዘመን በነበረበት በዚያን ጊዜ፡ ራሱን በተሰፋ ቃሉ ውስጥ እንዴት እንደሰወረ። በሙሴ ዘመን፡ ራሱን እንዴት እንደሰወረ። በኤልያስ ዘመን፡ ራሱን እንዴት እንደሰወረ። በኢየሱስ ዘመን፡ ራሱን እንዴት እንደሰወረ። “በዓለም ነበረ፡ ዓለሙም በእርሱ ሆነ፡ ዓለሙም አላወቀውም። ወደ ገዛ ወገኖቹ መጣ፥ የገዛ ወገኖቹም አልተቀበሉትም።” አያችሁ?

95 በምድር ላይ ካሉት፡ እጅግ ብልህ ከሆኑ ምሁራን ራሱን ይሰውራል። እናንተም፡ “መልካም፡ ይህ ዶክተር ቅዱስ አባት **እከሌ-እና-እከሌ** ነውኮ” ትሉ ይሆናል። ማንም ቢሆን ግድ አይሰጠኝም፡ እግዚአብሔር ከእርሱ ራሱን ይሰውራል፥ ነገር ግን ሊማሩ ለሚፈቅዱ ሕፃናት ይገልጠዋል፡ አያችሁ፡ ለእግዚአብሔር ሕፃናት፡ አስቀድመው ለተወሰኑት ዘሮች።

96 እስቲ እስቡ። ኃያሉ እግዚአብሔር፡ በገዛ ቃሉ ውስጥ ተቀምጦ፡ የዚህን የአሁኑን ዘመን ብልህና፡ የተማሩ ሰዎችን ሲያሳውር፡ እነርሱም ይህንን አያዩም። ይህ ዝም ብሎ የአክራሪነት ስብስብ እንደሆነ ያስባሉ። ለጴንጤቆስጤዎች፡ ለባፕቲስቶች፡ ለሜቶዲስቶችና፡ ለፕሬስቢቴሪያን፡ ራሱን ሰውሮ እዚያ ሲቆም ተመልከቱት። ራሱን በአደባባይ በግልጽ እየገለጠ፡ ልዩ ልዩ ነገሮችን ሁሉ እያሳየ፡ በጋዜጦች ላይም ጭምር ወጥቶና፡ የመሳሰሉት ሆነው ሳለ፡ አሁንም ግን አያዩትም። ኦህ፡ አምላካችን ሆይ፡ እርሱ እንዴት ታላቅ ነው፡ ሊገልጥለት ለሚፈቅደው ራሱን ይገልጣል።

97 "ኦህ፡" እናንተም፡ "ወንድም ጆንስ ወይም ወንድም **እከሌ-እና-እከሌ፡** እ—እርሱ ታላቅ ሰው ነው። ይህንን ያየዋል" ትሉ ይሆናል። ኧረ፡ በጭራሽ። እርሱ ለሚፈልገው ሰው ይገልጠዋል። "ሚስቴ ይህንን አላየችውም፡ ደግሞ ክርስቲያን ሴት ናት፡" ትሉ ይሆናል። ራሱን ለሚፈልገው ሰው ይገልጥለታል። "እንግዲህ፡ የእኔ ፓስተር ታላቅ ሰው ነው።" ልክ ነው፡ ነገር ግን ራሱን ሊገልጥለት ለሚወደው ይገልጣል። አሁን፡ የተገለጠውን ነገር፡ አሁን እየሆነ ካለው ጋር አነጻጽራችሁ መርምሩ፡ ከዚያም እናንተ... በሚገባ ልትረዱት ትችላላችሁ።

98 አሁን እንግዲህ እንደምናስተውለው፡ የእግዚአብሔር መጽሐፍ እንጂ የሰው መጽሐፍ እንዳይደለ ያደርገዋል። የሰው ቢሆን ኖሮ... አሁን ራሱን እንዴት ሊገልጽ እንደሚችል እንመልከት። የጻፉትን ሰዎች ኃጢአት እንዴት እንደሚያጋልጥ ተመልከቱ፡ አስተውሉ፡ በዚያ ዘመን የ—የኖሩትን ሰዎች ኃጢአት።

ለምሳሌ፡ አብራሃምን ብንወስድ፡ እርሱ "የእምነት አባት" ተብሎ ተጠራ። ያ እንዴት እንደሆነ አስተውሉ... አብርሃም ይህንን መጽሐፍ ስለ ራሱ፡ ስለ ራሱ ፈሪነት ይጽፈዋል ብላችሁ ታስባላችሁ? ያኔ በዚያ ማለዳ ለንጉሡ በመዋሸት የተናገረውን ነገር፡ ሚስቱ ሆና ሳለ፡ እህቴ ናት ብሎ እንዴት ይጽፋል ብላችሁ ታስባላችሁ? ስለፈጸመው የፈሪነት ተግባሩ ይጽፍ ነበርን? በእርግጥም፡ ፈጽሞ አያደርገውም ነበር።

99 በማታለል የተሞላው ያዕቆብስ? ያዕቆብ አታላይ ነበርና። ይህ አንድ—አንድ—አንድ ሰው፡ አንድ ዕብራዊ ስለ ዕብራዊ ወንድሙ ሲጽፍ፡ በእርሱ ላይ መላው እስራኤል በተጠራበት፡ የመላው የአገሪቱ አባት የሆነውን ሰው ማታለል ሊጽፍ ይደፍር ነበርን? ከያዕቆብ፡ አባቶች ወጡ፥ ከነገድ አባቶች ደግሞ፡ ነገዶች ወጡ። የዚህ ሁሉ የመሠረት ድንጋይ የሆነውን እርሱን፡ መጽሐፍ ቅዱስ አታላይ ስለ መሆኑ ያጋልጠዋል። ልክ ነው? ሰው ይህን ይጽፈዋል ብላችሁ ታስባላችሁ? አያደርገውም፡ ጌታዬ።

100 እዚህ ምድር ላይ ከነበሩ ነገሥታት ሁሉ ታላቅ ስለነበረው፡ ዘውድ ስለጫነው ንጉሥ፥ ዳዊት፡ በዝሙት ስለመውደቁስ ሰው ሊጽፍ ይችላልን? እነዚያ አይሁዳውያን እጅግ የተከበረ ንጉሣቸው አመንዝራ እንደነበር ሊጽፉ ይችላሉን?

ኦህ፡ እኛ፡ "ጆርጅ ዋሽንግተን መቼም ዋሽቶ አያውቅም፡" የሚልና የመሳሰሉ፡ ታሪኮች አሉን። ያንን፡ ታሪክ ብለን እንጠራዋለን።

ዳሩ ግን ዳዊትን “አመንዝራ” የሚለው ይህ ሰው፡ መጽሐፍ ቅዱስ ነው፡ እንዲሁም ነበረ። ኢየሱስ የዳዊት ልጅ ተብሎ ሊጠራበት የተመደበው… የእስራኤል ንጉሥ፡ አመንዝራ ተባለ። ያ የማዕዘን ራስ ድንጋይ፥ በሥጋ አባቱ፡ አመንዝራ ነበረ። አይሁዳውያን እንደዚህ ያለ መጽሐፍ ፈጽሞ አይጽፉም ነበር። የሰው ልጅ ስለ ራሱ እንደዚህ ይጽፋልን? በእርግጥም አይጽፍም።

101 ያ ኩሩ የእስራኤል ህዝብ እንዴት ይሆን? ምን ያህል ኩሩዎች እንደነበሩ ታውቃላችሁ። ኩሩው የእስራኤል ህዝብ፡ ሄዶ ስለ ራሱ ጣዖት አምልኮ ይጽፋልን፡ በአምላኩ ላይ ሰላደረገው ዓመፅ ይጽፋልን፡ ሰላደረጋቸው፡ ቆሻሻና ርኩስ ነገሮች፡ በመጽሐፍ ላይ አሰፍሮ ይጽፋልን? በእርግጥ ያንን ይደብቁት ነበር። መልካም ነገሮችን ብቻ ያሳዩ ነበር። ነገር ግን፡ ይህ መጽሐፍ ቅዱስ፡ ትክክል የሆነውንና ስህተት የሆነውን ይናገራል። አይሁዳውያን ስለ ገዛ ርኩሰታቸው፡ ጣዖት አምልኳቸው፡ ውድቀታቸውና፡ ሰለነበራቸው ነገር ሁሉ፡ እንደዚህ ያለ መጽሐፍ ፈጽሞ እንደማይጽፉ፡ ማንም ያውቃል። ያንን መቼም አይጽፉም ነበር። ኧረ፡ በፍጹም።

ታዲያ፡ ማነው የጻፈው? መጽሐፍ ቅዱስ፡ በዕብራውያን 1፥1 ላይ፡ “ከጥንት ጀምሮ እግዚአብሔር፡ በብዙ ዓይነትና በብዙ ጎዳና ለአባቶቻችን በነቢያት ተናግሮ” ይላል። እንደዛ ከሆነ፡ ነቢያት አልነበሩም፡ ሟች ሰው አልነበረም። “እግዚአብሔር!” ነው እንጂ “ከጥንት ጀምሮ ነቢያት” አይደለም የሚለው። ነገር ግን፡ “ከጥንት ጀምሮ፡ እግዚአብሔር፡ በብዙ ዓይነትና በብዙ ጎዳና ለአባቶቻችን በነቢያት ተናገረ።”

እዚህ የጻፍኩት አንድ የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል አለ። ምን እንደሆነ አላውቅም፥ አሁን ላገኘው አልቻልኩም። አብዛኛውን ጊዜ፡ እነዚህን ነገሮች በምጠቅሰበት ጊዜ፡ መጽሐፍ ቅዱሰን እመለከታለሁ። ይቅርታ አድርጉልኝና፡ ለአንድ ደቂቃ ያህል ልፈልገው። 2ኛ ጢሞቴዎስ 3፥16 ነው። የ—የ— የማስታውሰው መሰሎኝ ነበር፡ ነገር ግን እዝናለሁ። ምን እንደሆነ ለማየት ለአንድ ደቂቃ ያህል እቆማለሁ።

102 “ከጥንት ጀምሮ፡ እግዚአብሔር በብዙ ዓይነትና በብዙ ጎዳና ለአባቶቻችን በነቢያት ተናግሮ።”

አሁን 2ኛ ጢሞቴዎስ 3፡ 3፥16። 3፥16 ላይ ምን እንደሚል እስቲ እንመልከት።

> **ቅዱስ ቃል በሙሉ** (አዎን) **የተሰጠው በማን ምሪት ነው** (በነብያት ነውን? አይደለም።)… **ምሪቱ የ** (ማን ነው?) **እግዚአብሔር፡ የእግዚአብሔር ሰው ፍጹምና፡ ለበጎ ሥራ ሁሉ፡ የተዘጋጀ ይሆን ዘንድ፡ ለትምህርትና፥**
>
> **ለተግሣጽ፡ ልብንም ለማቅናት በጽድቅም** ላለው **ምክር ደግሞ ይጠቅማል።**

103 መልካም፡ እንግዲያውስ፡ መጽሐፍ ቅዱስ ሁሉ የተጻፈው በመንፈስ ቅዱስ መሪነት ነው። ኢየሱስ፡ እዚህ ምድር ላይ ሳለ፡ ሰማይና ምድር ያልፋሉ፡ ቃሌ ግን አያልፍም ብሏል። ቅዱሳት መጻሕፍት ሁሉ ሊፈጸም ይገባዋል ብሏል። ስለዚህ መጽሐፉ የሰው ጽሑፎች መጽሐፍ አይደለም። የእግዚአብሔር ጽሑፎች መጻሕፍት ነው።

104 አሁን፡ እግዚአብሔር ቤተክርስቲያኑን፡ ሰፍራውን፡ ነቢያቱንና ስለ እርሱ ያለውን ነገር ሁሉ፡ አስቀድሞ በመወሰን እንደመረጠ እናውቃለን። አስቀድሞ በማወቅ፡ ነቢዩን አስቀድሞ ወስኗል። ዘመኑም ሲደርስ፡ ነቢዩ በዚያው ጊዜ እንዲደርስ አደረገ፡ በእርሱም በኩል መጽሐፍ ቅዱስን ሲጽፍ በመንፈሱ መራው። አሁን፡ እግዚአብሔር መጽሐፍ ቅዱስን የጻፈው ነቢዩን ብቻ በመጠቀም ነው፡ ምክንያቱም ነገሮችን የሚያደርግበት የእርሱ መንገድ ያ ነውና። ስለዚህ፡ አያችሁ፡ እርሱ የሰው ቃል አይደለም… ስለዚህ፡ አያችሁ፡ እርሱ የእግዚአብሔር ቃል እንጂ፡ የሰው ቃል አይደለም።

105 እግዚአብሔር አካል ነው። እግዚአብሔር ሊናገር ይችላል። እግዚአብሔር ሊያወራ ይችላል። እግዚአብሔር ሊጽፍ ይችላል። በዚያ መንገድ ማድረግ አይጠበቅበትም ነበር፡ ነገር ግን እ—እርሱ ሊያደርገው የመረጠው በዚያ መንገድ ነው። በዚያ መንገድ ማድረግ አይጠበቅበትም ነበር፡ ነገር ግን በዚያ መንገድ ሊያደርገው መረጠ። አሁን እናንተ፡ “እግዚአብሔር አሥርቱን ትእዛዛት በጣቱ፡ ግርማ ሞገስ ባለው፡ በገዛ ጣቱ ጻፈ። ስለዚህ እግዚአብሔር፡ ከፈለገ፡ ራሱ መጻፍ ይችላል” ትሉ ይሆናል። አያችሁ? ነገር ግን እ—እርሱ በነቢያት በኩል ሊጽፈው መረጠ፡ አያችሁ። ምክንያቱም እርሱ በእነርሱ በኩል የገለጸው የእርሱ ባህርያትና ቃሉ ስለነበረ፡ ሁሉንም ክፍል፡ ወይም የእርሱ አካል ክፍል ሰላደረጋቸው ነው። አያችሁ? በጣቱ መጻፍ ይችል ነበር። ደግሞም ጣቱን ተጠቅሞ በባቢሎን ግድግዳዎች ላይ፡ “በሚዛን ተመዘንክ ቀለህም ተገኘህ” ብሎ ጽፎ ነበር። በገዛ ጣቱ ጽፏል።

106 እግዚአብሔር መናገር ይችላል። እግዚአብሔር መናገር እንደሚችል ታምናላችሁን? በተራራው ላይ በሚነደው የእሳት ቁጥቋጦ ውስጥ ሆኖ፡ ሙሴን አናገረው። ይህንን ታምናላችሁን? አዎን፡ ወዳጄ። በርግብ አምሳል ሆኖ፡ ዮሐንስን አናግሮታል፡ (ይህንን ታምናላችሁን?) “በእርሱ ደስ የሚለኝ የምወደው ልጄ ይህ ነው፡” አለ። አናግሮታል። በጴጥሮስ፡ በያዕቆብና፡ በዮሐንስ ፊት፡ በመገለጥ ተራራ ላይ ኢየሱስን አነጋግሮታል። መናገር ይችላል። እርሱ ዲዳ አይደለም። እግዚአብሔር መናገር ይችላል። ስለዚህ በመገለጥ ተራራ ላይ—ኢየሱስን አነጋግሮታል። እንዲሁም በታላቅ ሕዝብ ፊት ኢየሱስን ተናግሮታል፥ በዚያን ጊዜም፡ ሕዝቡ ነጎድጓድ ነው አሉ፡ ዳሩ ግን እግዚአብሔር ኢየሱስን እያነጋገረው ነበረ። ማቴዎስ፡ ማርቆስ፡ ሉቃስና፡ ዮሐንስ፡ ከሞላ ጎደል ኢየሱስ የተናገረበት ነው። እርሱ እግዚአብሔር ነው። ስለዚህ፡ እግዚአብሔር መናገር ይችላል።

107 አንድ ቀን፡ በገዛ ጣቶቹ አሸዋ ላይ ጽፏል። ሥጋ ሆኖ በመካከላችን ባደረ ጊዜ፡ በገዛ ከንፈሮቹ፡ ተናግሯል፡ ሰብኳል፡ ትንቢትም ተናግሯል፡ እግዚአብሔር ይህንን አድርጓል፡ “እግዚአብሔር በሥጋ ተገለጠ።” መጻፍና፡ መናገር ከቻለ፡ ለሌሎችም ምን ማድረግ እንዳለባቸው ሊነግራቸው አይችልምን? በእርግጥም ይችላል። በሰው ድምፅ ሊያነጋግራቸው ይችላል። ምን ማድረግ እንዳለባቸው ጽፎ ሊያሳያቸው ይችላል። አድርጎታልም።

ስለዚህ፡ “ከጥንት ጀምሮ እግዚአብሔር፡ በብዙ ዓይነትና በብዙ ጎዳና ለአባቶቻችን በነቢያት ተናግሮአል።” እንዲህ አለ፡ በዚህ ጽሑፍ ላይ፡ “እስኪፈጸም ድረስ አንዲት ጆት ወይም አንዲት ነጥብ ከቶ አታልፍም፡” ብሏል፡ ከዚያም ይገለጣል፥ ከዚያም ይፈጸማል፡ ምክንያቱም ተገልጧልና። እንደዛ

ካልሆነ ሊፈጸም አይችልም፡ ነገር ግን ቃሉ ራሱ ሥጋ ሆኗል። **ጆት** ማለት “ትንሽ ቃል” ማለት ነው። **ነጥብ** ማለት ደግሞ “ትንሽ ምልክት” ማለት ነው። በእግዚአብሔር ቃል ውስጥ አንዲትም ሥርዓተ ነጥብ፡ አንዲትም አገላለጽ፡ ወይም ምንም ነገር፡ ፈጽሞ አይወድቅም። ሊወድቅ አይችልም፡ ምክንያቱም እርሱ እግዚአብሔር ነው፡ እግዚአብሔር በሰው ሥጋ አምሳል የተገለጠ ነው። ምክንያቱም፡ እግዚአብሔር ራሱ በፊደል መልክ፡ በነቢይ መልክ፡ በሥጋ የተገለጠ ነውና።

አሁን፡ ኢየሱስ እንዲህ ያለበት ምክንያት፡ “እነዚያን፡ በእግዚአብሔር ቃል የተናገሯችሁን፡ ‘አማልክት’ ትሏቸዋላችሁ፡” “በርግጥም አማልክት ነበሩ፡” አለ። እነዚያ ነቢያት በእግዚአብሔር መንፈስ ተቀብተውና፡ የእግዚአብሔርን ቃል በትክክል ባመጡ ጊዜ፡ ያኔ አማልክት ነበሩ። በእነርሱ ይናገር የነበረው የእግዚአብሔር ቃል ነበር፡ እ—እነርሱ ሊተረጉሙ የሚችሉት ደራሲው እንዲተረጉሙ በፈቀደላቸው መጠን ብቻ ነው።

108 አሁን፡ ያንን ማግኘት ከፈለጋችሁ፡ 2ኛ ጴጥሮስ 1፥20ና 21 ላይ ነው። መልካም። ምክንያቱም፡ ይህ፡ እግዚአብሔር… ማንም ለገዛ ራሱ ሊተረጉም አይችልም፡ እርሱ ራሱ የራሱን ትርጓሜ ይሰጣል።

እግዚአብሔር ይናገራል፡ ራሱም ይተረጉመዋል፡ ከዚያም ሊገልጥለት ለሚፈቅደው ይገልጠዋል፡ ከሌሎች ሁሉ ይሰውረዋል። ካልፈለገ በስተቀር ለማንም መግለጥ አይጠበቅበትም። እርሱ… እርሱ፡ እርሱ ነገሩን ሁሉ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ገልጾታል፡ ስለዚህ ነገሩ ሁሉ አስቀድሞ ታውቋል፥ ዝም ብሎ ሲፈጸም እያየ ተቀምጧል ማለት ነው። አያችሁ? አይ። ዝም ብሎ አካሉ ሲሰራና ወደ መጀመሪያ፡ መልኩ፡ ዳግመኛ ሙሽራይቱ ወደሆነችው ሲመለስ እያየ ነው። መልካም።

109 አማኞች ያምኑታል፡ አብርሃም ከቃሉ ጋር የሚቃረኑትን ነገሮች እንዳልነበሩ አድርጎ እንደጠራቸው ሁሉ ማለት ነው።

110 እንዲሁም፡ ይህ ቃል የልብን ምስጢር ይመረምራል፡ ዕብራውያን 4፥12። “የልብንም ምስጢር ይመረምራል።”

111 ነቢያት ምን እየጻፉ ወይም ምን እየተናገሩ እንደነበር ሁልጊዜ አይረዱም ነበር፡ ሊረዱት ችለው ቢሆን ኖሮ በምንም ሁኔታ አይናገሩትም ነበር። አያችሁ? መጽሐፍ ቅዱስ ግን፡ “በመንፈስ ቅዱስ ተነድተው” ይላል። ተነድተው! መንፈስ ቅዱስ ሲነዳችሁ፡ ትነዳላችሁ። ሰው… “እግዚአብሔር፡ ከጥንት ጀምሮ በብዙ ዓይነትና በብዙ ጎዳና በመንፈስ ቅዱስ በተነዱ ነቢያት ተናገረ።” በዘመናት ሁሉ፡ መንፈሳውያን የነበሩ ሰዎች ስለ ዘመናቱና ሊሆን ስላለው ነገር ነቢያትን ያማክሩ የነበረው፡ ለዚህ ነው።

ጸሐፊው-ነቢይ ከደራሲው ጋር ዘወትር ኅብረት ሊኖረው ይገባል። አያችሁ? መጽሐፉ ምን ሊሆን እንዳለው ለማወቅ፡ ዘወትር በደራሲው ፊት ሊኖር ይገባዋል። አያችሁ? ጸሐፊው-ነቢይ፡ ደራሲው ከሆነው ከእግዚአብሔር ጋር፡ ዘወትር ኅብረት እያደረገ፡ እርሱ ጻፍ ያለውን ማንኛውንም ነገር ለመጻፍ፡ በማንኛውም ጊዜ ብዕሩን አዘጋጅቶ ይጠብቃል። አያችሁ? ይህ ደግሞ ምን ዓይነት ሕይወት ሊኖረው እንደሚገባ ያሳያል… ከወንድሞቹ ሁሉ የተለየ ሕይወት።

112 አሁን፡ የነቢዩ አዕምሮ ዘወትር እግዚአብሔር በተናገረው ላይ ብቻ የሚያተኩረው ለዚህ ነው፥ ሰው ባሰበው፡ ዘመኑ ባሰበው፡ ቤተክርስቲያን ባሰበችው፡ ወይም መንግሥት ባሰበው ላይ አይደለም። እግዚአብሔር ባሰበው ላይ ነው! የእግዚአብሔርን ሀሳቦች ወደ ቃልነት ይገልጻል እንጂ ሌላ አያደርግም፡ ምክንያቱም ቃል ማለት አንድ ሀሳብ ሲገለጽ ማለት ነውና። አሁን ገባችሁን? ቃል የተገለጠ ሀሳብ ነው፡ ስለዚህ ነቢዩ የእግዚአብሔርን ሀሳቦች ይጠባበቅ ነበር። እግዚአብሔርም ሀሳቡን በገለጠለት ጊዜ፡ ያንን በቃል ይገልጸዋል፡ "**የሰራዊት ጌታ እግዚአብሔር እንዲህ ይላል።**" አያችሁ፡ "እኔ ነቢዩ፡ እንዲህ እላለሁ" አይልም። "**የሰራዊት ጌታ እግዚአብሔር እንዲህ ይላል!**" አያችሁ? መልካም።

113 መንግሥታትንና የቤተክርስቲያን ዘመናትን የተቃወሙት ለዚህ ነው፡ ይህም፡ በዘመናቸው ደግሞ ይህንን ማድረግ የሞት ቅጣት ያስከትል ነበር። በንጉሥ ፊት ቀርባችሁ፡ "**የሰራዊት ጌታ እግዚአብሔር እንዲህ ይላል፡ ይህ-እና-ይህ** ሊሆን ነው" ብትሉት፡ አንገታችሁን ትቆረጡ ነበር። ቤተክርስቲያንም ዛሬውኑ ይህንን በማድረጋችሁ ትገድላችኋለች። ነገር ግን እነዚህ ነቢያት ደፋሮች ነበሩ። ለምን? በመንፈስ ቅዱስ ተነድተው ነበር፡ አያችሁ፡ እነርሱም፡ ደፋሮች የሆኑበት ምክንያት፡ ያ ነው። እንዲሁም ስህተት የሌለበትን የ—የእግዚአብሔርን ቃል ጻፉ።

114 እንደ ካህናትና፡ የመሳሰሉት፡ እነዚያን ነቢያት ለማስመሰል የሞከሩ ብዙዎች ነበሩ። ታዲያ ምን አደረጉ? ነገሩን ከማበላሸት በቀር ያደረጉት የለም፡ ያ ነው በቃ። ሊያደርጉት አልቻሉም።

ምክንያቱም፡ እግዚአብሔር ለዘመኑ የሚሆነውን ሰው መርጦ ነበር፡ መልእክቱንም መርጦ ነበር፡ አልፎ ተርፎም የሰውየውን ተፈጥሮና በዚያ ዘመን ምን ሊሰራ እንደሚችል፡ እርሱ ምን ሊያስተላልፍ እንደሚችል፡ የዚያን የተወሰነ ሰው ተፈጥሮ በመጠቀም፡ የሌሎችን ዓይኖች እንዴት ማሳወር እንደሚችል፡ መርጦ ነበር። ያ ሰው የሚናገራቸው ቃላትና የሚያደርጋቸው ድርጊቶች፡ አንዳንዶችን ሲያሳውር፡ የሌሎችን ዓይኖች ይከፍት ነበር። አያችሁ? ሰውን በዚያ በነበረው ዓይነት ልብስ አለበሰው፥ ተፈጥሮው፡ ፍላጎቱና፡ ሁሉም ነገር ልክ ሊሆን በሚገባው መንገድ ሆኖ፡ በዚያ በተወሰነው ዘመን ለሚጠራቸው የተወሰኑ ሰዎች እንዲሆን ፍጹም በሆነ ሁኔታ መረጠው።

ይህም፡ ሌሎች ቆመው ሲመለከቱት፡ "መልካም፡ አልችልም። ይህ... ማ—ማየት አልችልም፡" ይላሉ። ታውረው ነበር።

115 ኢየሱስም ልክ በዚሁ መንገድ መጣ፡ የማይሞተው እግዚአብሔር የሰው ሥጋ፡ ለብሶ መጣ። በበረት ውስጥ፡ ፍግ በሞላበት ጋጥ ውስጥ በመወለዱ፡ ራሱን የሚያስጠጋበት ስፍራ ስላልነበረው፥ እንደ ሰዎች አስተሳሰብ፡ ዲቃላ የሚል ስም ተለጥፎበት፡ ተወለደ። አያችሁ? የነበረባቸው እነዚህ ነገሮች ሁሉ፡ የአናጢ ልጅ ሆኖ፡ እንዴት እንዳደገ፡ እንዴት ትምህርት ቤት እንዳልገባ አስተውሉ።

በጥቅሉ ሲታይ፡ በዓለም ላይ፡ ከዚህ ዓለም ጥበብ ጋር፡ ምንም ግንኙነት አልነበረውም። ከዚህ ዓለም ሰልጣኔ፡ ትምህርት፡ ወይም ከማንኛውም ነገር ጋር፡ እንዳችም ግንኙነት አልነበረውም። ለምን? እርሱ እግዚአብሔር ነውና።

ይጋጭ ነበር። ወደ አንድ ሴሚናሪ ሄዶ እነዚህ የዓለም አብያተ ክርስቲያናት የሚያደርጉትን አንዳች ነገር ለመማር ቢሞክር ኖሮ፡ ምን… ለምን፡ እንዲሁም በፍጹም… ለምን፡ በፍጹም… ከእርሱ ማስተዋል ጋር በፍጹም አይገጥምም ነበር፡ ምክንያቱም እርሱ እግዚአብሔር ነበረና።

ስለዚህ፡ ትምህርት፡ ትምህርት ቤቶች፡ ሴሚናሪዎችና፡ የመሳሰሉት፡ ሙሉ በሙሉ ለእግዚአብሔር ፈቃድ ተቃራኒ ናቸው። መላው የትምህርት መዋቅር ለእግዚአብሔር ተቃራኒ ነው። ሁሉም ነገር ሁልጊዜ፡ ከእግዚአብሔር የሚያርቅ ትምህርት ይሰጣል። አንድ ሰው ዶክተር፡ ፒ.ኤች.ዲ፡ ኤል.ኤል.ኪው ነኝ ሲል ስሰማ፡ ያ ለእኔ፡ ያ ሰው ከእግዚአብሔር እጅግ የራቀ መሆኑን ነው የሚያሳየኝ። አያችሁ? በእውነት እንዲያደርግ ከተጠራው ነገር ራሱን በማስተማር እጅግ አራቀ። በትክክል።

አሁን እንዴት በመንፈስ ቅዱስ ይንቀሳቀሱ እንደነበር አስተውሉ።

116 አሁን፡ ይህ ማለት የተማሩ ሰዎች ወደዚህ አይመጡም ማለት አይደለም። ጳውሎስን ተመልከቱ። የጠርሴሱ ሳውል የነበረው ጳውሎስ፡ በዘመኑ ከእርሱ የበለጠ ብልህ ሰው የነበረ አይመስለኝም። በዘመኑ ከነበሩት ታላላቅ መምህራን አንዱ በነበረው፡ በገማልያል ስር ተምሮ ነበር፥ እርሱ ታላቅና፡ ጥብቅ ዕብራዊ፡ የሐይማኖት ተቋም ፈሪሳዊ ነበረ። ጳውሎስም ያደገው በእርሱ ስር ነበረ። የአይሁድን ሐይማኖት ሁሉ ያውቅ ነበረ። ነገር ግን ወደ ቤተክርስቲያን በመጣ ጊዜ፡ እንዲህ አለ፡ "በሰዎች ትምህርትና፡ በመሳሰሉት ወደ እናንተ አልመጣሁም። ምክንያቱም፡ እንዲሁ ባደርግ ኖሮ፡ በዚያ በታመናችሁ ነበር። ዳሩ ግን እምነታችሁ በእግዚአብሔር እንዲሆን፡ በመንፈስ ቅዱስ ኃይልና መገለጥ ወደ እናንተ መጣሁ" አላቸው። ይኼውና። አያችሁ? በትክክል።

117 ብዙዎች እነዚህን ሰዎች ለማስመሰል ሞክረው ነበር፡ ነገር ግን ልክ ዛሬ እንደሚያደርጉት ነገሩን ሁሉ አበላሹት። ከኢየሱስ ዘመን በፊት አንድ ሰው ተነስቶ፡ አራት መቶ ሰዎችን መርቶ ነበረ። ጊዜው ከመድረሱ በፊት ለማድረግ ሲሞክሩ፡ መጽሐፍ ቅዱስ ስለ እነዚህ ነገሮች እንዴት እንደሚያነብ ታውቃላችሁ። ከእነርሱም አንዳንዶቹ እርሱን ለማስመሰል ሞክረው ነበረ፡ እነርሱም **ይህ፡ ያ፡** ወይም **ሌላኛው** ነበሩ። እርሱም፡ "በመጨረሻው ዘመን፡ ሀሰተኛ ክርስቶሶች፡ በመጨረሻው ዘመን ሀሰተኛ ነቢያት፡ እንዴት እንደሚነሱና፡ ምልክቶችንና ድንቆችን እንደሚያሳዩ" ተናግሯል። ያ ሁሉ አለን። አያችሁ? ዳሩ ግን ያ እውነተኛውን ነገር አያስወግደውም። ይበልጥ እንዲያበራ ያደርገዋል እንጂ፡ ምክንያቱም እውነተኛው ክርስቶስ እንጂ፡ ሀሰተኛው የለንምና።

118 አሁን፡ እንግዲህ፡ እግዚአብሔር ነቢያቱን እንደላከ እንረዳለን። ቃሉን በነቢያቱ ከንፈሮች በኩል፡ ወደ ሕዝቡ የሚያመጣበት መንገዱ ያ ነበረ።

አስተውሉም፡ ሙሴ፡ በዘጸአት 4ኛ ምዕራፍ፡ ከ10 እስከ 12 ቁጥር ላይ ማንበብ ከፈለጋችሁ፡ የተናገረውን ታውቃላችሁ። እግዚአብሔር እንዳናገረው ሙሴ ተናግሯል። እግዚአብሔር ሰውን አነጋገረው፡ ከከንፈር ወደ ጆሮ። ሙሴም፡ "አፌ ኮልታፋ ነው፡" አለ። "እኔ፡ እኔ ብቁ አይደለሁም። መ—መሄድ አልችልም።"

119 እርሱም፡ "ሰውን እንዲናገር ያደረገው ማን ነው፡ ወይስ ዲዳ ያደረገው ማን ነው? እንዲያይ ያደረገው ማን ነው፡ ወይስ እንዲሰማ ያደረገው ማን ነው? እኔ

ጌታ፡ አይደለሁምን? ” እንዲህም አለው፡ “እኔ ከአፍህ ጋር እሆናለሁ” አለው። እያችሁ? ስለዚህ...

120 በኤርምያስ 1፥6 ላይ፡ ያንን ማንበብ ከፈለጋችሁ ኤርምያስም ይህንኑ ብሏል። ኤርምያስ፡ “እግዚአብሔር ቃሉን በአፌ ውስጥ አኖረ” ብሏል። አያችሁ? እ—እርሱ አንዱን ነቢይ፡ ከከንፈር ወደ ጆሮ፡ አናገረው፥ በሌላኛው ነቢይ በኩል ደግሞ ተናገረ፡ በራሱ ላይ ምንም ቁጥጥር አልነበረውም፡ በከንፈሮቹም ተናገረ።

121 ታውቃላችሁ፡ ቃሉን የሚያወጣበት የራሱ መንገዶች አሉት። አዎን፡ ወዳጄ። ስለዚህ መጽሐፍ ቅዱስ የእግዚአብሔር ቃል እንጂ፡ የሰው ቃል እንዳልሆነ አያችሁ።

ሙሴ፡ “እግዚአብሔር በድምፅ አነጋገረኝ፡ እኔም ሰማሁት። የተናገረውንም ጻፍኩ” አለ።

122 ኤርምያስ እንዲህ አለ፡ “መናገር ፈጽሞ አልቻልኩም ነበር። እናም፡ በመጀመሪያ ደረጃ፡ ከንፈሮቼ መናገር ጀመሩና፡ እ—እ—እኔም እጽፍ ነበር” አለ። እግዚአብሔር በከንፈሮቹ በኩል ተናገረ፡ እርሱም ተፈጸመ።

ዳንኤል፡ ኢሳይያስና፡ የመሳሰሉት፡ እነዚያ ነቢያት ሁሉም ተመሳሳይ ነበሩ።

123 ታውቃላችሁ፡ በብሉይ ኪዳን ብቻ፡ እነዚያ ነቢያት ከሁለት ሺህ ጊዜ በላይ **የሰራዊት ጌታ እግዚአብሔር እንዲህ ይላል** ብለዋል። አሁን፡ አንድ ሰው **የሰራዊት ጌታ እግዚአብሔር እንዲህ ይላል** ካለ፡ እየተናገረ ያለው ሰውዬው አይደለም። እንደዚያ ቢሆን ኖሮ፡ ነቢይ አይሆንም፡ ግብዝ ይሆን ነበር፡ አያችሁ፡ ምክንያቱም (ፈጽሞ) አይፈጸምም ነበር፥ ከአሥር መቶ ሺህ ጊዜያት አንዴ፡ አያችሁ፡ በግምት ሊያገኙት ይችላሉ። ዳሩ ግን **የሰራዊት ጌታ እግዚአብሔር እንዲህ ይላል** ከሆነ፡ ጌታ እግዚአብሔር ተናግሮታል ማለት ነው።

“ኦርማን ኔቪል እንዲህ ይላል፡” ብል፥ ወንድሜ፡ “ሚስተር ማን እንዲህ ይላል” ቢል፥ እዚህ ጋር፡ “ወንድም ቬይል እንዲህ ይላል፡” ወይም ከነዚህ ሌሎች ወንድሞች መካከል፡ አንዳችሁ እንዲህ ይላል ብል፡ ማናችሁንም ብል፥ እየተናገርኩ ያለሁት እናንተ ያላችሁትን ነው። እውነተኛ ከሆንኩ፡ እየተናገርኩ ያለሁት ልክ እናንተ ያላችሁትን ነው።

እነዚህም ሰዎች፡ ነቢያት በመሆናቸው፡ “እኔ አይደለሁም። ከዚህ ጋር ምንም ግንኙነት የለኝም፡ ዳሩ ግን **የሰራዊት ጌታ እግዚአብሔር እንዲህ ይላል** ነው፡” አሉ። ስለዚህ መጽሐፍ ቅዱስ በነቢያት በኩል የመጣ **የሰራዊት ጌታ እግዚአብሔር እንዲህ ይላል** ነው።

124 አስተውሉ፡ የክርስቶስን መንፈስ በራሳቸው ላይ ወስደው፡ ወደ ፊት የሚሆኑትን ክስተቶች አስቀድመው ተናገሩ። እስቲ ስለ ትንቢት አስቡ! በዘመናት ሁሉ ምን እንደሚሆን ተናገሩ፡ ሲቀመጡ፡ ሲቆሙ፡ ሲተኙ፡ ሲራመዱ፡ ልክ እንደ ክርስቶስ እስኪሆኑ ድረስ፡ የክርስቶስ መንፈስ በላያቸው ሆነ። አንባቢያንም ሲያነቡት ነቢያቱ ስለ ራሳቸው እየተናገሩ እንደሆነ ያስቡ ነበር።

ጃንደረባው፡ በኢሳይያስ 53፥1 ላይ፡ ይህም፡ “እርሱ ግን ስለ መተላለፋችን ቆሰለ፡ ስለ በደላችንም ደቀቀ፡ የደኅንነታችንም ተግሣጽ በእርሱ ላይ ነበረ፡ በእርሱም ቍስል እኛ ተፈወስን” የሚለውን ሲያነብ ታስታውሳላችሁ?

ጃንደረባውም ለፊልጶስ፡ “ነቢዩ ይህን ስለ ማን ይናገራል፡ ስለ ራሱ ነው ወይስ ስለ ሌላ” አለው? አያችሁ፡ ነቢዩ ልክ ስለ ራሱ እንደሆነ አድርጎ ተናገረ።

125 ዳዊት በመንፈስ ሆኖ ሲጮህ ተመልከቱ፡ “አምላኬ፡ አምላኬ፡ ለምን ተውከኝ? አጥንቶቼ፡ ያዩኛል፡ እኔን ይመለከቱኛል፡” ያ ዳዊት ነው። “እጆቼንና እግሮቼን ቸነከሩኝ፡” እንዲህ ያለው ዳዊት ነው። “እጆቼንና እግሮቼን ቸነከሩኝ። ነፍሴን በሲኦል አትተዋትምና፡ ቅዱስህንም መበስበስን ያይ ዘንድ አትስጠውም፡” ይህን ያለው ዳዊት ራሱ ቅዱስ እንደሆነ አድርጎ ነው። ያ በዚያ በኩል ሲወርድ የነበረው ሕይወት ያለው፡ መንፈሳዊው ዘር፡ የዳዊት ልጅ ነበረ። ምንም እንኳን ዳዊት ራሱ የሾህ አረም ቢሆንም፡ በዚያ ውስጥ ግን የስንዴ ዘር ነበረ። ተረዳችሁ?

ስለዚህ፡ መላው መጽሐፍ ቅዱስ የሰው ቃል አይደለም፡ በሰውም አልተጻፈም፡ በሰውም፡ እንዲሁም በሰው ሊ—ሊገለጥ አይችልም። በእግዚአብሔር ራሱ የሚገለጥ የእግዚአብሔር ቃል ነው፡ የራሱ አስተርጓሚ ነው፥ ክርስቶስ በገዛ ቃሉ ውስጥ ራሱን ይገልጣል።

126 ወደ ኋላ ተመልሳችሁ ክርስቶስን እዚህ በዳዊት ውስጥ ቆሞ ተመልከቱት። ዳዊት አሁን ማሰብ እንኳ አልቻለም ነበር። አዕምሮው ከእርሱ ርቆ ነበር፡ ሊባል ይችላል። እርሱም በመስቀል ላይ ተሰቅሎ ነበር፡ ልክ እዚህ ያለውን ሐውልት እንደምታዩት፥ በመስቀል ላይ ተሰቅሎ፡ እየጮኼ፡ “አምላኬ፡ አምላኬ፡ ለምን ተውከኝ? አጥንቶቼ ሁሉ፡ ያዩኛል። እጆቼንና እግሮቼን ቸነከሩ። ጎኔንም ወጉት” እያለ ይጮኽ ነበር። አያችሁ? “ለምን ከእኔ ራቅህ? የባሳን በሬዎች ሁሉ ከበቡኝ። እንዲህ እያሉ፡ ራሳቸውን ይነቀንቃሉ፡ ‘እንደሚያድነው፡ በእግዚአብሔር ታመነ፥ እስቲ አሁን ያድነው እንደሆነ እንይ፡’” ያንኑ ቃል እየተናገረ ነበር።

ስለዚህ፡ አያችሁ፡ እግዚአብሔር እዚህ ምድር ላይ በተገለጠ ጊዜ፡ ዳዊት የተናገራቸውን እነዚያኑ ቃላት ተናገረ። ተረድታችኋልን? ስለዚህ፡ አያችሁ፡ እርሱ የሰው ቃል አይደለም፥ እርሱ የእግዚአብሔር ቃል ነው። በዳዊት ውስጥ እግዚአብሔር ነበረ፥ ያ ዳዊት አልነበረም። ምን እያለ እንደነበር አላወቀም፥ ሙሉ በሙሉ በመንፈስ ውስጥ ነበረ እንጂ።

ሙሴም እንደዚሁ ነበረ። ሙሉ በሙሉ በመንፈስ ውስጥ ስለነበር፡ ከሚኖርበት ዓለም አልፎ በመሄድ፡ እዚያ በሚነደው ቁጥቋጦ ውስጥ፡ ፊት ለፊት ቆሞ፡ እ—እ—እግዚአብሔርን ራሱን ያነጋግረው ነበር። “ጫማህን አውልቅ። የቆምክባት ስፍራ የተቀደሰች ናትና፡” አለው።

ሙሴ ከዚያ ሲወጣ፡ “ምን ተፈጠረ? ምን ተከናወነ? ምንድን ነበረ፡” ብሎ ያሰበ ይመስለኛል?

“ወደ ግብፅ ውረድ። እኔ ከአንተ ጋር እሄዳለሁ፡” አለው።

እርሱም፡ “ይህ ለእኔ እጅግ እውን ስለሆነ፡ መሄድ አለብኝ” አለ። ሚስቱንና ልጆቹን... ልጁን፡ ማለቴ፡ በትሩንም በእጁ ይዞ፡ ሕዝቡን ነጻ ለማውጣት፡ ወደ ግብፅ ወረደ። አያችሁ?

127 እግዚአብሔር፡ ራሱ፡ በነቢያት በኩል ይናገራል። አያችሁ፡ እነርሱ፡ እነርሱ በፍጹም... ነቢያቱ አልነበሩም፥ እግዚአብሔር ነበረ። ምክንያቱም፡ ነቢያቱ፡

በራሳቸው፡ እነዚያን ነገሮች ሊናገሩ አይችሉም ነበር።

“የሰማነውን ማን አምኖአል? ” አለ ኢሳይያስ፡ አያችሁ። “የሰማነውን ማን አምኖአል? የእግዚአብሔርስ ክንድ ለማን ተገልጦአል? በፊታችን በ—በጋጥ ውስጥ እንዳለ ጥጃ ያድጋል። ሆኖም፡ እርሱ፡ ስለ መተላለፋችን ቆሰለ፡ ስለ በደላችንም ደቀቀ፡ የደኅንነታችንም ተግሣጽ በእርሱ ላይ ነበረ፥ በእርሱም ቍስል እኛ ተፈወስን።” እኛ እዚህ ዘመን ውስጥ ሆነን፡ ተፈወስን፥ ኢሳይያስ ደግሞ፡ ከክርስቶስ በፊት ከስምንት መቶ ዓመታት በፊት እዚያ ነበረ። አያችሁ? “በእርሱ ቍስል እኛ፡” ያለፈ ጊዜ፡ አስቀድመን፡ “ተፈወስን።” ኦህ፡ ማይ!

የእግዚአብሔር ቃል፡ እንዴት፡ እጅግ ፍጹም ነው! ወገኖቼ፡ በእርሱ ታመኑ። ሊያድናችሁ የሚችለው ብቸኛ ነገር እርሱ ነው።

128 ሌሎቹ ቃላት ሁሉ፡ ምን ያህል በጥሩ ሁኔታ ቢቀመጡ፡ እንዴት፡ ከማንም ቢመጡ፡ ከየትኛውም የሐይማኖት ተቋም ቢመጡ፡ ወይም ሰውዬው ምን ያህል ብልህ ቢሆን ለእኔ ግድ አይሰጠኝም፡ ከቃሉ ጋር የሚቃረን ማንኛውም ነገር፡ ሙሉ በሙሉ ችላ ሊባል ይገባዋል። ያንን ጥቅስ መጻፍ ከፈለጋችሁ፡ ገላትያ 1፥8 ላይ ነው ያለው። አያችሁ? ጳውሎስ፡ “እኛ ብንሆን፡ ወይም ከሰማይ መልአክ፡ አስቀድማችሁ ከሰማችሁት ሌላ የተለየ ወንጌልን ቢሰብክላችሁ፡ የተረገመ ይሁን” ብሏል።

በሌላ አባባል፡ አንድ መልአክ ከሰማይ ወደ እናንተ ቢመጣ፡ ብሩህና የሚያበራ መልአክ ሆኖ፡ ቢቆም፥ ወንድሜ፡ ያ ለዚህ ዘመን እጅግ ማታለያ ይሆን ነበር፡ አይደለም እንዴ? የሚያበራ ብሩህ መልአክ እዚያ መጥቶ ቢቆምና፡ ከቃሉ ጋር የሚቃረን ነገር ቢናገር፥ “ሰይጣን፡ ከእኔ ራቅ፡” በሉት። በትክክል። ጳጳስም ቢሆን፡ እርሱ... ማንም ቢሆን፡ ከዚህ መጽሐፍ ቅዱስ ጋር ቃል በቃል በትክክል ካልተናገረ፡ በፍጹም አታምኑት። ተመልከቱት፡ አሁን በመጽሐፍ ቅዱስ ይወስዳችኋል። ወደ አንድ የተወሰነ ስፍራ ይወስዳችሁና፡ ልክ እዚያ ላይ ያጠምዳችኋል። መጽሐፍ ቅዱስ አንድ ነገር ሲናገር ካያችሁና፡ እርሱ ግን ያንን አልፎት ከሄደ፡ ልክ እዚያ ላይ ተጠንቀቁት።

አያችሁ፡ በሔዋን ላይ ያደረገው እንደዚያ ነው። ቀጥታ ወረደና ሁሉንም ነገር ልክ በትክክል ተናገረ። “መልካም፡ እግዚአብሔር **ይህንን** ብሏል።”

“ልክ ነሽ፡ ሔዋን። አሜን። ያንን፡ አብረን እናምናለን።”

“መልካም፡ እግዚአብሔር **ይህንን** ብሏል።”

“አሜን። ያንን አብረን፡ እናምናለን።”

“እግዚአብሔር **ይህንን** ብሏል።”

“ያንን እናምናለን፡ አዎን።”

“መልካም፡ ነገር ግን እግዚአብሔር እንሞታለን ብሏል።”

129 “መልካም፡ አሁን፡ እርሱ ጥሩ አምላክ እንደሆነ ታውቂያለሽ።” አላደረገውም አላለም፡ ታውቃላችሁ። “ነገር ግን በእርግጥ... ” ኦህ፡ ማይ! እነሆ ተመልከቱት።

እርሱም በዚህ ልክ አታላይ ከነበረ፡ እንዲሁም መጽሐፍ ቅዱስ፡ “በመጨረሻው ዘመን ቢቻል ኖሮ የተመረጡትን እንኳ እስከ ማሳት ይደርሳል”

አለ፡ ወዳጆቼ፡ ዛሬ እኛ የት መሆን አለብን? አሁን፡ እነዚህ አጫጭር የሰንበት ትምህርቶች፡ ታውቃላችሁ፡ ለማየት፡ በልባችን ውስጥ፡ እጅግ ጠብቀን ልንይዛቸው ይገባል... እጅግ በጥሞና አዳምጠን ያ ነገር ምን ያህል አታላይ እንደሆነ ልናይ ይገባል።

130 አስተውሉ፡ የሌላን ማንም ሰው ቃል፡ መስማት አንችልም፡ መስማትም የለብንም። ምንም ያህል ብልህ ቢሆን፡ ምን ያህል የተማረ ቢሆን ለእኛ ግድ አይሰጠንም። መጽሐፍ ቅዱስ፡ በምሳሌ መጽሐፍ ውስጥ፡ "የሰውን ሀሳብ መጣል አለብን፡" ይላል። አያችሁ? አሁን፡ እዚህ በዚህ በሁለተኛው ዳይመንሽን ውስጥ...

የመጀመሪያው ዓለም የማየት፡ የመቅመስ፡ የመዳሰስ፡ የማሽተትና፡ የመስማት ሕዋሳቶቻችሁ ናቸው። ያ በውጫዊ አካላችሁ ውስጥ ያለው ነው።

መንፈስ በሆነው፡ በውስጣዊው አካል ውስጥ ደግሞ፡ ማመዛዘን፡ ሀሳብና፡ የመሳሰሉት አሉ። ያንን ሁሉ አፍርሰን መጣል አለብን። እንዲህ በማለት፡ ማመዛዘን አንችልም፡ "ቆይ እስቲ፡ እግዚአብሔር ጥሩ አምላክ ከሆነ... " ዛሬም እርሱ ጥሩ እንደሆነ እጅግ ብዙ ተነግሮናል። "እርሱ ጥሩ አምላክ ከሆነ፡ ከዚያም እኔም ቅን ሰው ከሆንኩ፡ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ያለው ያ ትክክል እንደሆነ ማየት ባልችልም፡ ቅን ከሆንኩ፡ እድናለሁ።" ትጠፋላችሁ። [በቴፕ ላይ ባዶ ቦታ አለ—አርታዒ።]

131 "ወደ ቤተክርስቲያን ብሄድና ትክክል ነው ብዬ የማምነውን ነገር ብቻ ባደርግ፡ እንዲሁም ትክክል ነው ብዬ የማስበውን ነገር አጥብቄ ለመያዝ ብሞክር፡ መልካም፡ እኔ... " አሁንም የጠፋችሁ ናችሁ።

"ለሰው ቅን የምትመስል መንገድ አለች፡ ፍጻሜዋ ግን የሞት መንገድ ነው።" አያችሁ? አትድኑም፥ ትጠፋላችሁ። አያችሁ? አያችሁ? ያ በውስጥ ሆኖ የሚቆጣጠረው ሰው ሊሆን ይገባዋል።

132 "መልካም፡ በልሳን እኮ ተናግሬአለሁ፡ ወንድም ብራንሃም። ደህና፡ በልሳን መናገርን አታምንም'ዴ፡ ወንድም ብራንሃም? " ያለ ጥርጥር። "ታዲያ፡ እኔ ጮኬያለሁ፥ ያንን አታምንም እንዴ? " አዎን፡ ወዳጄ። "ጥሩ ክርስቲያናዊ ሕይወት ነው የምኖረው። በዚያ አታምንም? " አዎን፡ ወዳጄ። ዳሩ ግን አሁንም ያ ማለት ድናችኋል ማለት አይደለም። እናንተ ጥሩ ሰው ናችሁ፥ ንጹህ፡ ስነ ምግባር ያላችሁ፡ ቅዱስ፡ ጥሩ ሰው ናችሁ።

እነዚያ ካህናትም ልክ እንደዚያው ነበሩ፡ እስከ ጥግ ድረስ ሐይማኖተኛ የነበሩ፡ እጅግ ሐይማኖተኛ ከመሆናቸው የተነሳ፡ አንዱ አንዲት ነገር እንኳ ቢያዛባ በድንጋይ ተወግሮ ይሞት ነበር። በእግዚአብሔር ቃል ላይ ማላገጥ የሚያስከትለው ቅጣት ሞት ነበረ።

133 ዛሬ በሀገራችን ላይ ያለው ችግር ያ ነው። ዛሬ በምድር ላይ እንዲህ ያሉ እጅግ ብዙ ልቅ-የሆኑ ስርዓተ አልባ ነገሮች የበዙበት ምክንያት፡ ቅጣቶቹ ከባድ ስላልሆኑ ነው። አንድ ሰው ከሌላ ሰው ሚስት ጋር ሲማግጥ ቢያዝ፡ ሁለቱም በአደባባይ እንዲወጡ ተደርጎ በአደባባይ እንዲኮላሹ መደረግ አለባቸው፡ በአደባባይ፡ ከዚያም እንዲለቀቁ መደረግ አለበት፡ በትክክል። ልክ ነው። አንድ ሰው በመንገድ ላይ፡ ሲያሽከረክር አንዳች ጥፋት ሲፈጽም፡ በፍጥነት ሲያሽከረክር ቢገኝ፡ ከአሥር ዓመት ያነሰ ቅጣት ሊሰጠው አይገባም፥ እርሱ-...

አስቀድሞ የታሰበበትን ግድያ ፈጽሟልና። አያችሁ? እንደዚህ ያሉ ቅጣቶችን ብታስቀምጡ ኖሮ፡ ድርጊታቸውን ገታ ታደርጉት ነበር።

ነገር ግን አንድ አጭበርባሪ ፖለቲከኛ **እዚህኛው** ሰው ዘንድ ደርሶ ነገሩን ሸፋፍኖ፡ "እንግዲህ፡ ያው ትንሽ ጠጥቶ ነበር፡ እንጂ... አስቦበት አላደረገውም፡" ብሎ ያልፈዋል። በዚህም አንድን ሰው፡ ሚስቱንና፡ በርካታ ንጹሃን ልጆችን ቢገድልም እንኳ፡ ያ ሪኪ ያለምንም ቅጣት እንዲያመልጥ ይፈቀድለታል፡ ያ ፖለቲካ ነው። ያ ዓለም ነው። ያ ዲያብሎስ ነው።

134 እግዚአብሔር፡ አንድ ወንድ ወይም አንዲት ሴት በዝሙት ቢያዙ፡ አውጥታችሁ በድንጋይ ውገሯቸው ብሏል። ያ እልባትን ሰጠው። አያችሁ? በሰንበት ቀን፡ አንዲት ትንሽ እንጨት ሲለቅም እንኳን ቢገኝ፡ "ወስዳችሁ በድንጋይ ውገሩት።" በዚያን ጊዜ በዚያ ህግ ይኖሩ ነበር። አሁን ግን፡ አያችሁ፡ ዛሬ እንደዚያ ዓይነት ህጎች የሉንም።

ነገር ግን ክርስቲያን ለሆናችሁት፡ ዛሬ ጠዋት እያናገርኳት ላለሁት፡ ቤተክርስቲያን፡ ያ የእግዚአብሔር ህግ በልባችሁ ውስጥ ነው። አያችሁ? ያንን ለማድረግ ምንም ፍላጎት የላችሁም። እዚህ ውስጥ ነው። የእግዚአብሔርን ህግ እጅግ ፍጹም በሆነ ሁኔታ መጠበቅ ትፈልጋላችሁ። ምን መሆን እንዳለባችሁ ለውጥ አያመጣም፡ መሆን የምትፈልጉት ልክ... እ—እግዚአብሔር በበሩ ላይ የእግር መጥረጊያ ቢያስፈልገው፡ እናንተንም ያ መረገጫ እንድትሆኑ ቢፈልግ፡ ያንን ለመሆን እጅግ ደስተኞች ትሆናላችሁ። ምንም ቢሆን፡ ያንን መረገጫው መሆን ትፈልጋላችሁ። አያችሁ? እግዚአብሔር እንድታደርጉ የሚፈልገውን ማንኛውንም ነገር፡ ማድረግ የምትፈልጉት ያንኑ ነው፡ ምክንያቱም እርሱ እግዚአብሔር ነውና። አሁን፡ ለእግዚአብሔር ያላችሁን ትክክለኛ፡ እውነተኛና፡ ጥልቅ ፍቅር የምታገኙት እዚያ ላይ ነው።

135 አሁን የምናገኘው ነገር፡ አስቀድሞ ከወጣው ውጪ፡ "መልአክ እንኳ ሌላ ማናቸውንም ነገር ቢሰብክ፡" ይህም፡ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ አስቀድሞ ከተነገረው ውጪ፡ "የተረገመ ይሁን።" ማንም አይችልም። ያንን ማድረግ አይችልም፥ ልክ ቃሉ እንደሚለው በትክክል እንደዚያው መሆን አለበት።

136 እንደገናም፡ በራእይ 22፥18ና 19 ላይ፡ "ማንም በዚህ ላይ አንዲት ቃል ቢጨምር፡ ወይም ከእርሱ አንዲት ቃል ቢያጎድል፡ እግዚአብሔር እድሉን ከሕይወት መጽሐፍ ያጎድልበታል" የምለውን እናነባለን። በትክክል። አገልጋይም ቢሆን፡ ማንም ቢሆን፡ ቃሉ... ስሙ በሕይወት መጽሐፍ ላይ ተጽፎ ቢሆንም እንኳ፡ እግዚአብሔር እድሉን ያጎድልበታል። እግዚአብሔርም፡ "በእርሱ ላይ አንዲት ነገር ቢጨምር፡ ወይም ከእርሱ አንዲት ቃል ቢያጎድል፡" በትክክል፡ "ፈጽሜ እፍቀዋለሁ" አለ። ይህ እግዚአብሔር ቃሉን ምን ያህል ስህተት የሌለበት እንዳደረገው ያሳያል። አያችሁ? በቤተክርስቲያን ላይ ልትጨምሩ፡ ወይም ከቤተክርስቲያን ልታጎድሉ ትችላላችሁ። ነገር ግን በዚያ ቃል ላይ አትጨምሩ፡ ወይም ከእርሱ አታጉድሉ፡ ምክንያቱም እግዚአብሔር ስማችሁን ከሕይወት መጽሐፍ ላይ ፈጽሞ ያጠፋዋልና። እናም፡ ያኔ፡ አበቃላችሁ ማለት ነው። አያችሁ? በእርሱ ላይ ልትጨምሩ፡ ወይም ከእርሱ ልታጎድሉ አትችሉም። በትክክል...

137 ምንም አስተርጓሚ አያስፈልገውም፡ ምክንያቱም እግዚአብሔር መጽሐፍ ቅዱስን ራሱ እንደሚተረጉም መጽሐፍ ቅዱስ ተናግሯልና። ጴጥሮስ፡ “ማንም ራሱ ሊተረጉም አይችልም” ብሏል። መልካም።

138 ቅዱሳት መጻሕፍትም ሁሉ በመለኮታዊ መንገድ የተሰጡ ናቸው፡ በመለኮታዊ ሥርዓትም የተጻፉ ናቸው፡ ነገሩ ሁሉ የኢየሱስ ክርስቶስ መገለጥ ነው። ስለ እርሱ መምጣት፡ እዚህ ሲመጣ ምን እንደሚያደርግ፡ እንዲሁም በዚህ በሚመጣው ዘመን ምን እንደሚያደርግ አስቀድመው የተነበዩበት አዲሱና ብሉይ ኪዳን ናቸው። ያም እርሱን ትናንትና፡ ዛሬ፡ እስከ ዘላለምም ያው ያደርገዋል። አያችሁ?

ጳውሎስ እዚያ ዕብራውያን ላይ እንደጻፈው፡ ማለት ነው። እርሱ እግዚአብሔር ነው፡ የብሉይ ኪዳኑ፡ “የትናንቱ ኢየሱስ ክርስቶስ” ነው። በሥጋ የተገለጠው፡ “የዛሬው ኢየሱስ ክርስቶስ” ነው። “እስከ ዘላለምም ኢየሱስ ክርስቶስ ነው፡” በመንፈስ፡ “ሊመጣ ያለው” ነው። አያችሁ? አያችሁ? “ትናንትና፡ ዛሬ፡ እስከ ዘላለምም ያው ነው።”

ቃሉ ለዚያ ዘመን ያደርገዋል ብሎ የተናገረውን ሕያው ለማድረግም ለዘላለም ሕያው ሆኖ ይኖራል። እርሱ ሕያው ነው።

139 በብሉይ ኪዳን ውስጥ ሕያው ነበረ፡ ተገለጠም። ልትሸከሙት ከቻላችሁ፡ እዚህጋ አንዲት ትንሽ ነገር እንድታዩ እፈልጋለሁ። ተመልከቱ፡ እኛ እንደምናምነው፡ ኢየሱስ በብሉይ ኪዳን ውስጥ በተገለጠ ጊዜ።

አሁን፡ እዚያ ያላችሁ እናንተ ሰባኪዎች፡ ልትከራከሩበትና፡ የፈለጋችሁትን ልታደርጉ ትችላላችሁ፡ እኔ ግን እየተናገርኩ ያለሁት ለእኔ... እኔ ስለማስበው ነገር ነው። አያችሁ?

140 ኢየሱስ በብሉይ ኪዳን፡ በቲዮፋኒ፡ በመልከ ጼዴቅ አካል በተገለጠ ጊዜ፡ ክህነት ሳይሆን፡ አካል፡ ሰው ነበረ። አያችሁ? ምክንያቱም፡ ይህ ሰው ገና አልተወለደም ነበር፡ ነገር ግን በቲዮፋኒ ውስጥ ነበረ፡ ስለዚህ አባትና እናት አልነበሩትም። እርሱ እግዚአብሔር ራሱ ነበረ። “የሰላም ንጉሥ፡ እንዲሁም የጽድቅ ንጉሥ የሆነ፡ የሳሌም ንጉሥ፡” ተብሎ፡ በሰው አምሳል ተገለጠ። አያችሁ? እርሱ መልከ ጼዴቅ ነበረ። “አባትና እናት፡ ለቀኖቹ መጀመሪያ ወይም ለሕይወቱ ፍጻሜ አልነበረውም።” አያችሁ? እርሱ በቲዮፋኒ ውስጥ፡ በሰው አምሳል የነበረ ኢየሱስ ነበረ። ይህንን ልትቀበሉ ትችላላችሁን? መልካም።

141 ከዚያም እርሱ በእውነት የሰው ሥጋ ሆነ፡ በመካከላችም አደረ፡ ይኸውም ከድንግል ማርያም በተወለደው፡ በኢየሱስ ክርስቶስ ራሱ አካል ነበረ። መሞት ይችል ዘንድ በዚያ መልክ መጣ፡ ከዚያም ወደ ሰማይ ተመለሰ።

አሁን በዚህ በመጨረሻው ዘመን፡ በመንፈስ፡ በሥጋው ሙላት፡ ራሱን ዳግመኛ ሊገልጥ ተስፋ ሰጥቷል። አያችሁ? “በሰዶም ዘመን እንደነበረ፡ የሰው ልጅ በሚመጣበት ጊዜም እንዲሁ ይሆናልና።” አሁን ሰዶምን ተመልከቱ፡ እንዴት እንደነበረችና፡ ምን እንደተፈጠረ። ኢየሱስ ክርስቶስም ዛሬ በቤተክርስቲያኑ ውስጥ፡ በአካል መልክ ተገልጦ፡ አያችሁ፡ ያንኑ ነገር፡ ያንኑ ሥራ፡ ሁልጊዜ ሲያደርጋቸው የነበሩትን እነዚያኑ ነገሮች እያደረገ ነው፡ መቼም የማይለወጠው፡ ዘላለማዊው እርሱ ነው። አያችሁ? ዛሬም በምድር ላይ፡ ራሱን በሰው አካላት፡ በጠራቸው በእኛ በሰው አካላት ውስጥ ገልጧል፡ እንዲሁም

በጥንት ዘመናትና በምድር ላይ በሥጋ በነበረበት ጊዜ፡ ያደረገውን ያንኑ ነገር በትክክል እያደረገ ነው። ዛሬም ያንኑ ነገር እያደረገ ነው፡ ምክንያቱም፡ “ከጥንት ጀምሮ እግዚአብሔር በብዙ ዓይነት ለአባቶቻችን በነቢያት ተናግሮ፡ በዚህ በመጨረሻው ዘመን፡ በልጁ በኢየሱስ ክርስቶስ ተናገረን” ይላልና። እያችሁ፡ ወልድ በመጨረሻው ዘመን ሲገለጥ፡ በሰው ሥጋ የተገለጠው እግዚአብሔር፡ ከሰዶም ጥፋት ጥቂት ቀደም ብሎ፡ የአሕዛብ ዓለም ፍጻሜ ላይ ተቀምጧል። ይህንን እያችሁት?

ሦስት መገለጦች አሉ።

142 አሁን፡ ቀጣዩ የሚሆነው ነገር፡ ጌታ ኢየሱስ በአካል በሚመለሰበት ጊዜ፡ ሁሉም በአንዱ አካል፡ በኢየሱስ ክርስቶስ፡ በሙሽራይቱና በአካሉ ውስጥ ሲሰበሰብ ነው። ሦስቱን ጊዜያቱን ሲያደርግ... ወደ ምድር በመጣ ጊዜ፡ ተገደለ፡ ተሰቀለ፡ ተነሳ። ራሱንም ሙሽራው በሆነችው፡ ሴት፡ በአካሉ መልክ እየገለጠ ነው። ተረዳችሁን? የእርሱ አካል ክፍል ናት።

ሴትና ወንድም እጅግ ተቀራራቢ ከመሆናቸው የተነሳ፡ እነርሱ... እነርሱ አንድ ናቸው። ያም ሆነ ይህ፡ ሊሆኑም ይገባል። ይኸውና ተመልከቷቸው፡ እያችሁ፡ ልክ በትክክል በተመሳሳይ ሁኔታ ተገልጠዋል። እሷ ከእርሱ ውስጥ ስለተወሰደች፡ የእርሱ ክፍል ናት።

ዛሬም ሙሽራይቱ ከክርስቶስ አካል የተወሰደች ናት፡ እሷም ለዚህ ዘመን ታደርገዋለች ብሎ ልክ በተናገረው መንገድ በትክክል እያደረገችና እየሰራች ነው፡ ሙሽራይቱ፡ ንግሥቲቱ፥ ንጉሡና ንግሥቲቱ። መልካም።

አሁን ጊዜ እየረፈደብን ነው፡ ስለዚህ ፈጥነን መጨረስ አለብን።

143 መልካም፡ መላው መጽሐፍ ቅዱስ ሙሉው የኢየሱስ ክርስቶስ መገለጥ ነው፡ ለየዘመኑ ሁሉ ራሱን ያሳወቀበት ነው። በሉተር ዘመን ራሱን፡ እንደ መሠረት አሳወቀ፥ ቤተክርስቲያን፡ እግሩ፡ እግሮቹ።

በንጉሥ ናቡከደነፆር ላይ እንዳደረገው ማለት ነው፥ እርሱ እነዚያን ህልሞች እንዴት እንዳለመና፡ ከራሱ ጀምሮ ቁልቁል እንዴት እንደወረደ ታስታውሳላችሁ? እያችሁ? አሁን እርሱ ከእግሮቹ ጀምሮ ወደ ላይ ይወጣል። እያችሁ? በባቢሎን መንግሥት ውስጥ እነዚያን የብሉይ ኪዳን ነገሮች ሁሉ አሳየ፡ እግዚአብሔር ራሱ በመሰላሉ ግርጌ ሥጋ እስከሚሆን ድረስ፡ ከላይ ከራስጌው ጀምሮ ወረደ። አሁን እዚህ በአዲስ ኪዳን ውስጥ ደግሞ፡ ዳግመኛ ዘውድ ሊጫንበት ወደ ራሱ፡ የወርቅ ራስ፡ ወደሆነው፡ ወደ ላይ ራሱን ዳግመኛ ያወጣል። እያችሁ? ተመልከቱ። ተረዳችሁ?

እያችሁ፡ በመጀመሪያ እግዚአብሔር ነበረ፡ ከዚያም በነቢያት፡ ቁልቁል፡ እየወረደ መጣ፡ እግዚአብሔር ራሱ ልክ እንደ እኛ ሰው ሆኖ፡ ሙሉ በሙሉ በደረጃው ግርጌ ላይ እስኪደርስ ድረስ፡ በበረት የተወለደ ህፃን ሆነ፥ የተጠላ፡ የተገፋ፡ የተናቀና፡ መጥፎ ስም የተሰጠው፡ እርሱ የነበረውን ሁሉ ሆነ። ከዚያም መነሳት ጀመረ፡ እያችሁ፡ ከእግሮቹም ጀምሮ ቤተክርስቲያንን፡ ሙሽራይቱን መገንባት ጀመረ፡ እየተመለሰ፡ መጣ፥ አሁን ደግሞ ሁሉም በአንድ ላይ ወደሚገጣጠሙበትና፡ ያንን አንድ ታላቅ ክብር የተላበሰውን የኢየሱስ ክርስቶስን አካል ወደሚያደርጉት ወደ ማዕዘኑ ራስ ድንጋይ በመምጣት ላይ ነው።

144 እግዚአብሔር በየዘመኑ ሁሉ ለዚያ ዘመን በተሰጠው ተስፋ ቃል ይገለጣል። አሁን በእነዚህ የመጨረሻ ቃላት እየጨረስን ሳለ፡ ለዛሬ ከተሰጡት የተስፋ ቃሎቹ መካከል አንዳንዶቹ ምን እንደሆኑ እስቲ እንመልከት።

145 አሁን እግዚአብሔር በማታው ብርሃን ጊዜ ራሱን እየገለጠ ነው። እስቲ አሁን እንመልከት። እናያለን...

146 እዚህ የጻፍኳቸው ብዙ የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎች አሉ። በዚህ ገጽ ላይ እንደምታዩት፡ ስንት የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎች እዚያ ላይ እንደተጻፉ ታያላችሁ። ነገር ግን፡ አሥራ ሁለት ሰዓት ሊሆን አሥራ አምስት ደቂቃ ገደማ ነው የቀረው። ወደ ውጪ መውጣት እፈልጋለሁ። ዛሬ ጠዋት፡ በመናገሬ፡ ድምፄ አልተዘጋም። አንዳንዴ እዚህ ያሉት የአየር ማቀዝቀዣዎች ድምፄን ያዘጉታል።

ስለዚህ ወንድም ኔቪል... ዛሬ ማታ የምታካፍለው አንዳች ነገር የለህም? [ወንድም ኔቪል፡ "የለም" አለ።—አርታዒ።] መልካም፡ መልካም፡ እኔ... ፈቃዳችሁ ከሆነ፡ አንዲት ነገር አለችኝ። በቀደም ጫካ ውስጥ፡ አንድ የሲጋራ ባዶ ፓኬት፡ ወድቆ አገኘሁ፥ ከዚችም የሲጋራ ፓኬት፡ የጌታ ፈቃድ ቢሆን፡ ለዛሬ ማታ የሚሆን መልእክት አግኝቻለሁ። አያችሁ?

ስለዚህ፡ እነዚህን የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎች እዚህ ይዤአለሁ። ተመልሳችሁ መምጣት እንድትችሉ፡ ሰዓቱን አሳልፌ መውሰድ አልፈልግም።

147 አንዲት የሲጋራ ፓኬት አገኘሁ፡ ልንገራችሁ። መልካም። በጫካ ውስጥ እያቋረጥኩ ስሄድ፡ እዚያ አንድ የሲጋራ ፓኬት ወድቆ ነበር፡ እኔም ዝም ብዬ አልፌ ሄድኩ። "መልካም፡ አንድ ሰው ቀድሞኝ ሄዷል፡" ብዬ አሰብኩ።

አንዳች ነገርም፡ "ወደ ኋላ ተመለስና አንሳው" አለኝ።

እኔም፡ "የሲጋራ ፓኬት ላንሳ? በፍጹም" ብዬ አሰብኩ።

ያም ነገር፡ "ወደ ኋላ ተመለስና ያንን የሲጋራ ፓኬት አንሳ" አለኝ።

ተመልሼም ሰወርድ፡ አሮጌና ባዶ የሆነ ፓኬት ነበረ፡ በዚያም ላይ አንድ ነገር አየሁ። የጌታ ፈቃድ ቢሆን፡ ዛሬ ማታ፡ ስለ እርሱ እነግራችኋለሁ። መልካም።

148 አሁን ለጥቂት ደቂቃዎች ያህል፡ ስለ ምሽት ብርሃን እንናገራለን። ልክ በመዝጊያው ሰዓት፡ ፀሐይ የምትወጣበትና፡ የማታው ብርሃን የሚሆንበት ጊዜ እንደሚመጣ፡ መጽሐፍ ቅዱስ አስቀድሞ ይናገራል። ያንን ሁላችንም እናውቃለን። አይደል? እኛ፡ እኛ... ከጌታ ኢየሱስ ለመጣው ለዛሬው መልእክታችን ቅርብ የሆንን ሁላችንም፡ የማታ ብርሃን እንደሚኖር እናምናለን። ይህ የማታው ብርሃንም...

እርግጥ ነው፡ ታላቁ ብርሃን የሚመጣው ኢየሱስ ራሱ እዚህ ምድር ላይ በሚገለጥበት ጊዜ፡ ወይም ሙሽራይቱን ለመውሰድ፡ እዚያ በሰማያት ሲገለጥ ነው፡ ከዚያም የሺህ ዓመቱ መንግስት ይጀምራል።

149 ነገር ግን በሰው ልጆች ፊት ተደቅኖ ከሚያውቀው ሁሉ፡ እጅግ አስፈሪ የሆነውን ማለፍ ያለብን ጊዜ ከፊታችን አለ። እኔም ያችን ሰዓት እየጠበቅኩ ነው፡ መቼ እንደም... እያንዳንዱ ሰው ከሥራው ዕረፍት ወስዶ ጥቂት ቀናትን የሚያሳልፍበት ዕድል ሲያገኝ፡ በመጨረሻዎቹ ቀናት ስለሚወድቁት ስለ እነዚያ መቅሰፍቶችና ነገሮች መናገር የምችልበትን ሰፍራ አዘጋጅተን፥ የጌታ ፈቃድ ሆኖ በሕይወት ካቆየኝና በመንፈሱ ከገፋፋኝ፡ በሁለት ወይም ሦስት ሳምንታት፡

አንድ ላይ ወስደን ያንን ሁሉ በአንድ ላይ አምጥተን፡ እነዚያ ነገሮች እንዴት ወደ ውስጥ እንደሚገቡና፡ እነዚያ ነጎድጓዶች እንዴት እንደሚሆኑ እናያለን። ያኔ ያ ሰውና እነዚያ ሰዎች በህልማቸው ሲያዩት የነበረው ነገር ምን እንደሆነ ታውቃላችሁ፡ እነዚያ ነገሮች ሁሉ፡ በዚያ ይፈጸማሉ፥ አያችሁ፡ ያ ከሰማያት የሚወጣው ያ ታላቅ ነጎድጓድ፡ እነርሱ የ—የገለጡት ነገር ምን እንደሆነ ታስተውላላችሁ። አሁን፡ እርግጥ ነው፡ ያ—ያ ምን ማለት እንደሆነ እኔ እንደማውቅ እዚህ ያላችሁት፡ ሁላችሁም ታውቃላችሁ፡ አያችሁ። እናም፡ ጊዜው እስኪደርስ ድረስ ዝም ብለን እንጠብቅ፡ አያችሁ፡ ያ እንዲሆን፡ አያችሁ፡ አሁን፡ በወቅቱም የበለጠ ይሆናል።

150 አሁን፡ ስለዚህ እዚህ ውስጥ ካሉት ከ—ከእነዚህ የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎች አንዳንዶቹን እናነባለን። አሁን፡ የምሽት ብርሃን ሲመጣ፡ አሁን፡ በጠዋቱ ከነበረው ያው አንድ ዓይነት ብርሃን መሆን እንዳለበት እናስተውላለን።

ምክንያቱም፡ ጠዋት አንድ ፀሐይ ከሰዓት በኋላ ደግሞ ሌላ ፀሐይ የለንም። ያው አንዲት ፀሐይ ናት። ከሰዓት በኋላ ያለችው ያቺው ፀሐይ በጠዋትም ያለችው እሷው ናት፥ በጠዋት የነበረችው ከሰዓት በኋላ ካለችው ጋር ያው ናት።

አሁን፡ መጽሐፍ ቅዱስ፡ "ቀኑ ራሱ፡" በዚያ መሀል ያለው ቀን፡ "በተወሰነ መልኩ፡ ኦህ፡ ልክ እንደ ጭጋጋማና፡ ጨለማ ቀን ይሆናል። በመካከል ያለው ያ ጊዜ፡ ቀን ወይም ሌሊት ተብሎ ሊጠራ አይችልም" ይላል።

151 አያችሁ፡ ያ ከእግር ጀምሮ፡ ወደ ላይ የሚወጣው፡ የአካሉ አሰራር ነው። እዚህ ምድር ላይ በነበረበት ጊዜ፡ እርሱ ወልድ፡ ብርሃን ነበረ፡ ከዚያም ተገደለ። ቤተክርስቲያን የእርሱን ሰፍራ ወሰደች፡ ከዚያም በሰማዕትነትና በጨለማው ዘመን ውስጥ አለፈች፡ ከዚህም ወጥታ በመሠረቱ ላይ መገንባት ጀመረች። ታዲያ ማየት ከየት ይመጣል? ከራሱ አናት ላይ ነው።

ያንን ራእይ አያችሁ፥ የናቡከደነፆርን? ደሙ ስለ እነርሱ ከመፍሰሱና ማስተሰረያ ከመደረጉ በፊት፡ የአሕዛብ ዘመን ከጀመረበት ጊዜ አንስቶ ቁልቁል ሲወርድ አያችሁ። ወደ እምነቱ የገቡ አዲስ አማኞች ነበሩ። ነገር ግን በምሳሌ፡ ቀጥታ ወደ ታች፡ ወደ ታች፡ ወደ ታች ወደ ግርጌው እንደወረደ አስተውሉ፡ አያችሁ፡ ወደ ታች አወረደው።

ከዚያም ቀጥታ፡ ወደ ኋላ መመለስ ጀመረ፡ ቤተክርስቲያን ከእግሮቹ ተነስታ፡ ወደ ላይ መውጣት ጀመረች። አሁን ደግሞ የራስ ጊዜ ነው የ—የራስ ጊዜ። አሁን ብርሃኑን አስተውሉ።

152 በእጆቻችሁ ማየት አትችሉም፡ ነገር ግን የአካላችሁ ክፍል ነው። በጆሮዎች ማየት አትችሉም፡ ነገር ግን መስማት ይችላሉ። በአፍንጫ ማየት አትችሉም፡ ነገር ግን ያሸታል። በከንፈሮች ማ—ማየት አትችሉም፡ ይናገራሉ እንጂ፥ አያችሁ፡ ያ የጴንጤቆስጤ ዘመን ነበረ። አሁን ግን በዓይን ጊዜ ውስጥ ነን፡ በማየት ጊዜ። አያችሁ? አሁን፡ ከዓይን በላይ የሚንቀሳቀስ ሌላ የሰውነት ክፍል የለም። ልክ ነው?

ቀጣዩ አዕምሮ ነው፡ ያም አካሉን በሙሉ የሚቆጣጠረው፡ ክርስቶስ ራሱ ነው።

ከዚያ በላይ የሚንቀሳቀስ፡ እንቅስቃሴ የለም። አያችሁ? ሌላው ነገር ሁሉ ተንቀሳቅሷል። አያችሁ? እግሮቻችሁን ታንቀሳቅሳላችሁ፡ በእግሮቻችሁ ያሉትን ጡንቻዎች ታንቀሳቅሳላችሁ፡ ሁሉንም ነገር ታንቀሳቅሳላችሁ። የእናንተን... ጆሮዎቻችሁ ሊንቀሳቀሱ ይችላሉ፡ አፍንጫችሁ፡ ከንፈሮቻችሁና፡ የመሳሰሉት። ነገር ግን ከዓይኖቻችሁ በላይ፡ ምንም የሚንቀሳቀስ ነገር የለም።

ወንዶች ቶሎ መላጣ ይሆናሉ የሚባለውም ለዚህ ነው፡ ምክንያቱም፡ አያችሁ፡ በ—በጸጉር ውስጥ፡ በጭንቅላት ቆዳ ውስጥ ያሉትን ጡንቻዎች የሚያዳብር ምንም እንቅስቃሴ የለምና። አያችሁ? ደሙ ወደዚያ መድረስ የሚችልበት ማለስለሻ የለውም። ደሙ አይረጭም፡ አያችሁ፡ ወደ ላይ ወጥቶ ደም አያቀርብም። እርግጥ ነው፥ የ—የጸጉር ስር በደም ነው የሚኖረው።

አሁን ያ ክፍል፡ አያችሁ፡ ከዓይን በላይ ሌላ ምንም ነገር እንደሌለ ደርሰንበታል።

153 አሁን እስቲ እንመልከት። "ብርሃን ይሆናል" (በቀን መሀል አካባቢ ነው? ) "በማታ ጊዜ!" ብርሃን ለምን ተላከ? እናንተ የት... እንዴት መጓዝ እንዳለባችሁ ማየት እንድትችሉ ነው። ልክ ነው? የት እንዳላችሁ እንዲታዩ። "ሰመሽ ብርሃን ይሆናል።"

154 አሁን፡ ይህንን ወስደን በሚልክያስ 4 ላይ ካለው ጋር እናነጻጽረው። ሰመሽ ብርሃን ዳግመኛ እንደሚመጣ ተስፋ ሰጥቷል፡ አያችሁ፡ "ምክንያቱም፡ እነሆ፡ ነቢዩን ኤልያስን እልክላችኋለሁ፡ እርሱም የ—የልጆችን ልብ ወደ አባቶች፡ የአባቶችንም ልብ ወደ ልጆች ይመልሳል፥" (ልክ ነው? ) "መጥቼም ምድርን በእርግማን እንዳልመታ።"

155 አሁን ዮሐንስን ወይም... የሉቃስ ወንጌል 17፥30ን እንውሰድ፡ ኢየሱስም በዚያ የተነበየውን እንመልከት፡ እንዲህ አለ፡ "በሰዶም ዘመን እንደነበረ፡ እንዲሁ ይሆናል... "

አሁን አስታውሱ፡ አስተውሉ፡ ይህ የሰው ልጅ የሚገለጥበት ጊዜ ነው፥ የሰው ልጅ መገለጥ። አሁን፡ የሰው ልጅ ሰዶም ከመቃጠሏ ጥቂት ቀደም ብሎ፡ ለጥቂት ጊዜያት፡ በዚያ እንደ መያዣ በእውነት ተገልጦ ነበረ። አሁን፡ ያ ሰው ኤሎሂም ነበረ። ያ እግዚአብሔር ነበረ፥ ኢየሱስም እግዚአብሔር ነው። እግዚአብሔርም በምርመራው ፍርድ ላይ፡ አብርሃምን ለማነጋገር፡ ለጥቂት ጊዜያት እንደ ቅድመ ማሳያ በዚያ ተገልጦ ነበረ። ለጥቂት ጊዜ ያህል፡ የሰው ልጅ ተገለጠ፡ የሰው ልጅ፥ ኤሎሂም። ቤተክርስቲያን፡ አያችሁት? [ጉባኤው፡ "አሜን" አለ።—አርታዒ።] የሰው ልጅ፡ ኤሎሂም፡ ለጥቂት ደቂቃዎች ብቻ ተገለጠ። ምክንያቱም፡ በማግስቱ ጠዋት ተቃጠለች፡ (መቼ? ) ፀሐይ ዳግመኛ ከመውጣቷ በፊት።

ስለዚህ የሚቀር ምንም ድርጅት ሊኖር አይችልም፡ እንዲሁም አሁን እየሆነ ካለው የላቀ ሌላ መሻሻል ሊኖር አይችልም፡ ምክንያቱም ቀኑ ዳግመኛ ሳይነጋ እሷ ትቃጠላለችና። በመላው ሀገሪቱ፡ መነቃቃት አብቅቷል። ከእንግዲህ ምንም መነቃቃቶች አይኖሩም፡ ሀገር አቋራጭ የሆኑ ታላላቅ መነቃቃቶች አይኖሩም፥ ይህች ሀገር ፈጽሞ አትቀበለውም። የምሁራን ስብሰብ ሊኖራችሁ ይችላል። ነገር ግን፡ መንፈሳዊ መነቃቃትን፡ ማለቴ ነው፡ የነበረውን ሁሉ

አይተነዋል። እየገባችሁ እንደሆነ ተስፋ አደርጋለሁ። ይህንን እየተናገርኩ ያለሁት እንደሚገባችሁ ተ—ተስፋ በማድረግ ነው። አያችሁ? አብቅቷል።

ከጥቂት ጊዜ በፊት፡ አንድ ጥሩ አገልጋይ፡ እንዲህ አለኝ፡ "ወንድም ብራንሃም፡ የጌታን ደስታ በልቤ ውስጥ ማግኘት ብቻ ብችል ኖሮ!"

እኔም፡ "ልጄ፡ መነቃቃቱኮ አብቅቷል" አልኩት። አያችሁ?

156 አሁን በመርከቧ ላይ ሚዛን ጠባቂዎች ተገጥመዋል። ታላላቅና አስፈሪ ማዕበሎች ከፊታችን አሉ፥ ነገር ግን ከዚያ ማዕበል ባሻገር፡ ወደ ዳርቻው እየተቃረብን እንደሆነ፡ እናውቃለን። አያችሁ? ወደ ዳርቻው እየተቃረብን ነው። ዝም ብላችሁ ተረጋግታችሁ ቁሙ። ቃሉ ውስጥ ጸንታችሁ ቁሙ። ከእግዚአብሔር ጋር ቁሙ። ምንም ዓይነት ስሜት ቢሰማችሁም፡ ወይም ሌላ ማንኛውም ነገር ቢሆን፥ ልክ በቃሉ ውስጥ ጸንታችሁ ቁሙ። በ—በ—በዙሪያችን ያሉትን፡ እነዚህን ታላላቅ ደመናዎችን፡ እየመጣ ያለውን ማዕበል፡ የአቶሚክ ቦምቦችንና፡ ስለ እነርሱ የሚያወሩትን ሌላውንም ነገር ሁሉ ስታዩ ተረጋግታችሁ ቁሙ። የኛ ሚዛን ጠባቂ ግን በቀጥታ ቃሉ ውስጥ ነው። እግዚአብሔር እዚህ እንደሚሆን ተናግሯል፥ እያንዳንዳቸውንም በማዕበሉ አናት ላይ ጥሰን እናልፋለን። አዎ፡ ቀጥታ በአናታቸው ላይ እናልፋለን። አዎን፡ በእርግጠኝነት! እነርሱ፡ ሊያሰምጡን አይችሉም። ሊያፍኑን አይችሉም። በመቃብር ውስጥ ብታስገቡን፥ ዳግመኛ እንወጣለን። ነገሩ ይኸው ነው በቃ። እዚያ በታች ሊያስቀረን የሚችል ምንም ምድራዊ ኃይል የለም። እያንዳንዳቸውን ጥሰን እናልፋለን፡ ምክንያቱም ታላቁ ዋነኛ አዛዣችን ከማዶ ሆኖ እየጠራን ነውና።

በኢየሱስ ላይ መልህቄን ጥያለሁ፡ የሕይወትን ማዕበል
 እጋፈጣለሁ፥
በኢየሱስ ላይ መልህቄን ጥያለሁ፡ ምንም ዓይነት ንፋስ
 ወይም ማዕበል አልፈራም፥

157 ምንም ቢሆን፡ ይምጣ። ምንም ቢሆን፡ ምንም ቢመጣ፡ ምንም ለውጥ አያመጣም። ልክ እዚያው በኢየሱስ ላይ መልህቃችንን ጥለናል። ብኖር፡ ለእግዚአብሔር ክብር እኖራለሁ። ብሞትም፡ ለእግዚአብሔር ክብር እሞታለሁ። ማ—ማ—ማድረግ የምፈልገው... ለእግዚአብሔር ክብር፡ የሆነውን ነገር ብቻ ነው። ያ ሁሉ ሲያበቃ፡ ከእንግዲህ ወዲህ መቆየት አልፈልግም። ወደዚያ... እርሱ ወደገዛልኝ ሽልማት መሄድ እፈልጋለሁ፥ እኔ በላቤ ወደሰራሁት ሳይሆን፡ እርሱ ወደገዛልኝ፡ በጸጋው ወደሰጠኝ ነገር መሄድ እፈልጋለሁ።

158 ስለዚህ የማታው ብርሃን እዚህ እንደሆነ እናያለን። በብርሃኑ ውስጥ እንዴት መመላለስ እንዳለባችሁ የሚያዩ ዓይኖች ከሌሏችሁ፡ ብርሃን መኖሩ ምን ይጠቅማል? የምሽቱ ብርሃን ምንድን ነው? ብርሃን የሚመጣው፡ አንዳች ነገርን ሊገልጥ ነው። ልክ ነው? **እዚህ** በጨለማ ውስጥ፡ አንዳች ነገር ቢኖርና፡ እየተሰማችሁ ምን እንደሆነ መረዳት ካልቻላችሁ፡ መብራት ታበራላችሁ። ሊገልጥ ነው! ሚልክያስ 4 የሚያደርገው ምንድን ነው? አያችሁ? ያንኑ ነገር ነው የሚያደርገው። እነዚህ ሁሉ የሐይማኖት ተቋማት እየተደናቀፉበት ባለው፡ በዚህ ውስጥ... ?... የሰባቱ ማኅተሞች መከፈት ለምን ነበር፡ ሊገልጥ ወደ

ውጪ ሊያወጣው ነው። ዓይኖች ከሌሏችሁ፡ መገለጡ ምን ጥቅም አለው? በመጀመሪያ፡ ለማየት፡ ዓይኖች ሊኖሩ ይገባል። ልክ ነው? ሚልክያስ 4ን ሊገልጥ፡ ሉቃስ 17÷30ን፡ ዮሐንስ 14÷12ን፡ እንዲሁም ዮሐንስ 15÷24ን፡ 16÷13ን ሊገልጥ። እንዲሁም ራእይ 10÷1-7ን ሊገልጥ፡ የሰባቱን ማኅተሞች መከፈትና፡ የሰባተኛውን መልአክ መልእክት ሊገልጥ፥ የምሽት ብርሃን በመጣ ጊዜ፡ ሊከፍትና፡ ሊገልጥ ነው። አሁን አንድ ሰው...

159 በሎዶቅያ ዘመን፡ ሕዝቡ (ምን?) "ራቁታቸውን" ነበሩ። ናቸውን? "ዕውሮች።" ለእውር ሰው ብርሃን ምን ይጠቅመዋል? ዕውር ዕውርን ቢመራው፡ ሁለቱም ጉድጓድ ውስጥ አይወድቁምን? "ራቁታቸውን፡ ዕውሮች፡ ይህንንም እንኳ አያውቁም።" የአዕምሮ ህዋሳቶቻቸው እንኳን ጠፍተዋል፡ አዕምሯዊና መንፈሳዊ ማስተዋል ጠፍቷል። አያችሁ?

"ትዕቢተኞች፡ በትዕቢት የተነፉ፡ ከእግዚአብሔር ይልቅ ተድላን የሚወዱ፥ ውል አፍራሾች፡ ሐሜተኞች፡ ራሳቸውን የማይገዙ፡ መልካም የሆነውን የማይወዱ፥ የአምልኮት መልክ አላቸው፡ ኃይሉን ግን ክደዋል።" የመገለጥን ኃይል፥ በእርሱ እንኳ አያምኑም። አያችሁ? እንደ ነቢያት ባሉ ነገሮች አያምኑም። ስለዚህ አያምኑበትም። ሚልክያስ 4 አ—አንዲት የተወሰነች ቤተክርስቲያን ወይም የተወሰነ ድርጅት ይሆናል ብለው ያምናሉ።

ለመጀመሪያ ጊዜ ሲመጣ፡ ሰው ነበረ። ለሁለተኛ ጊዜ፡ በእጥፍ መንፈስ ሲመጣ፡ ሰው ነበረ። በመጥምቁ ዮሐንስ መልክ ሲመጣም፡ ሰው ነበረ። አያችሁ?

በመጨረሻዎቹ ቀናት፡ የምሽት ብርሃን ማብራት ሲጀምር፡ ዓይኖች ይከፈታሉ ወዴት እየሄዳችሁ እንዳላችሁም ታያላችሁ። ከዚያም አካሉ አስቀድሞ ተሰርቷል፡ በእግሮቹ ቆሟል፡ እየተንቀሳቀሰ ነው፡ በመንፈስ ቅዱስም ይመራል። ምንድን ነው? መጽሐፍ ቅዱስን የጻፉትን ነቢያት ሲመራ የነበረው ያው እርሱ፡ በመንፈስ ቅዱስ በተሞላ አካል ውስጥ የሚንቀሳቀሰው፡ ያው መንፈስ ቅዱስ ነው፡ ከየትኛውም ድርጅት፡ ከየወገኑ፡ ከቋንቋውና፡ ከሕዝቡ ሁሉ ወጥቶ በመንፈስ ቅዱስ ተመርቷል።

160 እዚች አንዲት እህት አለች፡ የዚህ ድርጅት፡ ወይም የዚህ ድርጅት... የዚህ ጉባኤ አባል አይደለችም። የመጣችው ከሌላ ሰፍራ ነው፡ ዛሬ ጠዋትም ስትመጣ፡ አንድ ፎቶ ይዛ ነበር። ያንንም... እጅግ ለተደነቀው፡ ለልጄ ሰጠችው። ስለዚህ ጉዳይ ሰምታ እንደሆነ ወይም እንዳልሆነ አላውቅም። እኔ አላውቅም። ሰባቱ ማኅተሞች በዚያ በተከፈቱበት ጊዜ፡ ይህ ሲሆን፡ በሰባቱ የቤተክርስቲያን ዘመናት ላይ፡ የነበረውን፡ የዚህን የጌታ መልአክ ፎቶ ይዛ ነበር። ወደዚያ ወደ ኋላ ስትመለከት፡ በሰማይ ቆሞ እንዳለ በሕልሟ እንዳየችው፡ ተናገረች። እሷም ወደ ኋላ ስትመለከት፡ አንድ ነጭ የለበሰ ሰው፡ ወደ ፊት ሲዘምት አየች፥ ከኋላው ደግሞ፡ በመመልከት... እንዲህ አለች፡ "ወንድም ብራንሃም፡ እርሱ አንተ ነበርክ" አለች። እንዲህም አለች፡ "በዚያ ሲዘምቱ፡" እንዲህ አለች፡ "ከአንተ ኋላ፡ የተለያዩ ቀለማት ያላቸው ሰዎች፡ ባንዲራዎችን ይዘው፥ ከጆርጂያ፡ ከአላባማና፡ ከተለያዩ ሰፍራዎች ሁሉ መጥተው፡ ወደ ፊት ይዘምቱ ነበር" አለች፡ በራእዩ ውስጥ ክርስቶስ ወደሚገለጥበት ራስነት እየመጡ ነበር። ኦህ፡ ሃሌሉያ!

161 በመጨረሻዎቹ ቀናት ውስጥ ነን፡ እንዲሁም በቀኖቹ የመጨረሻ ሰዓታት ውስጥ ነን። አሁን እርሱን በቃሉ ውስጥ ታዩታላችሁን፡ ቃሉም ሁሉ ልክ እዚህ ከፊታችን ሲገለጥ ታያላችሁን? ኦህ፡ የሕያው እግዚአብሔር ቤተክርስቲያን ሆይ፡ በእግራችሁ ቁሙ፡ በሙሉ ኃይላችሁም እመኑት። በመንኮራኩሩ መካከል ያለውን ያንን ትንሽ መንኮራኩር አጥብቃችሁ ያዙ፡ እርሱም የምታደርጉትን እያንዳንዱን እርምጃና እንቅስቃሴ የተረጋጋ እንዲሆን ያድርገው። ያላችሁ እያንዳንዱ ሀሳብ፡ በውስጣችሁ ባለው በዚህ ግንብ ይቆጣጠር። ምክንያቱም፡ እግዚአብሔር ብርሃኑን እያሳየ፡ በምሽቱ ብርሃን ውስጥ፡ ለዚህች ሰዓት በተሰጠው በገዛ ቃሉ ውስጥ ተቀምጧልና።

162 የሌሊት ወፍ ዕውርነት! መብራት ብታበሩ፡ የ—የሌሊት ወፏ እጅግ ዕውር ከመሆኗ የተነሳ መብረር አትችልም። ጉጉት፡ እነዚያ በሌሊት የሚንቀሳቀሱ ሁሉ፡ እንደዚያ ያሉ ነገሮች፡ በረሮዎችና ነገሮች፡ በቀን ውስጥ ማየት አይችሉም። ነገሩ ሁሉ ምን እንደሆነ አያውቁም። ማየት አይችሉም።

የምሽት ብርሃን መጥቷል። እያንዳንዱ ምሳሌ፡ በምንሄድበት ሰፍራ ሁሉ፡ ወደ ተፈጥሮ፡ ወደ መጽሐፍ ቅዱስ፡ ወደ መ—መልከ-... ዳንኤል ወዳየው ሐውልት፡ የ—የዚያ ዘመን ንጉሥ፡ ሁሉም ወዳዩት፥ እነዚህ ነገሮች ሁሉ፡ ሁሉም ሰው፡ እያንዳንዱ መልክ፡ እያንዳንዱ እንቅስቃሴ፡ በአካሉ ውስጥ ያለው እያንዳንዱ ሰፍራ፡ እየኖርንበት ያለውን ልክ ይህንኑ ሰዓት በሰፍራው ያሳየናል። ከእርሱ በላይ ሊመጣ የሚችል ሌላ እንቅስቃሴ የለም።

የእጅ እንቅስቃሴ ነበረ፥ ፍቅር፡ ዌስሊ። የመሠረት፡ እንቅስቃሴ ነበረ፥ ሉተር። ፍቅር፡ ከዚያ የሚበልጥ መቼም አልነበረም፥ የዌስሊ እንቅስቃሴ ተብሎ ይጠራ ነበር። ወደ ዓለም ሁሉ ሚሲዮናውያንን ልከው ነበር። ከዚያ ዘመን በፊት ከተደረጉት፡ ታላላቅ እንቅስቃሴዎች አንዱ ነበረ።

ከዚያም የጴንጤቆስጤ ዘመን መጣ፥ ከዚያም የተለያዩት ጣቶችና ነገሮች ገቡ፡ የጴንጤቆስጤ ዘመን፡ የልሳናት፡ የአፍንጫና፡ የመሳሰሉት።

አሁን ደግሞ በዓይኖች ላይ ነው። ለማየት የሚያስችሉ ዓይኖች ከሌሉ፡ ዓይኖች፡ ወይም ብርሃን ምን ይጠቅማል? ለማየት፡ በመጀመሪያ፡ ዓይኖች ሊኖሩ ይገባል። ያ ሲመጣ፡ ሰባቱን ማኅተሞች ከፈተ የማታውንም ብርሃን ገለጠ፡ በእነዚህ የቤተክርስቲያን ዘመናት ሁሉ ተሰውረው የነበሩትን ምስጢራት ሁሉ በመውሰድ፡ በራእይ 10፥1-7 ላይ አደርገዋለሁ ብሎ ተስፋ በሰጠው መሰረት አሁን ገለጣቸው። ዛሬ እኛ እዚህ በቃሉ መካከል ተቀምጠናል፡ ቃሉም በኢየሱስ ክርስቶስ እየተገለጠልን ነው። ስለዚህ፡ **ይህ** የእግዚአብሔር ቃል ነው።

163 ለእርሱም የተገዛን በመሆን፡ እንረዳው ዘንድ፡ ይገለጥልንም ዘንድ፡ ወደ ደራሲው ተጠግተን መራመድ አለብን። "ጌታ ሆይ፡ ምን አደርግ ዘንድ፡ ትወዳለህ? ወደ መስክ ወጥቼ ወንጌልን መስበክ አለብኝን፡ ወይስ እቤቴ መቆየት አለብኝ? ምንም ቢሆን፡ ጥሩ የቤት እመቤት መሆን ካለብኝ፡ ጥሩ እናት መሆን ካለብኝ፡ **ይህንን**፡ **ያንን**፡ ወይም **ሌላውን** ማድረግ ካለብኝ? ምንም ይሁን ምን፡ ገበሬ መሆን ካለብኝ፡ እኔ... ምንም ቢሆን፡ ጌታ ሆይ፡ ምን እንዳደርግ ትወዳለህ? "

164 ሳውል እዚያ ጋ፡ "ጌታ ሆይ፡ ምን አደርግ ዘንድ ትወዳለህ፡" ብሎ የጮኸው ይህንኑ አልነበረምን? እርሱም ቤተ-... ቤተክርስቲያንን ሁሉ ወኅኒ ውስጥ ለ—ለመክተት በመንገድ ላይ ሳለ ነበረ። ነገር ግን ከዚያም፡ "ምን አደርግ ዘንድ ትወዳለህ" ብሎ ጮኸ? ታላቅ የእሳት ዓምድ ሆኖ፡ ብርሃኑ በላዩ ላይ ባበራ ጊዜ። "ምን አደርግ ዘንድ ትወዳለህ? "

165 በመዝጊያችን ላይ እንዲህ ማለት፡ መልካም ቃል ይመስለኛል፡ "ጌታ ሆይ፡ ምን አደርግ ዘንድ ትወዳለህ? ይህ መጽሐፍ ቅዱስ ልክ አሁን እንዲህ ፍጹም በሆነ ሁኔታ ሲገለጥ ሳየው፡ ጌታ ሆይ፡ ምን አደርግ ዘንድ ትወዳለህ? "

ራሳችንን ዝቅ እናድርግ።

166 እዚህ ያላችሁ እያንዳንዳችሁ አሁን ልባችሁን እንድትመረምሩና፡ "ጌታ ሆይ፡ ምን አደርግ ዘንድ ትወዳለህ" የሚለውን ያንን ጥያቄ እንድትጠይቁ እጠይቃችኋለሁ? እናንተም ሰዎች፡ በመላው ሀገሪቱ አሁንም በስልክ መስመር ላይ ያላችሁ፡ ራሳችሁን ዝቅ አድርጋችሁ፡ "ጌታ ሆይ፡ ምን አደርግ ዘንድ ትወዳለህ? እዚህ በመጨረሻዎቹ ቀናትና በመጨረሻዎቹ ሰዓታት ውስጥ መሆናችንን እያየን፡ ይህ ልክ ከፊታችን ይህን ያህል ፍጹም በሆነ ሁኔታ፡ በግልጽ እየተገለጠልን ሳለ፡ ምን አደርግ ዘንድ ትወዳለህ" ብላችሁ ጠይቁ?

167 ውድ አምላክ ሆይ፡ እነርሱ ያንን ጥያቄ እየጠየቁህ ሳሉ፥ እያንዳንዱ ቀን፡ ዋጋ ሊኖረው እንደሚገባ ስለምገነዘብ፡ እኔም ራሴ፡ ጌታ ሆይ፡ ምን አደርግ ዘንድ ትወዳለህ ብዬ፡ እጠይቅሃለሁ። ጌታ ሆይ፡ እያንዳንዱ ቀን ለአንተ ክብርና ምስጋና ሆኖ እንዲቆጠር፡ መኖር እችል ዘንድ፡ እንድትረዳኝ እጸልያለሁ።

በመላው አገሪቱ ያሉትን እንዲሁም በተበርናክሉ ውስጥ የተገኙትን ሁሉ፡ እንድትረዳ እጸልያለሁ ልባችንን እየመረመርንም እንዲህ እንላለን፡ "ጌታ ሆይ፡ ምን አደርግ ዘንድ ትወዳለህ? ጌታ ሆይ፡ መንግሥትህንና ዓላማህን ይበልጥ ለማስፋፋት፡ ምን ላድርግ? " አምላክ ሆይ፡ ይህንን ፈጽምልን።

አቤቱ፡ ልባችንንም መርምር፡ ፈትነንም። ጌታ ሆይ፡ በእኛ ውስጥ አንዳች በደል ቢኖር፡ አንዳች ራስ ወዳድነት፡ አንዳች መጥፎ የልብ ሀሳብ ወይም ዓላማ ቢኖር፡ አምላክ ሆይ፡ በሞቱና፡ በትንሣኤው ያደረገውን ማስተሰረያ፡ በትሕትና በምንቀበልለት በልጅህ በኢየሱስ ክርስቶስ ደም አንጻን። ይህንንም እንዳደረገ በማመን ጸድቀን፡ አንተ የሰጠኸንን፡ ለእኛ የሰጠኸንን የደህንነት እቅድ በደስታ እንቀበላለን።

አባት ሆይ፡ ስለምናምነውና አጥብቀንም ስለምንይዘው፡ ቃልህና መልእክትህ መሆኑን አውቀን ስለምናምንበት፡ ስለ ዛሬው መልእክት እናመሰግንሃለን። ይህን የምናደርገው ከሌሎች ሰዎች የተለየን ለመሆን ሳይሆን፡ ምሳሌያችን የሆነውን ኢየሱስ ክርስቶስን ይበልጥ ለመምሰል በመጣር ነው።

168 ውድ አምላክ ሆይ፡ እዚህ የተቀመጡ መሀረቦች አሉ፡ በየቦታውም ታማሚዎች አሉ። ጌታ ሆይ፡ እኔ ራሴም፡ ዛሬ ጠዋት፡ ደክሞኛል አቅምም አንሶኛል። ውድ አምላክ ሆይ፡ እንድትረዳን እጸልያለሁ። ለብርታት ወደ አንተ እንመለከታለን። ብርታታችን አንተ ነህ። ውድ አምላክ ሆይ፡ እጅግ ብዙዎችን ረድተሃል።

169 በቀደም፡ ልቡ እጅግ ከመታመሙ የተነሳ፡ መንቀሳቀስ ተሰኖት በነበረበት ጊዜ፡ ሐኪሞቹ... እዚያ ጫካ ውስጥ ከወንድም ባንክስ ውድ ጋር እየተራመድኩ ሳለሁ ያንን አሰብ ነበር። ከዚያም ከዚያ ራእይ በኋላ በነዚያ ተራራዎች ላይ ሰጓዝ፡ እኔ ምን ያህል... ትንሽ እንዳወቅኩ ሳሰብ፡ "ያንን አንበሳ ማግኘት አለብኝ። ያ አንበሳ ሲገደል ማየት አለብኝ" አልኩ።

ከዚያም ወደዚያ ወርጄ፡ ቱክሰን ውስጥ፡ ፈርስ ካፍቴሪያ ላይ ቆሜ ሳለሁ፡ ልብሶቹ ሁሉ ሰውነቱ ላይ ተንጠልጥለው፡ ዓይኖቹም ወደ ታች ወርደው አየሁ። እኔም፡ "እግዚአብሔር ሆይ፡ አንበሳ የት እንዳለ በራእይ ማሳየት ከቻልክ፡ በእርግጥም ስለ ወንድም ውድም ማሳየት ትችላለህ" አልኩ።

ከዚያም፡ "እጆችህን ጫንበት" የሚል መጣ።

እነሆ ዛሬ ተመልሷል፡ ዳግመኛ፡ ወንድማችን ባንክስ ሆኗል፡ በርትቶ፡ በነዚያ ተራሮች ላይ ወደ ላይ-እና-ወደ ታች ይሮጣል። ውድ አምላክ ሆይ፡ እንዴት እናመሰግንሃለን። ለወንድም ውድ የሆንክለት ያው አምላክ፡ ለሁላችንም ያው ነህ። እውነተኛና ቅን የሆነ፡ አገልጋይህ ስለሆነ፡ እንደምትወደው አውቃለሁ።

170 ውድ አምላክ ሆይ፡ ከእያንዳንዳችን ጋር እንድትገናኝ፡ ኃጢአቶቻችንንም፡ ይቅር እንድትልና፡ የሥጋችንንም ደዌ እንድትፈውስ እጸልያለሁ። ጌታ ሆይ፡ ወደዚያ ወደ ሙሉው የኢየሱስ ክርስቶስ ሙላት እስክንደርስ ድረስ፡ ከዕለት ወደ ዕለት፡ ይበልጥ አንተን እንድንመስል አድርገን። ጌታ ሆይ፡ ይህ ይሁንልን። አሁን እያንዳንዱን ልብ እንደመረመርክ አምናለሁ፡ ምን ማድረግ እንዳለብንም እናውቃለን። አሁን በኢየሱስ ስም እንድትባርከን እንጠይቅሃለን።

171 ራሳችንን ዝቅ አድርገን ሳለን፡ እዚህ ያላችሁ፡ ወይም በ—በመላው ሀገሪቱ በስልክ መስመር ላይ ያላችሁ፡ እየጸለያችሁና፡ ራሳችሁን ዝቅ አድርጋችሁ ሳለ፡ አሁን እጃችሁን ወደ እግዚአብሔር ከፍ ማድረግ፡ የምትፈልጉ አላችሁን? ልታደርጉ የምትችሉት ያንን ብቻ ነው፥ ዛሬ ጠዋት እዚህ ቦታው ጠቧል። ዝም ብላችሁ እጃችሁን ወደ እግዚአብሔር ከፍ አድርጋችሁ፡ "እግዚአብሔር ሆይ፡ ይበልጥ ኢየሱስን እንድመስል አድርገኝ። ይ—ይበልጥ ኢየሱስን መምሰል እፈልጋለሁ፡" በሉ። እግዚአብሔር ይባርካችሁ። በመላው ሀገሪቱ ባሉ ስፍራዎች ሁሉ፡ እጆች በየቦታው ተነስተዋል፡ በእርግጥም እጅግ ብዙ ህዝብ ነው። የእኔም፡ እጅ ተነስቷል። "ይበልጥ እርሱን መምሰል እፈልጋለሁ። ጌታ ሆይ፡ መርምረኝ፡ በእኔ ውስጥ አንዳች ክፉ ነገር ቢገኝ፥ አውጣልኝ። እ—እፈልጋለሁ... " ምን? እዚህ የምንቆየው ለተወሰነ ጊዜ ብቻ ነው፡ ነገር ግን ማንም ብትሆኑ... ምንም ያህል ሀብታም፡ ምንም ያህል ድሀ፡ ምንም ያህል፡ ወጣት፡ ወይም አዛውንት ብትሆኑ፡ መሄዳችን አይቀርም።

172 ትላንትና እዚያ ተራራ ላይ፡ ወንዝ ዳር... ም—ምስኪን ድሀ ቤተሰብ ጋር፡ ቆሜ ነበር። በዚያ አንድ ትንሽ ቤተሰብ ነበር፡ ስለ እግዚአብሔር ለረጅም ጊዜ፡ ስነግረው የነበረ አንድ ሰው። ወደ ታች ሰወርድ፡ ምስኪኗ ሚስቱ፡ ሰባት ወይም ስምንት ልጆች፥ እርሱም፡ ትንሹና ቀጭኑ ሰው፡ በቀን ሁለት ዶላር ለማግኘት፡ ወደ ውጪ ወጥቶ ለመስራት ይጥር ነበር። አንድ ሰውም በትንሽ ጎጆ ውስጥ እንዲኖር ፈቅዶለት ነበር። እዚያም ሚስቱ፡ እንደገና ለመውለድ ተቃርባ ሳለች፡ ታላቅና ሰፊ መጥረቢያ ይዛ፡ ለመጣል፡ እንጨት ትቆርጥ ነበር፥ አንዱን ህፃን ዳሌዋ ላይ አዝላ፥ በሌላኛው እጇ ደግሞ እንጨቱን እየጎተተች፥ በክረምት

ብርድ ጊዜ እንዳይራቡ አንዳንድ የጥቁር እንጀራ፡ ፍሬዎችን ለማከማቸት ያንን እንጨት ለመቁረጥ ትወርድ ነበር። ማይ፡ እንዴት እንዳሳዘነችን! ወንድም ውድና እኔ ሄደን የጭነት መኪናዋን በማምጣት፡ ወደዚያ ሄደን እንጨቷን ቆርጠን፡ አምጥተን አስገባንላት። እሷም፡ ያቺ አመስጋኝ ምስኪን ሴት፡ በዚያ ቆማ ነበር። አሳዘነችኝ። እኛም አጥብቀን እንጸልይላቸው ነበር።

173 ትንሽ ህፃን ልጇም የሚጥል በሽታ ያዘው። ሄደን ለትንሹ ህፃን ጸለይንለት፡ እግዚአብሔርም ፈወሰው። በቀደም ደግሞ፡ ባሏ የእምብርት እብጠት ነበረበት፡ ወደ ውስጥም ገባ…

ሳነጋግረው ነበር። ያጨስ ነበር፡ ሁለቱም ያጨሱ ነበር። እሷም ትምባሆ ትጠቀም ነበር፡ እርሱም እንዲሁ፡ የተለመደ የተራራ ላይ ሰዎች፡ ባህርይ ነው። እኔም ስለዚህ ጉዳይ አጥብቄ እነግራቸው ነበር። ትላንት ጠዋት ጎህ ሲቀድ፡ ወደዚያ ሰገባ፡ እነሆ እጆቹን አጣምሮ፡ ወደ ውጪ እየወጣ መጣና፡ እንዲህ አለ፡ "ወንድም ቢሊ፡ እኔ የተለወጥኩ ሰው ነኝ" አለኝ። ቀጥሎም፡ "የመጨረሻዋን ሲጋራዬን አጭሼ ጨርሻለሁ፡ አሁን ደግሞ በጌታ ወገን ነኝ" አለ።

እሷም፡ "እኔም፡ የመጨረሻዋን አጭሼ ጨርሻለሁ" አለች።

ኦህ፡ ዘሩን ዝሩ! "እኔ ጌታ አጠጣዋለሁ። ማንም ከእጄ እንዳይነጥቀው፡ ቀንና ሌሊት አጠጣዋለሁ።"

174 አምላክ ሆይ፡ አሁን እንድትምረን፡ እጸልያለሁ፡ በልባችን አንተን ማገልገል ስለምንፈልግ፡ የልባችንን መሻት ሰጠን። አሁን፡ አባት ሆይ፡ በየቦታው፡ ሁሉም በእጅህ ውስጥ ናቸው። ልጆችህ ናቸው። ጌታ ሆይ፡ እንደ ምሕረትህ አድርግላቸው፥ በፍርድ ሳይሆን፡ በምሕረት ተመልከታቸው። በኢየሱስ ስም እንጠይቃለን። አሜን።

175 ትወዱታላችሁን? [ጉባኤው፡ "አሜን" አለ።—አርታዒ።] በሙሉ ልባችሁ! አሁን፡ መሀረቦች ያላችሁ ሰዎች፡ መውሰድ ትችላላችሁ።

አሁንም፡ አገልግሎቶቻችን፡ ትንሽ ቀደም ብለው የሚጀምሩ ይመስለኛል፡ በሰባት ሰዓት፡ ወይም እንደዚያ አካባቢ። መቼ እንደሚጀምር፡ ወንድም ኔቪል አሁን፡ ባጭር ጊዜ ያስታውቃል።

ዛሬ ጠዋት፡ የጥምቀት ፕሮግራም፡ አለን እንዴ? [ወንድም ኔቪል፡ "ውሃው ተዘጋጅቷል" አለ።—አርታዒ።] ውሃው ተዘጋጅቷል፡ እዚህ ውስጥ በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ ስም ገና ያልተጠመቀ ሰው ካለ፡ ለምን፡ በእርግጥም… ውሃው ለጥምቀት አገልግሎት ተዘጋጅቷል።

176 አገልጋይ ወንድሞችን ሁሉ እናመሰግናለን። ወንድም… እያለሁ ወንድም ፓርኔል፡ አገልግሎትህ እንዴት ነበር፡ ሁሉም ነገር በጥሩ ሁኔታ አለፈ? እንዲሁም ወንድም ማርቲን፡ እና፡ ኦህ፡ እዚህ እጅግ ብዙዎች አሉ፡ ወንድም ሊ ቬይልን እያለሁ። ኦህ፡ በሰፍራው ሁሉ አገልጋዮች ሞልተዋል። እዚህ በመገኘታችሁና፡ በቃሉ ዙሪያ ከእኛ ጋር ኅብረት በማድረጋችሁ በእርግጥም እጅግ እናመሰግናለን።

177 ምናልባት በዚህ ጉዳይ ላይ ከእኔ ጋር ሙሉ በሙሉ ላትስማሙ ትችላላችሁ፥ እንድትስማሙም አልጠይቃችሁም፡ እያችሁ። ብቸኛው ነገር፡ ዝም ብላችሁ እንድታስቡበት ነው። እናንተ የምትነግሩኝ፡ እኔም አስብበታለሁ።

አገልጋዮች ቴፑን ወሰደው፡ “መልካም፡ በዚህ አልስማማም፡” ይላሉ። ያ ምንም ችግር የለውም፡ ወንድሜ። ምናልባት አንተ የተወሰኑ በጎች ትጠብቅ ይሆናል፥ የ—የፈለከውን ትመግባቸዋለህ።

በእግዚአብሔር ፈቃድ በእጄ ለተሰጡት ለእነዚህ ሰዎች ሲባል፡ በተቻለኝ መጠን ከቃሉ ጋር በትክክል ለመቆም እየጣርኩ ነው፡ ምክንያቱም፡ በጎች የሚፈልጉት የበግ ምግብ ነውና። “በጎቼ ድምፄን ይሰማሉ።” የምንኖረውም በዚያ ነው፡ በሚወጣው ቃል ሁሉ… ሁሉም አይደለም… አልፎ አልፎ በሚገኝ ቃል ብቻ አይደለም፥ ነገር ግን ቅዱሳን ሊኖሩበት የሚገባው፡ ከእግዚአብሔር አፍ በሚወጣው ቃል ሁሉ ነው።

አሁን በእግራችን እንቆም። ራሳችንን ዝቅ አድርገን ሳለን…

ወንድም ኔቪል፡ ልትነግራቸው የምትፈልገው አንዳች ነገር አለህ? [ወንድም ኔቪል፡ “የለም” አለ።—አርታዒ።] ወንድም ማን? መልካም።

ሁላችሁም ደህና ናችሁ? “አሜን፡” በሉ። [ጉባኤው፡ “አሜን” አለ።—አርታዒ።] መልካም።

አሁን አንገታችንን ዝቅ እናድርግ።

ወንድም ሊ ቬይል ወደዚህ መምጣት ይችል እንደሆነ፡ ወይም ከቻለ እጠይቀዋለሁ። ወደዚያ ማለፍ ከቻልክ፡ ወንድም ቬይል፡ ከቻልክ።

ወንድም ቬይል እዚህ የኛ ወንድም ነው፡ የመጻሕፍት ጸሐፊ ነው። አሁንም **የሰባቱ የቤተክርስቲያን ዘመናት** የሚለውን መጽሐፍ፡ እያዘጋጀ ነው፡ በ**ሰባቱ ማኅተሞች** ላይ እየሰራ ነው። በቅርቡም አትመን እንደምናወጣቸው ተስፋ እናደርጋለን። መልካም። ወንድም ሊ ቬይል።

እግዚአብሔር ይባርካችሁ።

65-0822M ክርስቶስ በገዛ ቃሉ የተገለጠ ነው
ብራንሃም ተበርናክል
ጀፈርሰንቪል, ኢንዲያና ዩ.ኤስ.ኤ

AMHARIC

©2026 VGR, ALL RIGHTS RESERVED

VOICE OF GOD RECORDINGS
P.O. BOX 950, JEFFERSONVILLE, INDIANA 47131 U.S.A.
www.branham.org

## የቅጂ መብት ማሳሰብያ

ይህ መጽሐፍ የኢየሱስ ክርስቶስን ወንጌል ይሰፋ ዘንድ፣ በቤት ለግል ጠቀሜታም ሆነ ለሌሎች ሰዎች ያለ ክፍያ ለማበርከት፣ በቤት ማተሚያን መጠቀም ይቻላል። ይህ መጽሐፍ ያለ ቮይስ ኦፍ ጋድ ሪከርዲንግስ በጽሑፍ የተደገፈ ህጋዊ ፈቃድ መሸጥም ሆነ፣ አብዝቶ ማተም፣ በዌብ ሳይት ላይ ማስቀመጥ፣ በማከማቻ ዘዴዎች ላይ ማስቀመጥ፣ ወደ ሌሎች ቋንቋዎች መተርጎምም ሆነ የድጋፍ ማሰባሰቢያ አድርጎ መጠቀም የተከለከለ ነው። ህጋዊ መብቱም ሁሉ የተጠበቀ ነው®።

ለተጨማሪ መረጃ ወይም ተጨማሪ ግብዓቶች ቢፈልጉ፣ እባኮትን ይህ አድራሻ ይጠቀሙ፡

Voice Of God Recordings

P.O. Box 950, Jeffersonville, Indiana 47131 U.S.A.

www.branham.org